# ግልጽ ደብዳቤ

## "ዕፀ ሕይወት" የተባለችው ምሥጢር፡

**በእውነት መንፈስና በእግዚአብሔር መንግሥት የተከሠተችባቸው፡**
**የአማናዊቷና የዘለዓለማዊቷ ሔዋን፥ የፍጥረተ ዓለሙ መቅደስና ንግሥት፥**
**የእናት ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም፣**
**የአማናዊውና የዘለዓለማዊው አዳም፥ የፈጣሬ ዓለማትና የካህኑ ንጉሥ፥**
**የኢትዮጵያዊው ልጇ የመሢሑ ኢየሱስ፡**

**ትሑት አገልጋይ፡**
**እኔ፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፡**

## *"የዕፀ በለስ ምሥጢር"* በሚል አርእስት፡

**ሞትን ስላስከተለው፡ አዳማዊውና ሔዋናዊው የሓሰት መንፈስና የክፋት ግዛት፡**
**በትንሣኤ ሰፎንያስ፡ በ፳፻፪ ዓ. ም. ተዘጋጅቶና ታትሞ፡ ለተሠራጨው መጽሓፍ፡**
**የሰጠሁት የማስተካከያ ጦማራዊ መልስ።**

---

**ይኸውም፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡**
**"ዮም ፍሥሓ ኮነ! በእንተ ርደተ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ሐዋርያት!"**
**ማለትም፡**
**"እንኳን ደስ አለን! በዛሬዪቱ ዕለት፡**
**መንፈስ ቅዱስ፡ በሓዋርያት ላይ ወርዷልና!"**
**እያሉ፡ ዓመታዊ በዓሉን የሚያከብሩለት መንፈስ ቅዱስ፡**
**በሚወደስበት ሰሞን የተላለፈና ከዚህ ቀጥሎ የሠፈረላችሁ ነውና፡**
**ይህንኑ ደብዳቤ፡ እንካችሁ ተመልከቱት!**

# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት።
# Ethiopia: The Kingdom of God Services

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥ ኢትዮጵያውያንም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳት፥ የ"ኢትዮጵያ" እና "የኢትዮጵያውያን" የኾነውንም ኹሉ ለመጠበቅና ለማሳወቅ።

To reveal the truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God; and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.


ሰኔ ፲፪ ቀን፥ ፳፻፫ ዓ. ም.

ይድረስ፡ ለ*"የዕፀ በለስ ምሥጢር"* መጽሓፍ ደራሲ ትንሣኤ ሰፎንያስ።
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ።

"እንኳን ለዓመታዊው በዓለ መንፈስ ቅዱስ፡ ኹላችንንም፡ በያለንበት፡ በሰላም አደረሰን!" እያልሁ፡ ኢትዮጵያዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ፤ እግዚአብሔር ይመስገን እኔ ደኅና ነኝ።

እንደፈረንጆቹ አቆጣጠር፡ በJune 23, 2010፡ በአንተ በኩል፡ በመጀመሪያ የላክህልኝ እ-ጦማርህ፡ በተከታታይ ለተለዋወጥናቸው ደብዳቤዎቻችን መነሻ ኾኖ፡ እኔም፡ ይኸው መልእክትህ የደረሰኝ መኾኑን በመግለጽ፡ ሰኔ ፳፫ ቀን፥ ፳፻፪ ዓ. ም. በላክሁልህ መልስ መግቢያነት፡ በመካከሉ፡ በሓምሌ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፪ ዓ. ም.፥ በመጨረሻም፡ በጥቅምት ፲፫ ቀን፥ ፳፻፫ ዓ. ም. ያስተላለፍሁልህ ኹለቱ ገንቢ አስተያየቶቼ፡ የሚታወሱ ናቸው።

ለዚህ ደብዳቤዬ ምክንያት የኾነኝ፡ *"የዕፀ በለስ ምሥጢር"* በሚል አርእስት፡ በ፳፻፪ ዓ. ም. አዘጋጅተህ፡ በይፋ ያሳተምኸውና ያሠራጨኸው መጽሓፍህ፡ በቅድሚያ እንዲደርሰኝ ጥረት አድርገህ፡ ለጊዜው ቢዘገይም እንኳ፡ የኋላ ኋላ ስላገኘሁት፡ እነሆ፡ አኹን፡ አንብቤ ልጨርሰው በመቻሌና በእነዚያ፡ ከላይ በተጠቀሱት የመልስ ደብዳቤዎቼ፡ በእያንዳንዳቸው ውስጥ ተወስተው የተሠነዘሩት አሳቦቼ፡ መነሻ ኾነውኝ፥ የሰጠኋቸውንም የተስፋ ቃሎች ልፈጽም ብዬ መኾኑን፡ አበክረህ እንድታጤነው ላስታውስህ እወድዳለሁ።




መልእ. ሣ. ቁ. ፰፻፲፪፤ ስልክና ዕምነት ቁ. ዐ፲፩-፬-፲፮-፲፰-፹፭ እና ዐ፲፩-፫-፳-00-፹፭፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ።
P. O. Box 812, Addis Abeba, Ethiopia. Tel. & Fax. Nos. 011-4-16-18-85 & 011-3-20-00-85.
P.O.Box 43262, Washington, DC 20010-9262 U.S.A.
Tel. (301) 587-8074 ~ Fax: 301-587-1971 ~ E-mail: info@ethkogserv.org
Website: www.ethkogserv.org

በእነዚያ ደብዳቤዎቼ ውስጥ "የተስፋ ቃሎች" ያልኋቸው፡-

፩ኛ. "ባለፈው መልሴ፡ 'ምናልባት ካስፈለገኝ፡ ተጨማሪ ማብራሪያዎችን፡ ከአንተ የምጠብቅባቸው፥ አለዚያም፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ እምነታችን አኳያ፡ ትኩረትን በመስጠት፡ ራሴ፡ የማስተካከያ አስተያየት የምሰጥባቸው፡ አንዳንድ ነጥቦች ቢኖሩ፡ ...እነዚህን፡ ወደፊት በማስከትለው ደብዳቤዬ እጠቃቅሳቸዋለሁ።' ብዬ የሰጠሁህን ቃሌን፡ አኹን፡ ለጊዜው፡ ላቆየው መገደዴን፡ ላሳውቅህ እወድዳለሁ። ምክንያቱም፡ ከደብዳቤዎችህ ጋር የተላኩትና በመጽሓፍህ የተጠቃለሉት፡ ሦስቱም አባሪዎች፡ የያዟቸው መልእክቶች፡ መጽሓፍህን አንብቤ ስጨርስ፡ በሚኖረኝና ላንተ በምጽፍልህ አስተያየቴ ውስጥ፡ ዐብረው እንዲካተቱ ላደርግ ስለፈለግሁ ነው።"

፪ኛ. "*'የዕፀ በለስ ምሥጢር'* መጽሓፍህን አንብቤ እንደጨረስሁ፡ መንፈስ ቅዱስ ባወቀና ባመለከተኝ፡ የሚኖረኝን ገንቢ አሳብ አከታትልልሃለሁ።" የሚሉት ሲኾኑ፥

፫ኛ. "*መሠረታውያን አሳቦቼ*" ያልኳቸው ደግሞ፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡-

"...ያ፡ ወደፊት የማስከትለው የአስተያየት ደብዳቤዬ፡ ካለፈው እ-ጦማሬ ጋር አያይዤ በላክሁልህ፡ በአራቱ የጸሎቶቻችን መሠረታውያን ክታቦች ውስጥ፡በግልጽ በሠፈረው፡ <u>በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ እምነታችን፡</u> አንተ እና እኔ፡ አንድ የመኾናችንን እውነታ፡ እንዳኹኑ ግንዛቤዬ ኹሉ፡ በዚያን ጊዜም፡ [ማለትም፡'የዕፀ በለስ ምሥጢር' መጽሓፍህን አንብቤ ስጨርስም፡] የሚያጸና ከመኾኑ በስተቀር፡ ሌላ፡ አሉታዊ የኾነ እንከን እንደማይኖርበት፡ ከወዲሁ ልተማመን ችያለሁ።

"እንዲህ ለማለት ያስደፈረኝም፡ ምንም እንኳ፡ ምንባቡን፡ ገና ያላጠናቀቅሁ ብኾንም፡ ከዚህ አያይዤ የጠቀስሁትን አስተማማኝ ቃልህን፡ *"የዕፀ-በለስ ምሥጢር"* ከሚለው መጽሓፍህ፡ የመደምደሚያና የማጠቃለያ ምዕራፍ ውስጥ ተመዝግቦ ስለተመለከትሁ ነው።

"ቃልህም፡ <u>*'አሥራ አራት ዓመቶችን በፈጀብኝ፡ ...በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ፡ ከተባሉት ነገሮች መካከል፡ የሰውን ሰብእና የሚጥሱ ናቸው ተብለው፡ በሰዎች ዘንድ፡ ቁጣን ሊያስነሡ ይችላሉ የሚባሉት መልእክቶች፡ በጠቅላላ፡ መጽሓፍ ቅዱስንና ቅዱስ ቁርዐንን ካልኾነ በቀር፡ እኔን ሊያስጠይቁ እንደማይችሉ፡ ከወዲሁ፡ ላሳውቅ እወዳለሁ። ምክንያቱም፡ የተባሉት ነገሮች ኹሉ፡ በግልጽም፡ ኾነ፡ በምሳሌ፡ በኹለቱም መድበሎች ላይ፡ የተባሉ ነገሮች እንጂ፡ ከእኔ አሳብ የመነጩ አይደሉም። ወይንም ደግሞ፡ በኹለቱ መድበሎች ላይ የተባሉትን ኹሉ መነሻ በማድረግ፡ እኔ፡ በጽሑፍ አብራርቼ ከማቅረብ ውጭ፡ እነዚህን መልእክቶች፡ ከእራሴ ምናብ አፍልቄ ያወጣኋቸው፡ የእኔ ድርሰቶች አይደሉም።"*</u> የሚለው ነው።

*"በአንተ ዘንድ ያለው፡ የእምነት አቋምህ እውነታ፡ ይህ ከኾነ፡ ከዚሁ አቋምህና በደብዳቤህ ውስጥ ከዘረዘርካቸው ከሦስቱ ምርጫዎችህ የተነሣ፡ አንተ እና እኔ፡ በመንፈስ ቅዱስ አንድ መኾናችንን ለማስተዋል አላዳገተኝምና፡ በዚህ መለኮታዊ ድንቅ ሥራ፡ ኹላችንም፡ በያለንበት ደስ ተሰኝተን፡ ባንተው ቃል "በጋራ ይዘን የተነሣነውን መንፈሳዊ ተልእኳችንን" አዋሕደንና አጠናክረን ልንቀጥልበት ይገባናል።*

**"ይህ አቋምህ፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ 'ቅዱሳት መጻሕፍት' በተባሉት ሳይቀር፥ በሌሎቹም፡ የሰዎች** *ሥራዎች ላይ ኹሉ ካለን አቋም ያልተለየ መኾኑን፡ እንዲህ በሚለው መመሪያችን ተረጋግጦ ይገኛል፤* **ይህም፡ "እግዚአብሔር፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ ቀድሞ፡ በጥንተ ተፈጥሮ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልብ ላይ ጽፎትና በየልቦናቸው ውስጥ አሳድሮት፥ ኋላ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት በተገኘው፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና በረከት፡ እንደገና አጽድቆትና አጽንቶት፡ በበለጠ እንዲያበራና እንዲያፈራ ካደረገው፡ <u>ከሕጉና ከሥርዓቱ እውቀት ጋር የማይስማማ፡</u> ማናቸውም ዓይነት፡ ቃልና ነገር፥ ንግግርና መልእክት፥ ይትበሃልና ዘይቤ፥ ፍችና ትርጓሜ፥ ትችና ሓተታ ኹሉ፡ <u>ፍርስና ውድቅ ነው!"</u>** የሚለው፡ የእግዚአብሔር እውነት ነው።

"የዚህ፡ የእግዚአብሔር እውነት ኃይለ ቃል፡ በልሳን ተያይዞ በተላለፈውና በጽሑፍ ተከትቦ በተመዘገበው፥ ሰዎች በተቀበሏቸው፡ 'ቅዱሳት' በተባሉት መጻሕፍት ውስጥ ባለው ኹሉ ላይ ሳይቀር፡ የጸና ኾኖ ይሠራል። (ዘፍጥ. ፩፥ ፳፮-፳፯፤ ፪፥ ፯፤ ፫፥ ፳፪። ኤር. ፴፩፥ ፴፩-፴፬። ዮሓ. ፮፥ ፷፫። የሓዋ. ፪፥ ፩-፬። ዕብ. ፰፥ ፰-፲፪።)

፬ኛ. ከእነዚህ ጋር ዐብሮ ሳይወሳ ሊታለፍ የማይገባው፡ አንድ ቍም ነገር አለ፤ ይኸውም፡ በአንተ በኩል የተሠነዘረውና ወደእኔ የላክኸው፡ መሠረታዊ አስተያየትን የያዘው፡ ቀዳሚና የአደራ ማሳሰቢያህ ነው፤ ያም፡ *"'ያሰፈርኳቸውን ማስረጃዎች በሚገባ ሳትመረምር አርእስታቸውን ብቻ በመመልከት በቀጥታ አንተ ለሥላሜ[ሴ] ከምትሰጠው ትርጉም አንጻር ተርጉመህው ፈጽሞ ይህ ሰው ከሀዲ ነው ብለህ እንዳትጠላኝ፣ ...በአጠቃላይ በመጽሐፌ ውስጥ ካቀረብኳቸው ጥናታዊ ጽሁፎች መካከል አንተ ልትቀበላቸው የማትችላቸው መስለውህ የታዩህን አርእስቶች ባታምንባቸውም ውስጣቸውን ግን ለማንበብ እንዳትጠየፍ፣ ... እንዲሁም ደግሞ አንተ ያላመንክባቸውን መልእክቶቼን በጋራ ይዘን ከተነሳነው መንፈሳዊ ተልእኮ ይልቅ አልቀህ በእኔና ባንተ ግንኙነት ላይ መሰ[ሠ]ረታዊ ጉዳይ ናቸው በማለት እንዳትወስን ከወዲሁ አደራ እልሀለሁ፤'* ብለህ፡ በደብዳቤህ መዝጊያ ላይ የገለጽኸው የሥጋት ስሜትና ያቀረብኸው ተማኅጽኖ፡ በእኔ ዘንድ፡ አስፈላጊነት እንደሌላቸው፡ አኹን መገመቱ፡ ለአንተ አያዳግትህም።" ብዬ የገለጽሁልህ ነው።

፫ኛ. *"ሰባተኛው መለከት"* ለሚለው፡ ለመጽሓፍህ መቅድም ባደረግኸው፡ ክታብህ ውስጥ፡ *"በዚህ ጥናታዊ ጽሁ[ሑ]ፍ ሰዎች ለዘመናት በኃ[ሃ]ይማኖት የተለያዩበት ምክንያት ከንቱ መሆ[ኾ]ኑ ይረጋገጥ ዘንድ አቅራቢው ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቅዱስ ቁርዐን መርምሮና የሰዎችን ሥጋዊ ፍልስፍና ፈትኖ ከማቅረቡ በቀር በውስጡ የተባለው ነገር ሁ[ኹ]ሉ በዚህ ዘመን ከሰማይ የወረደ መለኮታዊ ቃል ወይንም ደግሞ ከጸሐፊው ምናብ የፈለቀ የዘመኑ ወጥ ድርሰት አይደለም።"* ስትል፡ ያመለከትኸው ቃል፡ እዚህ ላይ አግባብነት ስላለው፡ ከመሰሎቹ መካከል ልጠቅሰው ተገድጃለሁ።

እነዚህን የአንተኑ ቃላትና የእኔን ያለፉ ማስታወሻዎች ማዘከሩ ግድ የኾነብኝ፡ ያለምክንያት አይደለም፤ መጽሓፍህን፡ በማነብበት ጊዜ፥ ወይም፡ ካነበብሁ በኋላ፡ በመጽሓፉ ውስጥ የተገለጸውና የቀረበው አንዳንዱ ከባድ አሳብ፡ "ከራስህ የመነጨና ራስህም የምታምንበት ኾኖ የተገለጸና የቀረበ ይኾን? ወይስ፡ ከላይ እንዳወሳሁትና አንተው ራስህም እንዳመለከትከው፡ የሌሎች ኾኖ፡ አንተ፡ በዚያ ላይ በመተቸት የገለጽኸውና ያቀረብኸው ብቻ ይኾን?" በሚል መልክ፡ በኅሊናዬ ውስጥ ለሚወጣ ለሚወርደው አሻሚ ጥያቄ፡ አንዳንዴ መልስ ለመስጠት፡ የምቸገርበት ጊዜ በመኖሩ መኾኑን፡ ልሸሽግህ አልፈልግም። ይኹን እንጂ፡ በእኔ በኩል፡ በመጨረሻ በዚህ ረገድ ያጸደቅሁት መደምደሚያ አሳቤ፡ ያ፡ አሥራ አራት ዓመታትን ለፈጀብህ ጥናታዊ ጽሑፍህ፡ አንተው ራስህ የሰጠኸውንና ከመጽሓፍህ ክፍል፡ <u>*ከላይ፡ ይህን በመሰለው፡ በልዩ ቅርጽ ተጠቅሶ፥ ጎልቶና ተሠምሮበት የተዘከረውን ብያኔህን*</u> መኾኑን ላረጋግጥልህ እሻለሁ።

ከዚህ በላይ የተመለከቱትን፡ እነዚህን ምስክሮች፡ በዚህ መልክ፡ እንደገና ያቀረብኳቸው፡ በቅድሚያ፡ ለጽሑፌ መሠረትና መንደርደሪያ እንዲኾኑኝ በማሰብ ሲኾን፡ ቀጥሎ፡ በዚሁ *"የዕፀ በለስ ምሥጢር"* መጽሓፍህ ውስጥ፡ ከቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ እምነታችን ውጪ የኾኑ፥ ወይም የሳቱ ኾነው ላገኘኋቸው አስተሳሰቦች፡ ተገቢውን ማስተካከያና ማብራሪያ እየሰጠሁ ማለፍ ስላለብኝ፡ ይህን፡ የሚጠበቅብኝን ግዳጅ በምፈጽምበት ጊዜ፡ እነዚሁ ባዕዳን አስተሳሰቦች፡ ምናልባት፡ "የአንተኑ የራስህን እምነት የሚያንጸባርቁ ሊኾኑ ይችሉ ይኾን እንዴ!" ብዬ እንዳልጠራጠር እንደሚደግፉኝ በማሰብ መኾኑን፡ ከወዲሁ፡ አበክረህ እንድትገነዘብልኝ ላሳስብህ እወድዳለሁ።

እንግዴህ፡ ለጽሑፌ መግቢያ፡ ይህን ያህል ከገለጽሁ፡ አኹን፡ ወደዋናው ርእሰ ጉዳይ ዘልቄ በማምራት፡ አስተያየቶቼንና ትችቶቼን፡ በመጠነኛና በአጠቃላይ መልክ፡ እነሆ፡ ከዚህ በታች አበርክቼልሃለሁና ተከታተላቸው! አቀራረባቸውም፡ በመጽሓፉ ውስጥ ባላቸው የገጽ ተርታ አቀማመጥ መሠረት ሳይኾን፡ በቍም ነገር ይዘታቸው፡ ቀለል ያሉትን በማስቀደምና ከበድ ያሉትን በማስከተል መኾኑን እንድታውቀው ይኹን!

## *"የዕፀ በለስ ምሥጢር"* መጽሓፍህን ድርሰትና ይዘት በሚመለከት፡ የተሰጠ ማስተካከያ አስተያየትና ትችት።

፩. የአሌፋትንና የሆህያትን፥ የአኀዛትንና የነቍጣትን ኢትዮጵያዊ ሥርዓት ስለመጠበቅ፡ እኔ፡ በቀደሙት መጻሕፍቴ አማካይነት ያስተላለፍሁትን መልእክታዊ ማሳሰቢያ ተመልክተኸው ይኾናል። አልተመለከትኸው እንደኾነ፡ ልትመለከተው የሚያስፈልግህና የሚጠቅምህ ይመስለኛል። ይህን ማሳሰቢያ ልሰጥህ የተገደድሁት፡ በዚህ ረገድ፡ በአሳብ አገላለጹና በቃላት አመራረጡ፥ በሥነ ጽሑፉ አቀራረብ ጭምር፡ እጅግ በሚደነቀው ድርሰትህ ውስጥ፡ ፈጽመው እንዳይገኙ ከተደረጉት የግእዙ አኀዞች ጋር፡ የሆህያቱ አገባብና የቃላት አበዛዙ ሥርዓት ጥበቃ ተገድፎና ጎድሎ በማየቴ ነው። እነዚህን ግድፈቶችና ጒድለቶች፡ ከብዛታቸው የተነሣ፡ በሙሉ ልዘረዝራቸው ስለሚከብዱ፡ አስፈላጊ እየኾኑ፡ ከመጽሓፍህ በማውጣጣቸው ጥቅሶች ውስጥ የማገኛቸውን ብቻ እያመለከትኋቸው አልፋለሁ።

በአጠቃላይ ግን፡ ግእዝን ማወቅ፡ ለደራሲ ቀርቶ፡ ከዚያ የተለየ፡ ማንኛውም ዓይነት ሙያ ላለው፡ ለሌላው፡ ለማነኛውም ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊትም ቢኾን፡ ፍጹም አስፈላጊ መኾኑ፡ በእውነተኞቹ የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ የሚያነጋግር፥ የሚያጠያይቅም አይደለም።

፪. በምዕራፍ አራት፡ ገጽ ፵፬ (44)፥ *"አዳም ተብሎ የተጀመረው ሰው መሢሕ ሆ[ኾ]ኖ ተፈጸመ"* በሚለው ንዑስ ርእስ ሥር፡ በአንቀጾች ፩ እና ፪ ውስጥ የሚነበበው፡ *"እየተፈበረከ"* የሚለው ቃል፡ *"fabrica"* ከሚለው ፈረንጂኛ የተወሰደ ሲኾን፥ እርሱም፡ ሰው-ሠራሽ ከኾነው ማምረቻና ከእርሻ ለሚመረት ዕቃ፥ ወይም፡እህል እንጂ፡ ማሕፀን እያፈራ ለሚያስገኘው ሰብአዊ ፍጡር፡ ሊውል የሚያስፈልግ አይመስለኝም። ለሰው፡ "እየተራባ" ቢባል ይበቃል፤ አግባብም ይኾናል።

፫. በዚሁ ምዕራፍ፡ *"ከአምላክ እንደአምላክ ኾኖ መፈጠር ማለት ምን ማለት ነው?"* በሚለው ንዑስ ርእስ ሥር፡ በገጽ ፶፬ (54)፥ አንቀጽ ፫ ላይ፡ የመሢሕ ኢየሱስን፡ *"የተወጋውን ቊስል በዓይኑ ማየት ተስኖት፡ በእጁ ዳሶ ማመኑ"* የተባለው፡ "ቶማስ" መኾኑ፡ በምሥራቹ መጽሓፍ (በወንጌሉ) ውስጥ በተጻፈው ቃል፡ ተረጋግጦ ስለሚታወቅ፡ *"ኒቆዲሞስ"* የተባለው ስም የገባው በስሕተት ለመኾኑ አያጠራጥርም።

፬. በምዕራፍ ስድስት፤ ገጽ ፻፲፰ (118)፥ አንቀጽ ፪ እና ፫ ላይ፡ *"ክህነተ ሥልጣን"* የሚለው ድርብ ቃል፡ "ሥልጣነ ክህነት" ቢባል፡ ትክክል ይኾናል።

፳. በምዕራፍ አንድ በገጽ ፬ (4)፥ *"'አዳም (ዕፀ በለስን) በመብላቱ፡ ተሳስቷል!' ከተባለ፡ 'አምላክም፡ በመትከሉ ተሳስቷል!' ማለት ነውን?"* በሚለው ዋና ርእስ መግቢያ አንቀጽ ውስጥ፡ *"በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ ቀደምት የኃ[ሃ]ይማኖት ሊቃውንቶች [ሊቃውንት/ሊቆች] ሙሴን 'የኦሪት ደራሲ ነው!' በሚያስብል መልኩ የተሳሳተ ስም ሰተውት [ሰጥተውት] እናገኛለን። ነገር ግን ሙሴ እራሱ በዘፍጥረት ታሪክ ውስጥ ተደራሲ ነው እንጂ፡ የኦሪት ደራሲ አይደለም። በእርግጥ፡ ሙሴ የኦሪት ፀሀፊ [ጸሓፊ] ነው።"* ብለህ ያሠፈርኸው አሳብ አለ።

ይህ አሳብ እንዳለ ኾኖ፡ **"ሙሴ፡ ያንኑም እንኳ ቢኾን፡ ያገኘውእኮ፡ በኢትዮጵያዊው አማቱ፡ በካህኑ ዮቶር አማካይነት፡ ከኢትዮጵያውያን ነው!"** የሚለውን ማረጋገጫ ቃል አክለህበት ቢኾን ኖሮ፡ ምንኛ የተሟላ በኾነ ነበር!? ይህንም፡ የእግዚአብሔር እውነታ፡ ቀደም ብለህ ካነበብሃቸው መጻሕፍቴ ሳታጤነው እንዳልቀረህ አምናለሁ።

፳፩. ከዚህ መግቢያ አንቀጽ ቀጥሎ፡ በዚሁ ምዕራፍ አርእስት ሥር ለተካተተው ሓተታ፡ የሚከተለውን ማብራሪያ እሰጥበት ዘንድ አስፈላጊ ኾኖ አግኝቼዋለሁ፡-

አዳም (ሔዋንም በውስጡ እንዳለች ኾና) "አትብላ!" የሚለውን ትእዛዝ፡ ከፈጣሪው ሲቀበል፡ በእግዚአብሔር መልክ ስለተፈጠረ፡ እርግጥ፡ በዚያ በቀዳማዊው የብቅዓት ደረጃው፡ ያን መለኮታዊ ትእዛዝ ለመቀበልና ለመፈጸም፥ ወይም፡ ላለመቀበልና ላለመፈጸም ይችል እንደነበረ አያከራክርም። ነገር ግን፡ ያችን፡ ክፉውንና ደጉን ለይታ የምታስታውቀውን፡ የእውቀት፡ ማለትም፡ የዕፀ በለስ ፍሬ፡ ገና አልበላም ነበርና፡ 'አትብላ!' የሚለውን ትእዛዝ መተላለፍ፡ ደግ እንጂ፡ ክፉ መኾኑን፡ ገና ለይቶ እንደማያውቅ ግልጽ ነው፤ እንደአንድ ሕፃን ማለት ነው።

ለሕፃን፡ ማንኛውም ዓይነት አሳብ፥ ነገርና ድርጊት ኹሉ፡ መልካም ብቻ እንጂ፡ በእርሱ ዘንድ፡ በጎ እና ክፉ፥ ወይም፡ መልካም እና መጥፎ የሚባል አሳብ፥ ነገርና ድርጊት እንደሌለ፡ በገሃድና በተጨባጭ የታወቀ ነው። በዚህ መልክና ይዘት፡ እርግጥ፡ አዳም፡ "አትብላ!" የሚለው ትእዛዝ፡ ደግ መኾኑን ብቻ አውቆ፡ የመቀበልና የመፈጸም ብቸኛ ዓቅም ነበረው፤ ነገር ግን፡ ትእዛዙን አለመቀበሉና አለመፈጸሙ "ክፉ" መኾኑን፥ ጥፋት፥ ወይም፡ ኃጢኣት ኾኖበት፡ ለሞት እንደሚያበቃ፥ ሞትም ራሱ ምን እንደኾነ፡ እንደዚያ፡ ምሳሌው እንደኾነው ሕጻን፡ ገና፡ ምኑንም የማያውቅ፥ የዋህ እንደነበረ፡ ከቶ ሊታበል የማይቻል እሙን ነገር ነው።

በመሠረቱ፡ "ዕፀ በለስ"፡ ክፉና ደጉን ለይታ የምታስታውቅ ፍሬን የምትሰጥ የእውቀት ዛፍ እንጂ፡ ራሷ፡ ክፉን የምታሳስብ፥ የምታናግርና የምታስተድርግ የክፉት ዛፍ አይደለችም። ፍጹም የአምላክን መልክ ለመምሰል፥ ማለትም፡ አዳምን፡ "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" አሰኝታ፡ እንደእግዚአብሔር እንዲያስብ፥ እንዲናገርና እንዲያደርግ ለማብቃት፡ ዕፀ በለስን መብላት ነበረበት የሚያስሰኘው ስለዚህ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ እግዚአብሔር የፈጠረው፡ ክፉና ደጉን ለይታ የምታሳይ፡ እውቀትን እንጂ፡ ክፉትን አለመኾኑ፡ በዚህ ይታወቃል። እግዚአብሔር፡ መልካምን ብቻ እንጂ፡ ክፉትን አልፈጠረም። ክፉትን፡ ኋላ ያመጣው፡ በቅድሚያ፡ መንፈሳዊው ፍጡር፡ ሰይጣን ሲኾን፡ ቀጥሎ፡ ሥጋዊው ፍጡር ሰው፡ ያንኑ ሰይጣናዊዉን ፈለግ በመከተል፡ ደገመው፤ አጸናው።

እግዚአብሔር፡ አዳምን፡ "አትብላ!" ያለው፡ አዳም፡ የዚያችን፡ የዕፀ-በላስን ፍሬ በመብላቱ፡ በእግዚአብሔር መልክ የመፈጠሩን ደረጃ፡ ከፍ አድርጎ፡ ፍጹም የሚያሟላው መኾኑንና ያ የሚበጀው መኾኑን፡ ይኸው ፈጣሪው አጥቶት አልነበረም፤ ነገር ግን፡ አዳም፡ ዕፀ በለስን በልቶ፡ ደጉንና ክፉውን ካወቀ በኋላ፡ ምርጫው፡ "የፈጣሪው ፈቃድ የኾነውን፡ መልካሙን በመምረጥ፡ ፍጹም እግዚአብሔርን የመምሰል መልኩን የሚያሟላበትን ጸጋ መቀዳጀት ሳይኾን፡ የፈጣሪው ፈቃድ ያልኾነውን መንገድ እንደሚኾን ስላወቀ ለመኾኑ፡ በዚያው በፈጣሪ ቃልና ኋላ በኾነው ድርጊት ታይቷል።

ይኸውም፡ አዳም፡ ዕፀ በለስን በበላ ጊዜ፡ "አዬ! ለምን አዳም ይህን አደረገ?" ብሎ ፈጣሪው ሳይጸጸት፡ "ናሁ አዳም ኮነ፡ ከመ አሐዱ እምኔነ፡ ያእምር ሠናየ ወእኩየ!" ማለትም፡ "መልካሙንና ክፉውን ያውቅ ዘንድ፡ እነሆ፡ አዳም፡ ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" የሚለውን፡ ይኸው ሰብአዊ ፍጡሩ፡ለተወጠነለት፡ ለፍጹም የእግዚአብሔርነቱ መልክ ለመብቃቱ፡ ማረጋገጫ የኾነውን መለኮታዊ ቃል ማስሰማቱ ነው። (ዘፍጥ. ፫፥ ፳፪።)

እዚህ ላይ፡ እግዚአብሔር፡ "ከእኛ" ያለው፡ "አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ" ተብሎ የታወቀበትን፡ የ፩ነቱንና የ፫ቱን (የሥላሴ) ምሥጢር የሚያካትተውን፡ የእምነታችንን መሠረታዊ እውነታ የሚያመለክት እንጂ፡ ከዚህ ቀጥሎ እንደሚታተተው፡ የሰይጣንን አማካሪነት የሚጋብዘውን፡ አስተሳሰብ የሚያስተናግድ አለመኾኑ በቅድሚያ ሊዘገብ ያስፈልጋል።

አዳም፡ "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" ያሰኘውንና ፍጹም ብቅዓት ያገኘበትን፡ የእግዚአብሔር መልክነቱን፡ እውን (አማናዊ) የሚያደርገው፡ እንደእግዚአብሔር፡ በቅድሚያ፡ መልካሙንና ክፉውን ለይቶ ባወቀበት የአእምሮ ዓቅሙ፥ ቀጥሎ፡ በመምረጥና በመወሰን ሥልጣኑ፥ በመጨረሻውም፡ የምርጫ ውሳኔውን፡ በመተግበር ኃይሉ ተጠቅሞ፡ ክፉውን ትቶ፡ የፈጣሪው ፈቃድ የኾነውን መልካሙን መፈጸም ሲችል ብቻ ነው።

ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደኾነ፥ አፈጻጸሙም እንዴት እንደኾነ፡ ሰው በኾነው፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስና በሓዋርያው ጴጥሮስ በታሰበውና በተነገረው፥ በኾነውና በተደረገው እውነታ ታይቷል፤ ተረጋግጧልም።

ይኸውም፡ ክርስቶስ፡ ተይዞና ታሥሮ፥ የመስቀል መከራንም ተቀብሎ ሊሞትና በሦስተኛው ቀን ሊነሣ የሚገባው መኾኑን፡ ለደቀ መዛሙርቱ ነግሮአቸው፡ ይህንኑ ጽዋውን ለመቀበል፡ ወደኢየሩሳሌም እየተጓዙ ሣሉ፡ የሌሊቱን ሰዓት ለማሳለፍ ባረፉበት ቦታ፡ ቅዱስ ጴጥሮስ፡ ወደጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀርቦ፡ "መልካም ነው!" ብሎ በመገመት፡ በጽሙና ላቀረበለት አሳብ፡ ጌታችን፡ በኃይለ ቃል በሰጠው ምላሽ፡ የተከሠተው እውነታ ነው።

የዚያን እውነታ ምንነት፡ እንዲህ የሚለው የመጽሓፍ ቃል ገልጦታል፡- **"ወተሰጥዎ ጴጥሮስ፤ ወአኀዘ ይክልእ እንዘ ይብል፡ 'ሓሰ ለከ እግዚኦ ይኩን ላዕሌከ ዝንቱ!' ወተመይጠ [እግዚእነ]፡ ይቤሎ ለጴጥሮስ፡ ሑር እምድኅሬየ ሰይጣን! እስመ ኮንከ ማዕቅፍየ፥ እስመ ኢትሔሊ ዘእግዚአብሔር፡ ዘእንበለ ለሰብእ።" ማለትም፡ "ጴጥሮስም መልሶ፡ 'አቤቱ! ይህ፡ በአንተ ላይ ሊደርስብህ፡ ፈጽሞ አይገባም!' እያለ ይከላከለው ጀመር። ጌታችን ኢየሱስ ግን፡ መለስ ብሎ፡ ጴጥሮስን፡ 'አንተ ሰይጣን! ከኋዬ ወግድ! ዕንቅፋት ኾነህብኛልና፤ የሰውን እንጂ፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለመፈጸም አላሰብህምና።** (ማቴ. ፲፮፥ ፳፩-፳፫።)

፯. በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ከሠፈረው ሰፊ ሓተታ ጋር *"በተጨማሪ ይህ አባባል አምላክ በእራሱ መልካምነት ላይ ብቻ ተወስኖ ሳይሆ[ኾ]ን በክፉነት ላይም ተመርኩዞ ሰውን በመልካችን እንደምሣሌአችን እንፍጠር በማለት ከሰይጣን ጋር መምከሩን ያረጋግጥልናል።"* ብለህ፡ ለምዕራፉ፡ መዝጊያ ዐረፍተ ነገር ላደረግኸው ጠጣር ቃል፡ አስፈላጊ የኾነውን፡ ከዚህ የሚከተለውን ማብራሪያ መልስ፡ ይኸው ጽፌልሃለሁና፡ ተመልከተው!

በድርሰትህ ውስጥ፡ ያን ያህል፡ የአምላክነት ዕሪና (እኩልነት) እና የመጨረሻው ታላቁ ክብር ተሰጥቶት፥ ለዚያ ልዕልናም በቅቶ፡ የእግዚአብሔር ወልድ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ተገዳዳሪ በመኾን፡ ለእግዚአብሔር አማካሪነት ሹመት የታጨው፡ ያ "ሰይጣን"፡ ለመኾኑ ማነው? ያው የታወቀው፡ በመልአክነት ስሙ "ሳጥናኤል" ተብሎ ይታወቅ የነበረው፥ የኋላ ኋላ ግን፡ በክፋት ምንጭነቱ፥ በክህደት ሥርነቱና በሓሰት አባትነቱ ተጋልጦ፥ ከመልአካዊ የእልቅና ማዕርጉ ተዋርዶና ወደጽንፈ ደይን ዐዘቅት ተጥሎ፡ በግዞት የሚኖረው፡ "ዐውሬ፥ እባብ፥ ዘንዶ፥ ርኩስ መንፈስ፥ የአጋንንት አለቃና ዲያብሎስ" በሚል የጥፋት ስመ ግብሩ እየተጠራ ያለው፡ ከቀደሙት ፍጡራን መካከል አንዱ የኾነው ፍጥረታዊ አካል አይደለምን? ወይስ ሌላ?

እርሱ ከኾነሳ ታዲያ፡ እሱማ፡ በቀድሞ ደረጃው፡ እነቅዱሳን ሚካኤልና ገብርኤል ይተካከሉት የነበረው መንፈሳዊ ፍጡር አይደለምን? ደግሞስ፡ በዚያ ተፈጥሮ ባሕርዩና አካሉ፡ እንኳንስ፡ በአኹኑ የዝቅጠት አኗኗሩ ቀርቶ፡ በቀድሞው፡ የርእሰ ሊቃነ መላእክት ህልውናውም እንኳ ቢኾን፡ ከሌሎቹ፡ መላእክትና ሊቃነ መላእክት ተለይቶ ከፍ የሚልበት፡ ለእርሱ የተለየ፡ አንዳችም የመሥፈርት ግላዊነት አልነበረውም። በባሕርዩም፥ በአካሉም፡ ተፈጥሮው፡ ያው መልአካዊ ነው።

ታዲያ! በዚያ፡ የቅድስና ባለሟልነቱ፥ ክብሩና ማዕርጉ ጊዜ ያላገኘውን፥ ከእርሱ ውርደትና ውድቀት በኋላም፡ በታማኝነታቸውና በቅድስናቸው፡ የእግዚአብሔር ባለሟሎቹ ኾነው የቀጠሉት፡ የዛሬዎቹ ብርሃናውያን ሊቃነ መላእክት ያላገኙትን፡ ያን የመሰለውን፡ የአምላክነት ሥልጣንና ጸጋ፡ ለእርሱ ተለይቶ ሊስሰጠው፡ እንዴት ተደፈረ?

እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያው የፍጥረት ልደት፡ በራሱ መልክ ሊፈጥረው፥ የኋላ ኋላም፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ራሱ ተወልዶበት፡ ሊያድነውና ለዘለዓለም ሕይወት ሊያበቃው ያሰበውን "ሰውን" ያህል ዕፁብ ድንቅ ሕያው አካል፡ "በመልካችን፥ እንደምሣሌያችን እንፍጠር!" ብሎ ይህን ውጥኑን፡ ለሌላ ቀዳሚ ፍጡር ሊያካፍል ፈልጎ ቢኾን እንኳ፡ ለዚህ የአማካሪነት ሹመት፡ እንዴት፡ ፈጣሪ፡ ይህን "ሰይጣን" የተባለውን ጉድ፡ "ወደአሳቡ ሊያስገባው ይቃጣ ይኾናል!" እንኳ ብሎ የሚገምት ሰብኣዊ አእምሮ ሊኖር ከቶ ይችላልን? በእኔ ግምት፡ የሚኖር አይመስለኝም።

ደግሞስ፡ እንኳንስ፡ እግዚአብሔርን ያህል ፍጹም ታላቅ፡ የእውነትና የእውቀት ፈጣሪና ባለቤት ቀርቶ፡ እርሱ፡ አዋቂ አድርጎ የፈጠረው ሰው እንኳ፡ ሊያደርግ ያሰበውን ምሥጢራዊ ዕቅዱን የሚገልጸውና የሚያማክረው፥ የሚያዋየውና የሚያካፍለው፡ እኩያው፥ ወይም የበላዩ፥ የበታቹም ቢኾን፤ለሚወድደውና ለሚያከብረው፥ ለሚያምነውና ለሚያቀርበው አይደለምን? ሥርዓቱና ወጉ እንዲህ ከኾነ፡ ቅዱሱና መልካሙ ፈጣሪ፡ በራሱ መልክና በዘለዓለማዊነት ሊፈጥረው ስላሰበው፡ ግሩምና ድንቅ ሥራው አፈጣጠር፡ የቱን ያህል፥ ምንስ ቢቸግረው ነበር፡ የለየለት ተቃዋሚው የኾነውን፡ በአጠራሩ እንኳ፡ "ርኩስና ክፉ መንፈስ" የተባለውን፡ ሰይጣንን፡ ለዚህ ለመጨረሻው ባለሟልነት ሊመርጠው የቻለው?

በታማኝነታቸው፡ ከወርቅ ይልቅ ተፈትነውና ጠርተው የወጡት፡ የቅርብ አገልጋዮቹ፡ እነቅዱሳን ሚካኤልና ገብርኤል፥ እነርሱንም የመሰሉት፡ በእልፍ አእላፋት፡ ወትእልፊተ አእላፋት የሚቆጠሩት መላእክቱና ሊቃናተ መላእክቱ፡ በአጠገቡ መኖራቸው እየታወቀ፡ "ይህ፡ ከቶ እንዴት ሊታሰብ ተቃጣ!?" ብሎ የሚጠይቅ አስተዋይ ሰብኣዊ ፍጡር እንደሚኖር ሳይገመት መቅረቱ ያስደንቃል!

እንዲያው ለመኾኑ፡ ፈጣሪ፡ በፈጣሪነቱ አማካሪ አያስፈልገውም እንጂ፡ ቢያስፈልገው እንኳ፡ በቅርቡ ያሉትንና የበቁትን፡ እኒህን ንጹሓን ባለሟሎቹን ያማክራል እንጂ፡ እነርሱ እያሉ፡ እንዴት ወደካደውና ወዳመፀበት ፍጡሩ ለምክር ይኼዳል? አይኼድም።

እነአርዮስ እንዳደረጉትና በዚህ ጽሑፌም ውስጥ፡ ወደፊት በበለጠ እንደሚጋለጠው፡ የእግዚአብሔር ወልድ የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮታዊና ትስብእታዊ ማንነት፡ ወደፍጡርነት ለማዋረድ፡ በመጽሓፍህ ውስጥ፡ ለካ፡ ያን ያህል ረቂቅ ሙከራ የተካኼደው፡ "የዚህኑ፡ 'ሰይጣን' የተባለውን ፍጡር፡ ክብርና ሥልጣን፡ ወደአምላክነት ደረጃ አልቆ በማድረስ፡ በቅድሚያ እርሱን፡ ከመጨረሻው የልዕልና ማዕርግ የማብቃቱን ተግባር ለማመቻቸት ሲባል ነው!" ብሎ መደምደሙ አያዳግትም። ይህም፡ በቦታው፡ በአግባቡ ይተችበታል።

፰. በምዕራፍ ሁ[ኹ]ለት፣ በገጽ ፲፯ (17)፥ *"በአምላክ ስ[ሥ]ልጣን ሥር ከጥንት ከዘለዓለም የነበረ እንጅ ያልተፈጠረ"* በሚለው ዋና ርእስ ሥር በሠፈረው ጽሑፍ ውስጥ፡ ባሕርዩ መንፈስ ቅዱስ የኾነውን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስንና በግብሩ፡ የክፋት አበጋዝ የኾነውን "ሰይጣን" የተባለውን ርኩስ መንፈስ ለማስተካከል ሲባል፡ አኹንም እንደገና፡ የሥነ ፍጥረት ልደትን ምሥጢር፡ በረቀቀ ስልት በመጠቀም፡ የተሳሳተ ሓተታ ሊስሰጥበት ሙከራ ተደርጓል።

የሙከራው ይዘት፡ ምን ዓይነት እንደኾነ ለይቶ ለመረዳት፡ እጅግም አያስቸግርም፤ ለምዕራፉ ሰፌ ሓተታ መግቢያ በኾነው ዐረፍተ ነገር፡ በቀላሉ፡ ወዲያው ይታወቃል፤ ይህም፡ *"የመልካምና የክፉ መንፈስ ተቃራኒነት በሰው ሥነ ምግባር ተንፀባርቆ ከመገለጡ በፊት ተቃራኒነታቸው በእንዲህ ያለ ግዜ እና ቦታ ተከሰ[ሠ]ተ ብሎ መናገር የሚከብድ ቢኾንም ከጥንት ከዘለዓለም ግን ሁ[ኹ]ለቱም መንፈሶች ተቃራኒነታቸው እንዳለ ሆ[ኾ]ኖ እማይወሰን እኩል እ[ዕ]ድሜ እንደነበራቸው ዘፍጥረትን መሰ[ሠ]ረት በማድረግ ብቻ በርግጠኝነት መናገር ይቻላል።"* የሚለው ነው።

የዚሁ ሙከራ ረቂቅ ስልት፡ ሰይጣን፡ ስለማናቸውም ነገር፡ መልካምነቱንና መጥፎነቱን፥ ወይም፡ ክፉነቱንና ደግነቱን ለይቶ ለማወቅና ከኹለቱ አንደኛውን ለመምረጥ፥ ስለዚሁ ምርጫውም በቍርጥ ወስኖ፡ ውሳኔውን ለመተግበር እንዲችል ያደረገውን ፍጹም ሥልጣን፡ እንደሰው ኹሉ፡ እርሱም፡ እንዲሁ፡ በጸጋ ከፈጣሪው ስላገኘና በዚያ ተጠቅሞ፡ ከመልካሙ ይልቅ፡ ራሱን፡ ለክፋት፥ ለክህደትና ለሓሰት አባትነት በፍጹም ጽናት አሳልፎ ስለዳረገ ብቻ፡ ያን ሥልጣን፡ ማንም ሳይጠይቀውና ሳያስገድደው፡ በፈቃዱ ካቀዳጀው፡ ከቸር ፈጣሪው ከእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እኩል ዕድሜ እንዳለው ተደርጎ መቅረቡ ነው።

አዎን! "ሰይጣን" የተባለውን አንድ ፍጡራዊ ርኩስ መንፈስ፡ ከፈጣሪው መንፈስ ቅዱስ ጋር ለማስተካከል ተሞክሮአል። ከዚህ ከንቱ ግብ ለመድረስ ደግሞ፡ በመጀመሪያ፡ ፈጣሪን፡ ወደፍጡርነት ማዋረድ፥ ከዚያም፡ መናፍስት ኾነው ከተፈጠሩት መላእክት መካከል፡ አንዱ የኾነውን፥ ያውም፡ በጥፋት ድርጊቱ ምክንያት ከዚያ የመልአክነት ማዕርጉ ተሽሮ፡ ለደይን እሥራት የተዳረገውን፡ ፍጡር መንፈስ፡ ከእኩዮቹ ፍጡራን መሰልነት ለይቶ አውጥቶ፡ ለፈጣሪነት ክብር ማብቃት አስፈልጓል።

እዚህ ላይ፡ ይህን የመሰለው፡ ከቀደመው ይልቅ እጅግ የባሰው ክፋት የተፈጸመበት ማን ኾኖ ተገኘ? ፈጣሪ ነዋ! ይገርማል። በተደጋጋሚ የተፈጸመው፡ የቀደመው ክፋት አንሶ፡ አኹን ደግሞ፡ እንደገና። አዎን! እንደገና! በዚህ ረገድ፡ ፍጡሩ ኹሉ፡ "ሰይጣን" ጭምር፡ ከፈጣሪው፡ በችሮታ በተለገሣቸው፡ ከላይ በተዘረዘሩት የሥልጣናት ጸጋዎች ተጠቅሞ፡ እንደፈጣሪው፡ ከክፉው ይልቅ፡ ራሱን፡ ለመልካሙ ባለቤትነት በማስቻል፡ ፈጣሪውን መስሎ ይኖር ዘንድ፡ ብቅዓቱን ለሰጠውና ከፍጡሩ፡ ያን መልካሙን ጣፋጭ ፍሬ ለሚጠብቀው ፈጣሪ፡ አኹንም፡ እንደገና የተመለሰለት ውለታ፡ ይህ ኾኖ ተገኘ!

የሰይጣን ማንነት፡ ከላይ፥ ቀደም ብሎም፡ በሚበቃ ስለተገለጸ፡ እዚህ ላይ እንደገና ማተቱ፡ አስፈላጊ አይኾንም።

## የሥነ ፍጥረት ምሥጢር፡ ገሃድ ማስረጃነት።

በተሳሳተ ረቂቅ ስልት፡ እንዲጠቅም ሙከራ የተደረገበት የሥነ ፍጥረት ልደት ዜና፡ በፈጣሪ ጣቶች፡ በየልባችን ጽላት ላይ ብቻ ሳይኾን፡ በግእዛችን ቅዱሳት መጻሕፍትም ጭምር ተጽፎ የታወቀበት ቃል፡ ንባቡም፥ ትርጓሜውም፡ ግልጽ ነው፤ ይኸውም፡ "በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር፡ ሰማየ ወምድረ!" ማለትም፡ "በመጀመሪያ እግዚአብሔር፡ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ!" በማለት፡ በረቂቅነትና በግዙፍነት፥ በመንፈስና በሥጋ፥ በመላእክትና በሰው ልጆች የተከሡቱትን፡ ኹለቱን ታላላቅ የፈጣሪ ዕፁብ ድንቅ የሥነ ፍጥረት ክፍሎች ከገለጠ በኋላ፡ "ሰማይ" ስለተባለው፡ ስለቀዳሚውና ስለረቂቁ፥ ስለመንፈሳዊውና ስለመላእክቱ የሥነ ፍጥረት ዘርፍ ነገር፡ በምንም መንገድ ማውሳቱን፡ እዚያው ላይ ጨርሶ አቁሞና በሙሉ ትቶ፡ ወዲያው አከታትሎ የቀጠለው፡ በተለይ፡ "ምድር"ን ብቻ የሚመለከተውን መኾኑ ነው።

ያም፡ "ወምድርሰ ሀለወት እምትካት ዕራቃ፤ ወኢታስተርኢ፤ ወኢኮነት ድሉተ። ወጽልመት መልዕልተ ቀላይ። ወመንፈሰ እግዚአብሔር ይጼልል መልዕልተ ማይ።" ማለትም፡ "ምድር ግን፡ ባዶዋን ነበረች፤ አትታይም ነበር፤ አልተዘጋጀችም ነበር። ጨለማም በጥልቁ ውኃ ላይ ነበር። እግዚአብሔር የፈጠረውም ነፋስ፡ በውኃው ላይ ነበር።" በሚለው ቃል፡ ተረጋግጦ ይታወቃል።

ይኸ፡ "ሰማየ" ያለው ሰማይ፡ ያ፡ ቀዳማዊውና ረቂቁ፥ መንፈሳዊውና የመላእክቱ የኾነው፡ ሰማያዊው እንጂ፡ በኹለተኛው፡ የፍጥረት ቀን የተፈጠረው፡ ምድራዊው "ሰማይ" አለመኾኑን፡ እንዲህ የሚለው፥ ከዚህ የሚቀጥለው ተከታዩ ዜና፡ በሚበቃ ያስረዳል። "ወገብረ እግዚአብሔር ጠፈረ፤ ወፈለጠ እግዚአብሔር፡ማእከለ ማይ ዘመልዕልተ ጠፈር፥ ወማእከለ ማይ፡ ዘመትሕተ ጠፈር። ወሰመዮ እግዚአብሔር፡ ለውእቱ ጠፈር፡ 'ሰማየ'፤ ወርእየ እግዚአብሔር፡ ከመ ሠናይ። ወኮነ ሌሊተ፣ ወጸብሐ፤ ወኮነ ክልኤተ ዕለተ።" ማለትም፡ "እግዚአብሔርም፡ ጠፈርን ፈጠረ፤ ከጠፈር በታች ባለው ውኃና ከጠፈር በላይ ባለው ውኃ መካከል ድንበር ለየ። እግዚአብሔር፡ ይህን ጠፈር፡ 'ሰማይ' አለው። እግዚአብሔር፡ መልካም እንደኾነ አየ፤ መሸም፣ ነጋም፤ ኹለት ቀን ኾነ።"

ከዚያ በማያያዝ፡ "ወይቤ እግዚአብሔር፡ 'ለይኩን ብርሃን!' ወኮነ ብርሃን። ወርእዮ እግዚአብሔር ለብርሃን፡ ከመ ሠናይ ውእቱ። ወፈለጠ እግዚአብሔር፡ ማእከለ ብርሃን፥ ወማእክለ ጽልመት፤ ወሰመዮ እግዚአብሔር፡ ለብርሃን፡ 'ዕለተ'፤ ወለጽልመት፡ 'ሌሊተ!' ወኮነ ሌሊተ፤ ወጸብሐ፤ ወኮነ፡ አሐደ ዕለተ።"

ማለትም፡ "እግዚአብሔርም፡ 'ብርሃን ይኹን!' አለ፤ ብርሃንም ኾነ። እግዚአብሔርም፡ ብርሃንን፡ መልካም እንደኾነ አየ። እግዚአብሔርም፡ ብርሃንንና ጨለማን ለየ። እግዚአብሔር፡ ብርሃኑን፡ 'ቀን'፥ ጨለማውን፡ 'ሌሊት' አለው። መሸም፤ ነጋም፤ አንድ ቀን ኾነ።" የሚለው ጥቅስ ይገኛል። (ዘፍጥ. ፩፥ ፩-፰።)

ይህ ቃልና ድርጊቱ ኹሉ የሚመለከተው፡ በረቂቅነትና በመንፈሳዊነት ህልውና ያለውን፡ "ሰማየ"፡ ማለትም፡ "ሰማይን" ያለውን፡ ቀዳማዊዉንና የመላእክቱን የሥነ ፍጥረት ዘርፍ ሳይኾን፡ "ወምድረ" ማለትም፡ "ምድርን" የሚለውን፡ ምድራዊውን የሥነ ፍጥረት ዘርፍ መኾኑን በግልጽ ያስረዳል።

ቀጥሎ፡ ፍጡራኑ፡ የመዓልቱን (የብርሃኑን) እና የሌሊቱን (ጨለማውን) ጊዜ ለመለየት ይቻላቸው ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡ በአራተኛው ቀን፡ በፈጠራቸው፡ በፀሓይና በጨረቃ የሚለካው፡ የዛሬው "የፍጡራኑ፡ የሃያ አራት ሰዓታት ቀን"፡ እግዚአብሔር፡ ፍጥረቱን ፈጥሮ፡ "ሰንበት" በተባለው፡ በሰባተኛው ቀን፡ ካረፈባቸው ከስድስቱ "የእግዚአብሔር ቀኖች" በዓይነትም፥ በመጠንም፡ እጅግ የተለየ መኾኑን ማስተዋል ይገባል።

ይህም እውነታ፡ "ወገብረ እግዚአብሔር፡ ክልኤተ ብርሃናተ ዐበይተ፤ ዘየዐቢ ብርሃን፡ ከመ ይምልክ መዓልተ፤ ወዘይንእስ ብርሃን፡ ከመ ይምልክ ሌሊተ ምስለ ከዋክብት። ወሤሞሙ እግዚአብሔር፡ በጠፈረ ሰማይ፡ ከመ ያብርሁ ዲበ ምድር። ወይኲንንዎሙ፡ ለዕለት፥ ወለሌሊት፡ ወይፍልጡ፡ ማእከለ ዕለት፥ ወማእከለ ሌሊት፤ ወርእየ እግዚአብሔር ከመ ሠናይ። ወኮነ ሌሊተ፥ ወጸብሐ፤ ወኮነ አርባዕተ ዕለተ።"

ማለትም፡ "እግዚአብሔር፡ ኹለቱን ታላላቅ ብርሃናት ፈጥሮ፡ ከፍተኛው ብርሃን፡ ቀኑን እንዲያበራ፥ ታናሹ ብርሃንም፡ ከከዋክብት ጋር፡ ሌሊቱን እንዲያበራ አደረገ። እግዚአብሔር፡ በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ፥ መዓልትንና ሌሊትን ያበሩ ዘንድ፥ መዓልቱንና ሌሊቱንም ይለዩ ዘንድ፡ በሰማይ ጠፈር አኖራቸው። እግዚአብሔር፡ መልካም እንደኾነ አየ። መሸም፤ ጠባም፤ አራት ቀን ኾነ።" በሚለው ይረጋገጣል። (ዘፍጥ. ፩፥ ፲፬-፲፱።)

"የእግዚአብሔር ቀን" ከፍጡራኑ ቀን ይልቅ፡ የቱን ያህል፡ እጅግ የረዘመ መኾኑን፡ "እስመ ዐሠርቱ ምእት ዓመት፡ በቅድሜከ፡ ከመ ዕለት፡ እንተ ትማልም ኀለፈት።" ማለትም፡ "ሺህ ዓመት፡ በፊትህ እንዳለፈች፡ እንደትናንት ቀን ናት!" የሚለው፡ የመጽሐፍ ቃል ያመላክታል። (መዝ. ፹፱፥ ፬። ፪ጴጥ. ፫፥ ፰።)

ኹሉም፡ ማለትም፡ የሥነ ፍጥረት እውነታ እንደሚያረጋግጠውና በዚያ ላይ የተመሠረተው ኢትዮጵያዊው እምነት እንዳወጀው፡ ከላይ ከተጠቀሰው መለኮታዊ ቃል የተነሣ፡ ብርሃንን ብቻ ሳይኾን፡ የብርሃን አለመኖር የሚያስከትለውን፡ "ጨለማ"ን፥ እንዲሁም፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ እዚህ ላይ፡ "ነፋስ" ብለው የተረጐሙትን፡ የሰይጣን "መንፈስ"ን ጭምር የፈጠረና የፈጣሪነት ብቸኛ ባሕርያዊ ሥልጣን የተሰጠው፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑ እሙን ነው።

የእግዚአብሔር የኾነችው፡ የሥነ ፍጥረት እውነት የምታረጋግጠው ሌላ ገጽታ ቢኖር፡ መናፍስት ኹሉ፡ ቅዱሳን መላእክትና "ሰይጣን" ጭምር፡ የእግዚአብሔር ፍጡራን መኾናቸው ነው።

እንዲህም ሲባል፡ መናፍስትን የፈጠረ፡ እርሱ፡ "መንፈስ ቅዱስ"፡ ራሱን፡ ወደርኩስ መንፈስነት፥ ወይም፡ ወደክፉ መንፈስነት እንደለወጠው፡ እንደሰይጣን፡ "ፍጡር ነው!" ማለት እንዳልኾነ፥ ወይም፡ በዚህ አንጻር፡ ራሱ፡ ፈጣሪ እንደኾነው፡ እንደመንፈስ ቅዱስ፡ ይኸው ሰይጣንም፡ "ያልተፈጠረ ነው!" በማለት፡ ይህንኑ፡ ፍጡሩን ርኩስ መንፈስ፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ማስተካከል እንዳልኾነ፡ በጥንቃቄ ሊያጤኑት ይገባል። ደግሞም፡ እንደጨለማውና እንደውኃው፡ የተፈጠረው ነፋስ፡ ሰፍኖበት በነበረው፡ በጨለማው ኾነ በውኃው ላይ የሰፈፈው መንፈስ፡ ያልተፈጠረው፡ መንፈስ ቅዱስ መኾኑን ማስተዋል ያስፈልጋል።

እዚህ ላይ፡ አበክረው ሊያውቁትና ሊያጤኑት የሚገባ፡ ጽኑ የእግዚአብሔር እውነታ አለ፤ ይኸውም፡ መናፍስትን፡ ("ሰይጣን" የተባለውን፡ ርኩስ መንፈስን ጨምሮ)፥ ነፍስንና ሥጋን፥ ሌላውንም፡ የማይታየውን፡ ረቂቁንና የሚታየውን፡ ግዙፉን ፍጥረት ኹሉ የፈጠረው፡ ራሱ፡ መንፈስና ፈጣሪ የኾነው፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ እርሱ፡ ከፈጠረው፡ ከመላእክት መንፈስ የተለየ መኾኑ ነው።

<u>ስለዚህ፡ "መንፈስ" የሚለው ቃል፡ አንድ ኾኖ፡ ፈጣሪ የኾነ መንፈስና እርሱ የፈጠረው መንፈስ መኖሩን መገንዘብ ይገባል።</u>

ምናልባት፡ ለዚህ መጽሐፍ፡ የተዛባ አስተሳሰብ፡ መንሥዔና ምክንያት የኾነው፡ ይኸው፡ በመንፈስ በኩል ያለው እውቀት፡ በዓይነቱና በይዘቱ፡ ከመሠረቱ ትክክል ባለመኾኑ ይመስላልና፡ ይህን ነገር ማስተዋሉ ይጠቅማል።

ለዚህም፡ *"ክፉ እንደመልካም ሁ[ኹ]ሉ ማደሪያውም ሆ[ኾ]ነ መፍለቂያው ያው መንፈስ እስከሆ[ኾ]ነ ድረስ አለመፈጠሩ ከሚታመንለት መንፈስ ተለይቶ የተፈጠረ ነው ሊባል አይችልም። አለበለዚያ ግን፡ የክፉ ሀ[ሐ]ሳብ መፍለቂያው እርኩስ መንፈስ መሆ[ኾ]ኑ እየታመነ ያ መንፈስ የተፈጠረ ነው ከተባለ የአምላክንም መንፈስ አለመፈጠር በእርግጠኛነት መናገር ይቸግራል።"* የሚለው አስተሳሰብ፡ በቂ ማስረጃ ነው።

*ታዲያ! እንዲህ ከኾነ፥ ማለትም፡ ራሱ፡ መንፈስ በመኾኑ፡ "እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ" የተባለው ፈጣሪ፡ እንደመላእክት፥ ወይም፡ እንደሰይጣን መንፈስ፡" የተፈጠረ ነው!" ከተባለ፡ የመንፈስም ኾነ የሥጋ፥ የመልካምም ኾነ የክፉው ፈጣሪ ማን ሊኾን ነው? እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን በፈጣሪነቱ ለማቆየት ደግሞ፡ ፍጡሩ የኾነውን ርኩስ መንፈስን፡ ማለትም ሰይጣንን፡ ወደፈጣሪነት ደረጃ ከፍ ማድረግ ግድ ኾነ። ይህ አስተሳሰብ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ እምነታችንን፡ ፈጽሞ የሚቃረን በመኾኑ፡ ተቀባይነት የለውም።*

*ራሱ፡ መልካም መንፈስ የኾነውና ኹሉን፡ በመልካምና ለመልካም የፈጠረው፥ እኛ፡ "እግዚአብሔር" ብለን የምንጠራው ፈጣሪ፡ በመልኩ ለፈጠረው ሰው፡ ለኑሮው ይበጀው ዘንድ፡ የሰጠው፡ ቋሚ መመሪያ ሥርዓት እንደነበረ ይታወቃል፤ ይህም፡ በአንድ ወገን፡ አሉታውያን የኾኑትን፡ "እንዳትሞት!" ማለትም፡* **"የያዝኸውን፡ መልካሙን፡ የእግዚአብሔርን ሕይወት እንዳታጣ፡ መልካሙንና ክፉውን ከሚያስታውቀው፡ ከዕፀ-በለስ ፍሬን አትብላ!" የሚለውን ብቻ ሳይኾን፡ "ከእኔ በቀር፡ ሌላ ባዕድ፡ አታምልክ!"፥ "የእግዚአብሔርን፡ የአምላክህን ስም፡ በከንቱ አትጥራ!"፥ "አትግደል!"፥ "አታመንዝር!"፥ "አትስረቅ!"፥ "በሓሰት አትመስክር!" እና "አትመኝ!" የሚሉትን፣ በሌላው ወገን ደግሞ፡ አዎንታውያን የኾኑትን፡ "ፈጣሪህ አምላክህ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር ነኝና፡ እኔን ብቻ አምልክ!"፥ "ሰንበትን ቀድስ!"፥ "አባትና እናትህንም አክብር!" የሚሉትን መመሪያዎች አጠቃልሎ የያዘ ሥርዓት ነው። (ዘጸአ. ፳፥ ፩-፲፯።)**

*ታዲያ! ይህን ሥርዓት የሠራና መመሪያውን የሰጠ፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ "እነዚህን፡ በአዎንታዊም ኾነ፡ በአሉታዊ መልክ የተሰጡትን የሥርዓት ክፍሎች፡ አልፈጠራቸውም፤ አያውቃቸውም!" ማለት ነውን? አይደለም፤ ኹሉን የፈጠረ እርሱ፡ እነዚህንም ፈጥሮአቸዋል፤ ያውቃቸዋልም።*

በአዎንታዊዉና በአሉታዊዉ ወገን የተፈረጁት፡ ኹለቱም ወገኖች፡ በመደረግም ኾነ፡ ባለመደረግ፡ ያ፡ መለኮታዊ የተፈጥሮ ሥርዓታቸው እስከተጠበቀና እስከተከበረ ድረስ፡ ኹሉም፡ በመልካምነት ገጻ ባሕርያቸው፡ የእግዚአብሔር ኾነው፡ ህልውናቸው ይቀጥላል እንጂ፡ በሌላ መልክ ታይተው፡ ከእግዚአብሔራዊው መልካምነታቸው ውጪ የሚኾኑበት ምክንያትና ኹኔታ፥ ጊዜና ሥፍራም ከቶ የለም።

በዚህ አንጻር፡ እነዚህ ኹለቱም የሥርዓቱ ወገኖች፡ ተጠብቀው መከበራቸው ቀርቶ፡ በመተላለፍ በሚፈርሱበት ጊዜ ግን፡ ጥፋት ይኾኑና፡ በክፋትነት ይፈረጃሉ። ይህም ማለት፡ እግዚአብሔር፡ የእርሱን እውቀት አቀዳጅቶ የፈጠራቸው፡ ሕያዋን ፍጡራኑ፡ "አድርጉ!" እና/ወይም፡ "አታድርጉ!" ብሎ፡ ስለህልውናቸው መልካም አጠባበቅ የሰጣቸውን መመሪያ ተላልፈው፡ ሥርዓቱን ሲያፈርሱ፡ በዚያን ጊዜ፡ በአዎንታዊነት ኾነ፡ በአሉታዊነት የተፈረጁት፡ እነዚያ፡ የሥርዓቱ ተአቅቦዎች እና/ወይም ድርጊቶች፡ በጋራም ኾነ፡ በተናጠል፥ በከፊልም ኾነ፡ በአጠቃላይ፡ ከእግዚአብሔራዊው መልካምነት ብቅዓት ወጥተው፡ ወደክፉነት የሚዳረጉ ይኾናሉ።

በዚሁ ሥርዓት መሠረት፡ በአንድ ወገን፡ "አታድርግ!" የሚለውን ክልከላ ባለመከተል፡ "እምቢ!" ብሎ፡ አሉታዊዉን ክፍል መፈጸም፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ "አድርግ!" የሚለውን፡ የፈቃድ ነጻነት በመቀበል፡ አዎንታዊዉን ክፍል አለመፈጸም፡ ክፉ አድራጊና የክፋት ተባባሪ መኾንን እንደሚያስከትል እሙን ነው።

ይህ እውነታ የሚከሥትልን፡ ሌላ ገጽታ አለ፤ ይህም፡ እንዲህ በሚል ቃል ሊገለጽ ይቻላል፡- መቸም፡ ለመንፈሳውያኑ መላእክትም ኾነ ለሥጋውያኑ ሰዎች፡ ከፈጣሪ፡ በተፈጥሮ የተሰጣቸው፡ መልካሙንና ክፉውን ለይቶ የማወቂያ ችሎታና ከኹለት፡ አንዱን የመምረጫ ነጻነት፥ እንዲሁም፡ ያን ምርጫቸውን ለማጽናት የመወሰን ሥልጣንና የመተግበር ኃይል እንዳላቸው ይታወቃል፤ ይህም፡ "በዚያ፡ በተቀዳጁት ታላቅ ጸጋ ተጠቅመው፡ የዚህኑ ሥርዓት፡ አዎንታዊዉንም ኾነ አሉታዊዉን ወገን፡ እንደፈለጉ ለመፈጸም ብቅዓት አላቸው!" ማለት ነው።

ታዲያ! እንዲህ ከኾነ፡ አዳምና ሔዋን፡ "አትብሉ!" ብሎ፡ ፈጣሪያቸው የሰጣቸውን መመሪያ ተቃርነውና አፍርሰው፡ እንደበሉ ኹሉ፡ እንዲሁ፡ "እኔን ብቻ አምልክ! ሰንበትን ቀድስ! አባትህንና እናትህን አክብር!" በሚለው፡ በአዎንታዊው መመሪያ አንጻር፡ "እምቢ! ሌላ ጣዖትን አመልካለሁ! ሰንበትን እሽራለሁ! ወላጆቼንም አዋርዳለሁ!" እንዲሁም፡ "ሌላ አምላክ አይኑርህ! የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ! በሐሰት አትመስክር! አትግደል! አታመንዝር! አትስረቅ፥ አትመኝ!" በሚለው በአሉታዊው መመሪያ አንጻር ደግሞ፡ "የለም! ጣዖትን አምልክ! እንዲያውም፡ ፈጣሪህን ስደብ! ተቃወመው! ዋሽ! ግደል! አመንዝር! ሥረቅ! መመኘት ብቻ ሳይኾን፡ በምቀኝነትና በቅናት ተነሣሥተህ፡ የተፈጥሮ ባልደረባህን አጥፋ!" የሚለው፡ የተቃውሞና የአፍራሽነት አስተሳሰብ፡ በእነዚህ መንፈሳውያንና ሥጋውያን ሕያዋን ፍጡሮች ዘንድ፡ ከየትና እንዴት ተሠረፀ፡ ብቅ አለ? ተገኘ?

በጥንተ ተፈጥሮ ባሕርያቸው ውስጥ ቢኖር አይደለምን? ይህስ የተፈጥሮ ባሕርይ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ እስከዛሬ፥ ዛሬም፡ በእያንዳንዱ፡ መንፈሳዊና መልአካዊ፥ ነፍሳዊና ሥጋዊ ህልውና ውስጥ ሕያው ኾኖ በሚኖረው ፍጡር ዘንድ ሲሠራ የኖረ፥ ዛሬም እየሠራ ያለ አይደለምን? የዚህስ የተፈጥሮ ባሕርይ ሠሪና ባለቤት ማን ነው? ራሱ፡ "እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ" የምንለው፡ አንድ ፈጣሪ፥ አንድ አምላክ አይደለምን? አዎን! ነው።

እርሱ እግዚአብሔርስ፡ በእያንዳንዱ፡ መልአካዊና ሰብአዊ ፍጡር ጥልቅ ህልውና ውስጥ፡ "ኅሊና" በተባለው ባሕርይ ተገልጾ፡ "የመለኮታዊዉን መመሪያ፡ አዎንታዊዉንም ኾነ አሉታዊዉን ወገን፡ ለያይቶና አጉልቶ በመግለጽ፡ ወቀሳውንና ዳኝነቱን፡ ያለማቋርጥ እየሰጠ አይደለምን? አዎን! እየሰጠ ነው።

ለምሳሌ፡ "ሌላ አምላክ አታምልክ!"፥ ወይም፡ "አትግደል!" በሚለው አሉታዊ መመሪያ አንጻር፡ "ጣዖትን አምልክ!"፥ ወይም፡ "ግደል!" የሚለው፡ ተቃራኒ አስተሳሰብ፡ በሚሠርፅበት ጊዜ፡ "የለም! በአሉታዊ ገጽታ የተሰጠህን፡ የፈጣሪህን መልካም መመሪያ ተላልፈህ፡ ይህን፥ ወይም፡ ያን ክፉ ነገር፡ ማድረግ የለብህም!" በሚለው የኅሊና ወቀሳና ዳኝነት፡ ራሱ እግዚአብሔር መናገሩ አይደለምን? መልሱ፡ "አዎን!" ነው።

ከዚህ በተለየ መልኩና ይዞታው ደግሞ፡ "ሰንበትን ቀድስ!" ወይም፡ "አባትና እናትህን አክብር!" በሚለው፡ አዎንታዊ መመሪያ አንጻር፡ "የለም! አትቀድስ!"፥ ወይም፡ "አታክብር!" የሚለው፡ ተቃራኒ አስተሳሰብ፡ በሚሠርፅበት ጊዜ፡ "አይ! በአዎንታዊ ገጽታ የተሰጠህን፡ የፈጣሪህን መልካም መመሪያ ተላልፈህ፡ ይህን፥ ወይም፡ ያን ክፉ ነገር፡ ማድረግ የለብህም!" በሚለው የኅሊና ወቀሳና ዳኝነት፡ አኹንም እንደገና፡ ራሱ እግዚአብሔር መናገሩ አይደለምን? አኹንም፡ መልሱ፡ "አዎን!" ነው።

ታዲያ! የመልካምና የክፋት ስሜት፥ እውቀቱም፡ ከማስተዋያውና ከመመዘኛው "ኅሊና" ጋር፥ እንዲሁም፡ ከምርጫ ነጻነቱ፥ ከመወሰኑ ሥልጣንና ከማድረጉ ችሎታም ጋር፡ እንዲህ፡ በእያንዳንዱ፡ መንፈሳዊ ፍጡር ከኾነው፡ መልአክና ሥጋዊ ፍጡር ከኾነው ሰው ጋር፡ በተፈጥሮ ባሕርይነት፡ ዐብሮና ተዋሕዶ የተሠራ ከኾነ፡ እነዚህና የእነዚህ ኹሉ ነገሮች፡ ማኅደራት የኾኑት አካላትና ባሕርያት ጭምር፡ ኹሉም፡ የፈጣሪ ፍጡራን መኾናቸው አይደለምን? አዎን! ነው።

እንግዲህ፡ እግዚአብሔርን፡ "እግዚአብሔርና ፈጣሪ" ያሰኘው፡ ይኸው እንደመኾኑ መጠን፡ መላእክትንና ሰዎችንም፡ እግዚአብሔርን ከመምሰል ብቅዓት የሚያደርሳቸውና ይህን ፍጹም ጸጋ የሚያቀዳጃቸው፡ በዚህ ሥርዓት መመሪያ መሠረት፡ መልካሙንና ክፉውን ለይተው ካወቁ በኋላ፡ ክፉውን ትተውት፡ መልካሙን በመምረጥ ሲከተሉትና ሲፈጽሙት ነው።

በዚህም አንጻር ደግሞ፡ መልካሙን ትተው፡ ክፉውን በመምረጥ ሲከተሉትና ሲፈጽሙት፡ ከመልካሙ የእግዚአብሔር ሕይወት ውጭ የመኾንን፡ "ሞት" የተባለውን ጽዋ፡ በፈቃዳቸው መቀበላቸው ስለሚኾን፡ ፍጻሜያቸው፡ "ሰይጣን" የመባልን፡ የፀረ-መልካም፥ ወይም፡ የፀረ-አምላክ ፍጹም ውርደትን ተሸክሞ፡ ወደጥልቁ ተጥሎ መሠቃየት ይኾናል።

እንዲህ ከኾነ፡ መንፈሳዊ አካል ያለው ኾኖ፡ ለእግዚአብሔር መልአክነት፡ በቅድሚያ በተፈጠረው፡ "ሳጥናኤል" በተባለው ፍጡርና የእግዚአብሔር መልክ በኾነችው ነፍስነት፡ ሥጋ ለባሽ ኾኖ፡ በኋላ በተፈጠረው፡ "አዳም" በተባለው ፍጡር፡ የእግዚአብሔሩን ሥርዓት ተላልፎ የማፍረሱ፡ ይህ ድርጊት፡ እንደአፈጣጠራቸው ቅደም ተከተል ተራ፡ በኹለቱም ፍጡራን ዘንድ፡ በእርግጥ ተፈጽሞ ስለተገኘ፡ ጥፋት ኾነ። ይህም ጥፋት፡ "ክፋት" ተባለ።

ስለዚህ፡ "ክፋት"፡ ከዚሁ ስያሜው ጋር፡ በቀዳማዊው መንፈሳዊ ፍጡር፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ተከሠተ! አጥፊውም፡ "ሰይጣን" ተባለ። ይኸው ጥፋት፡ በተከታይነት፡ በደኃራዊው ሥጋዊ ፍጡርም ተደገመ! እርሱም፡ "ሟች!" ኾነ።

<u>ከዚህ በላይ የተገለጸው የእግዚአብሔር እውነታ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ ክፉነት፥ ወይም፡ "ክፉ" የሚባል ነገር እንዳልተፈጠረ ያረጋገጣል።</u>

ዳሩ ግን፡ ይህን እውነታ ክዶ፥ ወይም፡ ሽሮ፡ የእግዚአብሔርን መልካም ሥርዓት፡ በድፍረት የሚተላለፍና የሚያፈርስ፥ ከዚህ የተነሣም፡ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ተቃዋሚ የሚኾን ኹሉ፡ ከፈጣሪ ጋር ተስተካክሎ፡ የፈጣሪነትን ብቅዓት "ማግኘት ይገባዋል!" የሚል ሕያው ፍጡር ካለ፡ እርሱ፡ ራሱ፡ ሰይጣን መኾኑ አይደለምን? ሳጥናኤልስ ራሱ፡ በድፍረቱና በትዕቢቱ፡ ስለራሱ፡ ለራሱ ያለውና ያደረገው ይህንኑ አልነበረምን? ነውኮ!

"ሕያው ነፍስ ያለው ፍጡር ኹሉ፥ መናፍስት ጭምር፥ ያም፡ ቅዱሳን መላእክትንና ርኩሳን መናፍስትን፥ ሰውንም ሳይቀር የሚያጠቃልለው የሥነ ፍጥረት አካላዊና ባሕርያዊ ህልውና፡ ከፈጣሪው በተለገሠው የነጻነትና የሥልጣን ጸጋ፡ የምርጫ ውሳኔውን አድርጎ፡ ራሱን ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት ሊያበቃና ፈጣሪውን ሊመስል፥ አለዚያ ደግሞ፡ ራሱን፡ ለርኩስ መንፈስ መሥፈሪያነት በመዳረግ፡ ሰይጣንን ሊኾን እንደሚችል፡ በእግዚአብሔር ቃል ተነግሯል፤ ደርሰው በታዩና በተፈጸሙ፡ የመለኮትና የፍጡራን ሥራዎችም ተመስክሯል።

ነገር ግን፡ እንዲህ ስለተባለ ብቻ፡ በዚህ ***"የዕፀ-በለስ ምሥጢር"*** መጽሓፍ ውስጥ እንደተሠነዘረው፡ "የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ባሕርይ የኾነው፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ ወደፍጡርነት ተዋርዶ፡ ዝቅ ሊል፥ ፍጡራን ደግሞ፡ ይልቁንም፡ ሰይጣን፡ በመንፈሳዊ ተፈጥሮው፡ ወደፈጣሪነት ደረጃ ልቀውና ደርሰው፡ ፈጣሪ ሊኾኑ ይችላሉ!" ማለት አለመኾኑ ተረጋግጦ ሊታወቅ ይገባል።

ስለዚህ፡ *"የአምላክ መልካም መንፈስና የሰይጣን ክፉ መንፈስ፡ ከጥንት አብረው የነበሩ እና ያልተፈጠሩ ስለመኾናቸው፡ ተጨማሪ መረጃ አድርገን፡ ዕፀ-በለስን ማየት እንችላለን!"* የሚለውና ይህን የመሰሉት፡ በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት አስተሳሰቦች፡ ከዚህ በላይ በተሰጠው ሓተታ፡ ውድቅ ሊኾኑ፥ ወይም፡ ሊስተካከሉ ይገባቸዋል።

እግዚአብሔር ጨለማንና ብርሃንን፥ ሌሎችንም፡ የማይመሳሰሉ የሥነ ፍጥረት አካላትንና ባሕርያትን የፈጠረው፡ እርስ በርሳቸው ተጣማጅ በመኾን፡ ለሕይወት መልካም ህልውና መቀጠል ያላቸውን፡ ገንቢ የኾነ ጠቃሚና አስፈላጊ አስተዋጽዖን እንዲያበረክቱ እንጂ፡ አንዱ የሌላው ተቃዋሚና ተቃራኒ ኾኖ፡ አንዱ ሌላውን እንዲፃረረውና እንዲያፈርሰው አለመኾኑ፡ በዚህ ረገድ፡ ያልተቋረጠው፡ የእነዚሁ፡ የሥነ ፍጥረት አካላትና ባሕርያት፡ የየአፍታው ፍሬያቸው፡ ለማንኛውም ሕያው ተንቀሳቃሽ ፍጡር፡ ዘወትር፡ በዓይን የሚታይና በጆሮ የሚሰማ፥ በአካል የሚዳሰስና በሕዋሳት የሚታወቅ በቂ ማስረጃ ነው።

ለዚህም፡ ፈጣሪና ፍጡር፥ ቀዳማዊና ደኃራዊ፥ ረቂቅና ግዙፍ፥ መንፈስና ሥጋ፥ መልአክና ሰው፥ ወንድና ሴት፥ ሰማይና ምድር፥ ነፋስና አፈር፥ እሳትና ውኃ፥ ጨለማና ብርሃን፥ ሌሊትና ቀን፥ ክረምትና በጋ፥ ደግነትና ክፋት፥ እነዚህን ከመሳሰሉት፡ በተቃራኒ አካላትና ገጸ ባሕርያት ከተፈጠሩት፡ ሥፍር ቍጥር ከሌላቸው፡ ከሌሎቹ የሥነ ፍጥረት ብርቅ ጥንዶች መካከል፡ የዕፀ በለስን፡ የመጀመሪያዎቹንና የመጨረሻዎቹን ፍሬዎች፥ ከእነርሱም በኋላ፡ በሥጋና በመንፈስ የተከተሉትን፥ ዛሬ ያሉትንና ወደፊት የሚነሡትን፡ እልፍ አእላፋት የኾኑትን መሰሎቻቸውን ሕያዋን ፍጡራን፡ በበቂ ማስረጃነት ማቅረብ ይቻላል።

ይኸውም፡ የወንድና የሴት፡ በጾታ ተፈጥሮ፡ እንደጨለማና ብርሃን፡ ፈጽሞ ልዩ መኾን፡ የባልና ሚስትን፡ በጋብቻ ህልውና፡ አንድ መኾንንና ከዚያም፡ ሰውን ያህል መሰል ፍጡርን ሊያፈራ የቻለ መልካም ስምምነትን ያስገኘ፡ አዎንታዊ ጸጋና በረከት እንጂ፡ ከዚህ ትርጉም ውጪ፡ ሌላ፡ አሉታዊ የኾነ፡ የተፃራሪነትና የተቃራኒነት ገጽታ ሊሰጠው የሚገባ አይደለም።

ስለዚህ፡ ጨለማና ብርሃን፡ በዚሁ መልክ፡ በመንፈስ ቅዱስና በርኩስ መንፈስ መካከል ለተፈጠረው፡ እስከጠላትነት ለደረሰው ተቃራኒነት፡ በመሠረቱ፡ ምክንያትም፣ ማስረጃም፥ ምሳሌም ኾነው ሊቀርቡ አይገባም። ቀድሞ፡ መንፈሳዊው ፍጡር ሰይጣን፣ ኋላም፡ ሥጋዊው ፍጡር አዳም፡ ኹለቱም፥ ከዚህ የተነሣም፡ ዘሮቻቸው፡ በግል ደረጃ ሳይቀር፡ ከፈጣሪያቸው በተፈጥሮ ባገኙት፡ መልካሙንና ክፉዉን ለይተው በማወቅ ችሎታቸው፥ ከዚያም፡ ከኹለት አንዱን መርጠው በመወሰን ሥልጣናቸውና ያን ውሳኔያቸውንም በሥራ ላይ በማዋል ኃይላቸው ተጠቅመው፡ ***"ክፋትን"***፡ በየራሳቸው ፍላጎትና ምርጫ፥ ውሳኔና ድርጊት አመጡት።

ይህም፡ የየራሳቸው ተፈጥሮአዊ ግብር፥ ወይም፡ ድርጊት እንጂ፡ ፍጡሩ ሰይጣን፥ ወይም፡ ፍጡሩ ሰው፡ መለኮታዊ የፈጣሪነት ባሕርይና ህልውና እንዳለው ተቆጥሮ፡ ያ የክፋት ተፈጥሮአዊ መንፈስ፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ ሕይወት ከኾነው፡ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋር፡ በማናቸውም መሥፈሪያና መመዘኛ፡ "ሊስተካከል፥ ወይም፡ ሊወዳደር እንዲችል የሚያደርግ ብቅዓት ይኾናል!" ብሎ መገመት ከቶ አይገባም።

## የሰይጣን ማንነት፡ በመለኮት ፍቅር ተጋልጧል!

ሰይጣን፡ ጥንቱኑም ቢኾን፡ በዚህ ፍጡራዊ መልኩና ይዞቱ፡ ከላይና ቀደም ብሎም፡ ተደጋግሞ እንደተመለከተው፡ በራሱ የተፈጥሮ የእውቀት ችሎታ፥ የምርጫ ዓቅም፥ የመወሰን ሥልጣንና የማድረግ ኃይል በመጠቀም፡ ራሱ ክህደት፥ የክህደትም አባት፥ ጠንሳሽና ጀማሪ፥ አራማጅና አስፈጻሚ እንደመኾኑ መጠን፡ ራሱ፡ ክፋት፥ የክፋት አባት፥ ጠንሳሽና ጀማሪ፥ አራማጅና አስፈጻሚ መኾኑ የሚታበል አይደለም።

ይህ እውነታ፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የምሥራች ቃል ተብራርቶና ተረጋግጦ ተነግሯል፤ ይኸውም፡ "ወአንትሙሂ ዘርኢክሙ በኀበ አቡክሙ ትገብሩ፤ ...አንትሙሰ፡ ትገብሩ ግብረ አበዊክሙ፤" ማለትም፡ "እናንተ፡ በአባታችሁ ያያችሁትን ታደርጋላችሁ፤ ...እናንተ፡ የአባታችሁን ሥራ ትሠራላችሁ፤" ባላቸው ጊዜ፡ "ለነሰ፡ አብርሃም አቡነ!" ማለትም፡ "የእኛስ አባታችን፡ አብርሃም ነው!" ከዚህም አልፈው ተርፈው ይባስ፡ "አሐዱ አብ ብነ፤ ወውእቱ እግዚአብሔር!" ማለትም፡ "አንድ አባት አለን፤ እርሱም፡ እግዚአብሔር ነው!" ላሉት አይሁድ፡ የሰጣቸው፡ ቍርጥ መልስ ነው።

ያም እንዲህ የሚል ነው፡- "ሶበሰ ውሉደ አብርሃም አንትሙ፡ ግብረ አብርሃም እምገበርክሙ፤ ወይእዜሰ፡ ተኀሥሡ ትቅትሉኒ፡ ብእሴ ጻድቀ፡ ዘጽድቀ እነግረክሙ፡ ዘሰማዕኩ በኀበ እግዚአብሔር፤ ወአብርሃምሰ ኢገብረ ከመዝ። ...ሶበሰ እግዚአብሔር አቡክሙ፡ እምአፍቀርክሙኒ ኪያየ፤ ወቃልየኒ፡ እምአቀብክሙ፡ እስመ አነ፡ እምኀበ እግዚአብሔር ወጻእኩ፤ ወመጻእኩ። ...አንትሙሰ፡ እምአቡክሙ ሰይጣን አንትሙ፤ ወፍትወቶ ለአቡክሙ፡ ትፈቅዱ ትግበሩ። ወውእቱሰ፡ ቀታሌ ነፍሰ ሰብእ ውእቱ እምትካት፤ ወኢይቀውምበጽድቅ፤ እስመ አልቦ ጽድቅ በኀቤሁ። ወሶበሂ ይነብብ ሐሰተ፡ እምዚአሁ ይነብብ፤ እስመ ሐሳዊ ውእቱ፤ ወአቡሃ ለሐሰት። ወአንሰ፡ እስመ ጽድቀ እነግር፡ ወኢተአምኑኒ።"

ማለትም፡ "የአብርሃም ልጆች ብትኾኑስ፡ የአብርሃምን ሥራ በሠራችሁ ነበር፤ አኹንም፡ በእግዚአብሔር ዘንድ የሰማሁትን እውነት የምነግራችሁን ሰው፡ ልትገድሉኝ ትሻላችሁ፤ አብርሃምስ፡ እንዲህ አላደረገም። ...እግዚአብሔር፡ አባታችሁ ቢኾንስ፡ እኔን በወደዳችሁኝ ነበር፤ ቃሌንም በጠበቃችሁ ነበር፤ እኔ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጥቼ መጥቻለሁና። ...እናንተስ፡ ከአባታችሁ ከሰይጣን ናችሁ፤ የአባታችሁን ፈቃድ ልታደርጉ ትወድዳላችሁ። እርሱ፡ ከጥንት ጀምሮ፡ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ በእውነትም አይቆምም፤ በእርሱ ዘንድ፡ እውነት የለምና፤ ሐሰትንም በሚናገርበት ጊዜ፡ ከራሱ አንቅቶ ይናገራል፤ ሐሰተኛ ነውና፤ የሐሰትም አባት ነውና። እኔ ግን፡ እውነትን እናገራለሁና አታምኑኝም።" (ዮሐ. ፰፥ ፴፩-፵፯።)

"የእግዚአብሔር ልጆች" የተባሉት፡ የኢትዮጵያ ልጆች፥ እንደእነርሱም፡ ከመላእክትም ኾነ ከሰዎች መካከል፡ እውነተኞች (ጻድቃን) ኾነው በመገኘታቸው፡ ለዚህ ስያሜ የበቁ ፍጡራን ኹሉ፡ በእርሱ፡ በፈጣሪያቸው፡ በእግዚአብሔር ማመንና መተማመን ብቻ ሳይኾን፡ ስለእርሱ እውነትና መንግሥት፡ ማናቸውንም አስፈላጊና ተገቢ መሥዋዕትነት በመክፈል፡ ከሰይጣንና ከቀሩት የክፋት ኃይላት ጋር እስከመጨረሻው የሞት ጽዋቸው ድረስ ተጋድለው፡ በሰማዕትነት የሚያልፉት ታዲያ! ለምንድር ነው? ስለእርሱ፡ ስለእግዚአብሔር፡ ፍጹም ፍቅር ስላደረባቸው አይደለምን? አዎን! ነው።

ይህን የመሰለው ፍቅርስ፡ በእነርሱ ላይ፡ ለምንና እንዴት ሊያድርባቸው ቻለ? እርሱ፡ እግዚአብሔር፡ ለእነርሱና ለመላው ፍጥረቱ ያለውን ፍጹም ፍቅሩን፥ በዚህም ፍቅሩ፡ በግብር ፈጽሞ ያሳየውን እውን ሥራ አረጋግጠው ስላወቁ አይደለምን? አዎን! ነው። እንግዲያማ፡ እውነታው ይህ ከኾነ፡ እስኪ፡ በመጠኑም ቢኾን፡ ከዚህ የሚከተሉትን ቍም ነገሮች፡ በማስተዋል እንመልከታቸው!

ፈጣሬ ፍጥረታትና ገባሬ ዓለማት እግዚአብሔር አምላክ፡ ጥንቱኑም፡ በአርአያውና በመልኩ መፍጠር ሳይበቃው፡ ከላይ በተገለጸው ምክንያትና ኹኔታ፡ ሌላ የቀረ ማማረጫ ስላልነበረው፡ በፈጣሪነቱ፡ ካለመኖር ወደመኖር ያመጣው የራሱ ፍጡር የበደለው ሲኾን፡ በመጨረሻ፡ ይህንኑ የበደለውን የፍጥረት ወገን ለማዳን ሲል፥ አዎን! ለፍጥረቱ ኹሉ፡ የዘለዓለም ደኅንነትና ደስታ፥ ሰላምና መልካም ሕይወት ሲል፡ ራሱን፡ ከፈጣሪነት ክብሩ አዋርዶ፡ እንደሰው ሳይኾን፡ እንደከብት በበረት ተወልዶና እንደመናጢ ደኃ፡ በፍጹም ምስኪንነት ኖረ!

የሚሰማ ጆሮ ያለው ኾኖ ለሰማው፡ ለፍጥረቱ ኹሉ፡ መለኮታዊ እውቀቱን ካስተማረና የበጎ አድራጎት አገልግሎቱን ካበረከተ በኋላም፡ በሰልፉ ፍጻሜ፡ እንዲያ፡ በድል አድራጊነት፡ ከሙታን ተለይቶ ሊነሣ፡ ለቀድሞ አገልጋዩና ለኋለኛ ከሃዲው፥ ለቀንደኛ ተቃዋሚውና ለክፉው ፍጡሩ፡ ለሰይጣን፡ ራሱን ዝቅ አድርጎ፡ ለእርሱ በመታዘዝ፡ በቅድሚያ፡ ከዚሁ፡ ከሰይጣን የቀረበለትን የፈተናና የመከራ፥ ሌላውንም የመስቀል መራራ ጽዋ በትዕግሥት ተቀበለ!

ዘለዓለማዊውና አማናዊው የፋሲካ በግ ኾኖም ታርዶ ሞተ! በፍጥረት ሕያው ዜና መዋዕል ውስጥ ወደር የሌለውን፡ ያን ኹሉ ገድል ያካኼደው፥ መሥዋዕትነትንም የከፈለው፡ ለምንድር ኖርዋል? ስለዚህ "ፍቅሩ" አይደለምን? አዎን! በእርግጥ ነው።

ኧረ ለመኾኑ፡ ጥንቱኑ፡ የኹሉ ፈጣሪና ባለቤት የኾነው እግዚአብሔር፡ አንድ አምላክ ሲኾን፡ "አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ" ተብሎ በአካል፥ በስምና በግብር ሦስትነት፡ ማለትም፡ በሥላሴነት የተገለጸው፥ የታወቀውና እየሠራ ያለው፡ ለምን ይመስለናል? ወይም፡ "ለምንድር ነው?" ብለን ነው ያመንነው? ለመላ ፍጥረቱ፥ ማለትም፡ ሰይጣንን ሳይቀር ለሚያጠቃልለው፡ ለመንፈሳዊዉ እና ሰውን ማዕከል ላደረገው፡ ለሥጋዊዉ ፍጥረተ ዓለም፡ ፍጹም መልካም ህልውናና ዘለዓለማዊ ደኅንነት መኾኑን፡ ለምንጊዜም ልንዘነጋው አይገባንም። ይህም፡ እግዚአብሔር፡ ለፍጥረቱ ያለው ፍቅር፡ የቱን ያህል የመጠቀና የጠለቀ "ፍጹም" መኾኑን አረጋግጦ ያስረዳናል።

ታዲያ! እግዚአብሔር አብ፡ ከዚህ ፍቅሩ የተነሣ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ይህን መሥዋዕትነት በመክፈሉ፡ በዚህ ቤዛነት ለተገኘው ዘለዓለማዊ ጸጋ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ የባሕርይ ሕይወቱ የኾነው፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ እንደሰይጣን፡ "ፍጡር" ነው ተብሎ፥ ወይም፡ "እንዳልተፈጠረም ተቆጥሮ" ከእርሱ፡ ከርኩስ መንፈስ ጋር እኩል ተወዳዳሪ፥ ተፎካካሪ፥ ተፃራሪ ኾኖ ሊነገርና ሊጻፍ ቀርቶ፡ ሊታሰብ፡ ከቶ ይገባ ነበርን? አይገባም ነበር።

ስለዚህ፡ በመጽሐፉ ገጽ ፲፰ (18): *"ብርሀ[ሃ]ንና ጨለማ የምንላቸው ነገሮች ከጥንት ከዘለዓለም ተቃራኒ በሆ[ኾ]ነ ስፍራና ባህ[ሕ]ሪ የጋራ በሆ[ኾ]ነ ህ[ሕ]ያውነት ላይ ለሰፈኑት የአምላክ መንፈስና የሰይጣን መንፈስ ማደሪያ ነበሩ ከማለት በቀር ምንም ማለት አንችልም።"* ደግሞም፡ *"የአምላክ መልካም መንፈስና የሰይጣን ክፉ መንፈስ፡ ከጥንት አብረው የነበሩ እና ያልተፈጠሩ ስለመኾናቸው ተጨማሪ መረጃ አድርገን፡ እ[ዕ]ፀ በለስን ማየት እንችላለን። ...እንዲሁም እንደሰው በራሱ ክፉ አሊያም መልካም የመኾን ነፃ[ጻ]ነት ተሰጥቶት የተፈጠረ መልአክ የለም።"* በሚል አገላለጽ፡ የተሰጠው ሓተታ፡ በተሳሳተ አስተሳሰብና አተረጓጎም ስልት ላይ የቆመ ስለኾነ፥ ቀደም ብሎም ተገቢው ትችትና ማብራሪያ ስለተሰጠበት፡ ተቀባይነት የለውም።

በዘወትሩ የኢትዮጵያ ልጆች ጸሎት፡ ልዑል እግዚአብሔር፡ "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፡ እግዚአብሔር ጸባዖት፥ ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ! ቅድሳተ ስብሓቲከ!" ማለትም፡ "'እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ' ተብሎ፡ በ፩ነትና በ፫ነት የሚመሰገን፡ ኹሉን የፈጠረ አምላክ፡ በሰማያትና በምድር፡ ፈጽሞ የመላ ነው።" እየተባለ ይመሰከርለታል።

እርሱ እግዚአብሔር፡ "ብርሃንንና ጨለማን" መፍጠር ብቻ ሳይኾን፡ እንዲህ፡ በምልዓትና ባለማቋረጥ የሚገኝባቸው በመኾኑ፡ በዚህና ከላይ በተዘረዘሩት ቍም ነገሮች ኹሉ ምክንያት፡ "ብርሃን" ብቻ፡ በመልካም ተፈርጆ፡ ለእግዚአብሔር፥ "ጨለማ" ግን፡ ለሰይጣን ሊታደል አይቻልም። ኹሉ፡ የእግዚአብሔር፥ መልካምም ናቸውና። (ኢሳ. ፷፥ ፩-፫።)

በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች እምነት ዘንድ፡ እግዚአብሔርን እኮ፡ እግዚአብሔር ያሰኘው፥ "ኹሉን በመልካምነት አከናውኖ የፈጠረ፥ ኹሉን በመልካም ለመልካም የያዘና የሚመራ፥ ኹሉን ማድረግ የሚቻለው፥ ነገር ግን፡ ማድረግ የሚሳነው፡ ምንም ነገር የሌለ" ተብሎም የሚመለከው፡ ኹሉን፡ ለይቶ አውቆ፥ ለፍጥረቱ፡ መልካሙን ብቻ የሚያደርግ በመኾኑ ነው።

በዚህም ብቻ አይደለም፤ ይህንኑ እውቀቱንና ችሎታውን፥ ሥልጣኑንና ኃይሉን፡ ለራሱ ብቻ ወስኖ ሳያስቀር፡ መልአክና ሰው ለተባሉት መንፈሳውያንና ሥጋውያን ፍጡሮቹ፡ ሳይጠየቅ የለገሠ በመኾኑም ጭምር ነው እንጂ። ከዚህም አልፎ፡ እኚህ ፍጡሮቹ፡ እንዲህ ኾነው ይገኙ ዘንድ፡ እየራሳቸውን ለዚያ ህልውና በሚያበቁበት ጊዜ፡ እርሱን ሊመስሉና የእርሱ ልጆች ሊኾኑ እንዲችሉ በማድረጉ ነው።

እንግዴህ፡ ከመጽሓፍህ መልእክት ጋር በተያያዘ መልኩና ይዘቱ፡ የዘፍጥረት ምዕራፍ አንድን ሓተታ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ እምነታችን መሠረትነት፡ እንዲህ በሚል ቃል አጠቃልለዋለሁ፡-

እግዚአብሔር፡ መጀመሪያ ከሌለው ጥንት አንሥቶ፡ ብቻውን፡ ቸር ፈጣሪና ደግ አምላክ ተብሎ፡ በአንድነትና በሦስትነት የሚመለክ ሲኾን፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ፡ በባሕርዩ ውስጥ፡ ህልዋን ኾነው በሚገኙበት፡ በእግዚአብሔር አብነቱ፡ የመንፈሳዊው፥ የነፍሳዊውና የሥጋዊው ፍጥረታት ኹሉ አስገኚና ሠሪ፥ ባለቤትና አሳላፊ ኾኖ ኖርዋል፤ አኹንም፡ እየኖረ ነው፤ ወደፊትም፡ ለዘለዓለም ይኖራል።

በመካከሉም፡ አብና መንፈስ ቅዱስ፡ በባሕርዩ ውስጥ፡ ህልዋን ኾነው በሚገኙበት፡ በእግዚአብሔር ወልድነቱ፡ አስቀድሞ፡ ፍጥረተ ዓለማትንና ሕያዋን ፍጡራኑን፡ ማለትም፡ መላእክትንና ሰውን፡ ከነንዛቸው በመፍጠር፥ ኋላም፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በፍጹም ሰውነት ተወልዶና የመስቀል ቤዛነትን በመክፈል፥ የከፋትን መንፈስ፥ ኃጢአትንና ሞትንም በመደምሰስ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ፡ ካህንና ንጉሥ ኾኖ ኖርዋል፤ አኹንም፡ እየኖረ ነው፤ ወደፊትም፡ ለዘለዓለም ይኖራል።

በመጨረሻም፡ አብና ወልድ፡ በባሕርዩ ውስጥ፡ ህልዋን ኾነው በሚገኙበት፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስነቱ፡ የፍጥረቱ ሕይወትና ጠባቂ፥ መጋቢና መሪ ኾኖ ኖርዋል፤ አኹንም፡ እየኖረ ነው፤ ወደፊትም፡ ፍጻሜ በሌለው ዘለዓለማዊነት ይኖራል።

እግዚአብሔር አምላክ፡ በመጀመሪያው የአብነት ህልውናው፡ በእውነት ለፈለጉት ኹሉ፡ በመንፈስ ቅዱስነቱ ሲሠራ ከኖረ በኋላ፡ በመካከለኛው የወልድነት ህልውናው፡ ለፍጥረቱ በከፈለው መሥዋዕትነት፡ ላመኑበት ኹሉ፡ በመንፈስ ቅዱስነቱ፡ ጸጋ ኾኖ እየተሰጠ ቆይቶ፡ በመጨረሻው የመንፈስ ቅዱስ ህልውናው፡ በፍጹም ምልዓትና ስፍነት፡ የፈጣሪነትና የአባትነት ቸርነቱን፡ በመንፈስ ቅዱስነቱ፡ እንዲህ፡ ለዘለዓለም የሚቀጥል ይኾናል።

እንዲህ እንደመኾኑ፡ ኹለንተናው፡ ፍጹሙ መልካም ብቻ ኾኖ፡ ኹሉንም ዓይነት ፍጡር፡ መልካም አድርጎ፡ በመልካምና ለመልካም ሠርቶታል፤ አዘጋጅቶታል። ፍጥረቱንም፡ ከኹለት ከፍሎ፡ የቀደመውንና ረቂቁን፥ መንፈሳዊዉንና መልአካዊዉን፡ "ሰማይ" ብሎ በጠራው ዓለም፥ ኋለኛውንና ግዙፉን፥ ሥጋዊዉንና ሰብአዊዉን ደግሞ፡ "ምድር" ብሎ በሰየመው ዓለም እንዲኖሩ አድርጓል።

ከላይ፡ ለዓይነት ያህል የተጠቀሱትን የመሳሰሉት ተቃራኒ አካላትና ባሕርያት የተፈጠሩት፡ ለመልካም ሕይወትና ህልውና ብቻ መኾኑ፡ በውጤታቸው ፍሬያማነት ታውቋል።

ይኸው መልካም የኾነው እግዚአብሔር፡ በዚሁ፡ መልካም ባሕርዩ፡ አስቀድሞ፡ በመንፈስነት የፈጠረው፡ "መልአክ" የተባለው፡ የመጀመሪያው ፍጡሩና ኋላ፡ በዚያው መልካም መልኩ፡ በሥጋነት የፈጠረው፡ "ሰው" የተባለው፡ ኹለተኛው ፍጡሩ፡ ኹሉን፡ ማለትም፡ መልካም የኾነውን ብቻ ሳይኾን፡ የመልካሙ፡ ተቃራኒ የኾነውን ወገን ለይቶ የሚያሳየውን "እውቀት" የተባለውንና ለእግዚአብሔር ፍጹም አርአያነት የሚያበቃውን ባሕርይ ጨምሮ፡ አስቀድሞ፡ በመንፈስ፥ ኋላ ደግሞ፡ በዕፀ በለስ አማካይነት ለፍጡራኑ ሰጠ።

እኒህ ፍጡራኑ፡ ደጉን ብቻ ሳይኾን፡ ክፉውን ጭምር አውቀው፡ ክፉውን ትተው፡ ደጉን በመምረጥ፡ ለእግዚአብሔር መልክነት የሚያበቃቸውንና ፍጹሙን የሕይወት ልዕልና የሚያቀዳጃቸውን፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን ክብርና ሥልጣን አገኙ።

ይኹን እንጂ፡ በመንፈስና በሥጋ ከተፈጠሩት፡ ከእኒህ ሕያዋን ፍጡሮች መካከል፡ መልካሙን በመምረጥ፡ ፈጣሪያቸውን እግዚአብሔርን መስለው የኖሩ ሲገኙ፡ በዚህ አንጻር ደግሞ፡ ከፈጣሪያቸው በተሰጣቸው፡ የመምረጥ ነጻነት፥ የመወሰን ሥልጣንና የማድረግ ኃይል ተጠቅመው፡ ክፉውን በመምረጥ፡ እየራሳቸውን፡ የመልካሙ የእግዚአብሔር ተቃዋሚዎች አድርገው ያቀረቡ ታዩ። እነዚያኞቹ፡ ቀዳሚዎቹ፡ "ቅዱሳን መላእክት" እና "የእግዚአብሔር ልጆች" ሲባሉ፥ እነዚህኞቹ ደግሞ፡ "ርኩሳን መናፍስት/ሰይጣናት" እና "የሰው ልጆች" ተባሉ።

"መላእክት"፡ እንደሰው ኹሉ፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ ከባሕርዩ ከፍሎና ቅዱስ ጳውሎስ፡ "እስመቦ ሥጋ ዘነፍስ፥ ወቦ ሥጋ ዘመንፈስ"፡ ማለትም፡ "የነፍስ [የሰውነት] ሥጋ [አካል] እንዳለ ኹሉ፡ የመንፈስ [የመንፈሳዊው ፍጡር] ሥጋ [አካል] ደግሞ አለ።" ብሎ እንደጻፈው፡ አካል ያላቸው አድርጎ፡ ለአገልግሎት፡ በመንፈስነት የፈጠራቸው፡ ሕያዋን ፍጡራን ናቸው። ስለዚህ፡ እንደሰው ኹሉ፡ ክፉና ደጉን፡ ለይተው የማወቁንና አውቀው፡ ከኹለት አንደኛውን የመምረጥ ነጻነቱን፥ በዚያ ምርጫቸውም፡ የመወሰን ሥልጣኑንና ያን ውሳኔያቸውን የመተግበር ኃይሉን ሰጥቷቸዋል። (፩ቆሮ. ፲፭፥ ፵፬።)

ከዚህ የተነሣ፡ ከእነሁ መላእክት፡ አንዱ የኾነው፥ ይልቁንም፡ አለቃቸው የነበረው ሳጥናኤል፡ በዚያ መለኮታዊ ጸጋ በመጠቀም፡ እግዚአብሔር፡ "አድርጉ! አታድርጉ!" ብሎ የሠራውን ሥርዓት ተከትሎ ለመፈጸም፡ ፈቃደኛ ባለመኾን፡ "አድርጉ!" ያለውን ባለማድረግ፥ "አታድርጉ!" ያለውንም በማድረግ፡ ተቃውሞውንና ተፃራሪነቱን፡ በገሃድና በድፍረት ስላካኼደ፥ ያን ድርጊቱንም፡ እንደመልካም ጀብድ ቆጥሮ፡ በዕብሪት ስለቀጠለበት፡ በዚያ ሥራው፡ "ሰይጣን" በሚል የግብር ስም፡ "የጥፋት ጠንሳሽና ወጣኝ፤ ምንጭና አባት" ኾነ። ይህም ጥፋቱ፡ "ክፋት/ኃጢአት" ተባለ፤ እርሱም፡ "ክፉ/ኃጥእ" ተባለ።

እንደእርሱ ኹሉ፡ ይህን የመሰለውን ጥፋት የፈጸሙ፡ አዳምና ሔዋን፥ ልጆቻቸውም፥ ሐዋርያው ጴጥሮስ ሳይቀር፡ (ከፈጣሪው ይልቅ፡ የፍጡርን ፈቃድ ባስቀደመ ጊዜ)፡ "ሰይጣናት፥ ክፉዎች፥ኃጢአተኞች!" ተባሉ።

የሳጥናኤልን ፈለግ በመከተል ያጠፉትንና በዚህ ግብራቸው ምክንያት፡ "ሰይጣን!" የሚለውን ስያሜ የተቀበሉትን፡ ሕያዋን ፍጡራኑን፡ መንፈሳውያኑንም ኾነ፡ ሥጋውያኑን፡ ሊቤዥ፥ ያን የተሳሳተና የተበላሸ የጥፋት ኹኔታም ደምስሶ በማደስ፡ ወደቀደመ መልካምነቱ ሊመልስ፡ እግዚአብሔር፡ ራሱን፡ ከአብነት ክብሩ የተለየና ያነሰ አስመስሎ፡ በመለኮታዊው የልጅነት ስሙና መልኩ፥ ባሕርዩና አካሉ፡ በተለይ፡ የኋለኛ ተቃዋሚውን አካልና ባሕርይ ተዋሕዶ፡ በዚያ፡ በፍጡሩ ሰውነት ተወልዶ፡ የመስቀል መከራን መቀበልና መሞት፥ መቀበርና ከሙታን ተለይቶ፡ በድል አድራጊነት መነሣት፡ ሌላ አማራጩ የሌለው የፈጣሪነት ግዴታ ኾነበት። "በድል አድራጊነት ተነሣ!" ያስሰኘውም፡ ክፋትን፥ ኃጢአትንና ሞትን፡ በትዕግሥቱ፥ በደሙና በመሥዋዕትነቱ አስወግዶ፡ መልካምን፥ ጽድቅንና ሕይወትን ስለመለሰ ነው።

ታዲያ! መልካም ብቻ እንጂ፡ የመልካም ተፃራሪ የኾነው ክፋት የማይስማማው እግዚአብሔር አብ፡ መልካሙንና ክፉውን ለይተው ካወቁ በኋላ፡ ክፉውን ተጸይፈው በመተውና መልካሙን ወድደው በመቀበል፡ እርሱን የመምሰል ክብርንና ሥልጣንን፡ በልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስም ኾነ፡ በባሕርይ ሕይወቱ፡ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት፡ ለሕያዋን ፍጡራኑ፡ በፍጹም ፈቃደኛነትና በታላቅ ልግሥና በመስጠቱ፡ ለዚህ ቸር ፈጣሪ፡ ፍጡሩ፡ ሊያደርግ የሚገባው፡ ከቶ ምንድር ነው?

ደግሞም፡ ለአጠፋና ለበደለ ፍጥረቱ ደኅንነት ሲል፡ በፈጣሪነቱ፡ ይህን ዓይነቱን የታዳጊነት መልካም ምግባርን፡ "ልጅ፥ መንፈስ ቅዱስ" በተባለበት፡ በእግዚአብሔራዊ ትሕትናው፡ ራሱን፡ ከኹሉ በታች፡ ዝቅ አድርጎ በመፈጸሙ፡ "ከፈጣሪነቱ ሊዋረድና ከአጥፊ ፍጡሩ ጋር ሊስተካከል ይገባዋል!" ተብሎ ሊጻፍበት ቀርቶ፡ ሊታሰብበት ከቶ ይደፈራልን? ያሳፍራል፣ ያስፈራል እንጂ፡ አይደፈርም።

ይኸው አጥፊ ፍጡሩስ፡ መንፈሳዊዉም ኾነ፥ ሥጋዊው፡ የፈጣሪውን ፈቃድ በመቃወም፡ የክህደት፥ የዓመፅና የአመንዝራነት ክፉ ድርጊትን፡ በድፍረት በመፈጸሙ፡ "ለፈጣሪነት ሊበቃ ይችላል!" ተብሎ ሊጻፍለት ቀርቶ፡ ሊታሰብለት ከቶ ይገባልን? አይገባም።

፱. በዚሁ ምዕራፍና ርእስ ሥር፣ በገጽ ፴፩ (31)፥ አንቀጽ ፫-፬፡ *"...ቃየን 'አትግደል' የሚል ትእዛዝ ኖሮ አይደለም ወንድሙን [አቤልን] የገደለው። ...ቃየን 'አትግደል' የሚል ትእዛዝ በወቅቱ አልተሰጠውም ነበር። ስለዚህ የአትግደል ሕግ በሌለበት የፈጸመው ተግባር ወንጀል ሆ[ኾ]ኖ ቃየንን በፍርድ አያስጠይቀውም።"* የሚለው የብያኔ አስተያየት፡ ከእምነታችን ውጭ መኾኑን ማስረዳት አግባብ ይኾናል።

ይህንኑ እውነታ፡ እንዲህ በሚል ዐረፍተ ነገር አጠቃልሎ መግለጽ ይቻላል፡- እግዚአብሔር፡ የእሥራኤልን ልጆች፡ በሙሴ የተልእኮ መሪነት፡ ከግብፅ ባርነት፡ ነጻ ካወጣቸው በኋላ፡ በሰብአዊውና በፍጥረታዊው ሕሊናቸው አማካይነት ከሚነግራቸው በላይ፡ በተአምራቱና በመቅሠፍቱ ያሳያቸው፡ ያ ኹሉ መለኮታዊ ኃይል እንኳ፡ ወደእርሱ እውነተኛ አምልኮት ሳይመልሳቸው እንደቀረ ይታወቃል።

እንዲያውም፡ በዚያ፡ በታወቀው ክህደታቸውና ዓመፃቸው፥ አመንዝራነታቸውም፡ እንደአሕዛብ፡ ጣዖት ቀርፀው በማምለካቸው፡ ሊደርስባቸው ከነበረው ጥፋት፡ በሙሴ አማላጅነት፡ ታድጓቸው፡ ዓሥሩን ቃላት፡ በበድኑ የድንጋይ ጽላት ላይ ጽፎ እንደሰጣቸው ተጽፏል። ከእነዚያ ቃላት መካከል አንዱ፡ "አትግደል!" የሚለው መኾኑም ይታወቃል።

እግዚአብሔር፡ ጥንቱኑ፡ በሰብአዊው ልቦናቸው ጽላት ላይ በተፈጥሮ የጻፋቸው እኒያ ሕያዋን ቃላት፡ በእነርሱ ዘንድ ሙታን ኾነው፥ ከዚያ ተነሥተውና በድንጋይ ላይ ተቀርፀው፡ ለእነርሱ፡ እንደገና ተመልሰው የመሰሰጠታቸው ውርደት፡ የእነርሱው፡ የክህደታቸውና የዓመፃቸው፥ የአምልኮ አመንዝራነታቸውም መራራ ውጤት መኾኑ፡ እሙን ነው።

እሥራኤሎች፡ በዚያ ታላቅ ኃጢአታቸው ምክንያት፡ እነዚህን ቃላት፡ በዚያ መልክ፡ ከእግዚአብሔር ከመቀበላቸው ከ፫ሺህ ዓመታት ያህል በፊት፥ ማለትም፡ ከላይ እንደተገለጸው፡ ሰው ከተፈጠረበት፡ ከጥንቱ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ እግዚአብሔር፡ እነዚህኑ ቃላት፡ ከሰብአዊውና ከፍጥረታዊው ሕያው ባሕርያቸው ጋር አንድ አድርጎ ፈጥሮና በየልቦናቸው ላይ ቀርፆ እንደሰጣቸው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ያውቃሉ። እነዚያም ቃላት፡ የኪዳነ ልቦና እምነታቸው ኾነውላቸው እንደኖሩ፥ ዛሬና ወደፊትም እንደሚኖሩ፡ እያረጋገጡ ይመሰክራሉ።

ስለዚህ ነው፡ "አትግደል!" የሚለው ሕግ፡ ከአቤልና ቃኤል በፊት፡ ከወላጆቻቸው፡ ከአዳምና ከሔዋን መፈጠር ጀምሮ፡ ከመላእክትና ከሰው የተፈጥሮ ባሕርያት ጋር ዐብሮ የነበረ መኾኑን፡ አረጋግጦ መግለጽ አስፈላጊ የኾነው።

፲. በምዕራፍ ሦሥ[ስ]ት፣ በገጽ ፴፫ (33)፡ *"ፍጹምነቱ እያለ፡ ጸጸቱን ምን አመጣው?"* በሚለው ዋና አርእስት ውስጥ በቀረበው ሓተታ ላይ፡ የእኛን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት የእምነት አቋም፡ ከዚህ በሚቀጥለው አንቀጽ አብራርቶ ማቅረብ አስፈላጊ ኾኖ አግኝቼዋለሁ።

እግዚአብሔር፡ ሰውን፡ በሥጋዊ ነፍስነት ሲፈጥረው፡ ቀደም አድርጎ፡ በእሳታዊ መንፈስነት ላስገኛቸው መላእክት እንዳደረገው ኹሉ፡ ለዚሁ፡ ለሰብአዊ ፍጡሩም፡ የእርሱ የኾነውን፡ መልኩንና አርአያነቱን ብቻ ሳይኾን፡ ኹሉን፥ ክፉውን ሳይቀር፡ ለይቶ የማወቅንና ፍጹም መልካም የመኾንን ወገን ለመምረጥ፥ ያን ምርጫውን ለመተግበር የሚችልበትን ሥልጣኑንና ኃይሉን ጭምር አቀዳጅቶና አሚልቶ የሠራው መኾኑ እርግጥ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ እግዚአብሔር፡ ይኸው፡ በመልኩ የፈጠረው ሰብአዊ ፍጡሩ፡ በመጪዎቹ ጊዜያት፡ በተደጋጋሚ የሚፈጽማቸው ድርጊቶች ምን እንደሚኾኑ፡ በፈጣሪነቱ፡ አስቀድሞ የሚያውቅ ቢኾንም፡ ምናልባት በቀደሙት የደረሰው ኹሉ፡ ትምህርት ኾኖት፡ ክፉውን እንደመረጠው፡ እንደሰይጣን ሳይኾን፡ "አኹን ያወቀውን፡ ያን ክፉውን ወገን ትቶ፡ በምሳሌነት፡ ከፊቱ እንደቆምሁት፡ እንደፈጣሪው፡ እንደእኔ ለመኾን የሚያበቃውን፡ መልካሙን ወገን ይመርጥ ይኾናል!" የሚል አሳብ እንደነበረው፡ ከተከታታዮቹ የፍጥረት ኺደቶችና ድርጊቶች መረዳቱ አያዳግትም።

እዚህ ላይ፡ የመጀመሪያው ሰብአዊ ፍጡር፡ አዳም፡ "አኹን ያወቀው፡ ያ፡ ክፉው ወገን" የተባለው "ሰይጣናዊነት"፡ ምን እንደኾነ፡ ለይቶ መግለጹ አስፈላጊ ይኾናል።

ይኸውም፡ ለሞት፥ (ማለትም፡ ከእግዚአብሔር ሕይወት አውጥቶ፡ ለሰይጣናዊ አኗኗር) እንደሚዳርገው አስቀድሞ ተነግሮት ሣለ፡ እርሱ ግን፡ "ብሞትም ልሙት!" ብሎ፡ የዕፀ-በለስን ፍሬ በመብላት፡ ምንነቱን (የክፉው ወገን መኾኑን) የለየበትና ማንነቱን (ሰይጣንነቱን) የተረዳበት እውቀት ነው።

ከአንዱ ኖኅና ከቤተሰቡ በስተቀር፡ ሌላው የሰው ወገን ኹሉ፡ እርሱ ፈጣሪው፡ ላዘጋጀለትና ምርጫው እንዲኾን ለፈለገው፡ ለመልካሙ ሕይወት ሳይኾን፡ ሰይጣናዊዉን ወገን የመረጠ በመኾኑ፡ ያ ምርጫ ለሚያስከትለውና ለማይቀረው የጥፋት ፍጻሜ፡ ራሱን በመዳረጉ፡ እግዚአብሔር ያዘነ መኾኑን፡ በቃል ኪዳን እምነታቸው በመጽናታቸው፡ ከድምሳሴ ለተረፉት፡ ለኖኅና ለልጆቹ ለማሳየት፡ "ወነስሐ እግዚአብሔር፡ እስመ ገብሮ ለእጓለ እመሕያው ላዕለ ምድር።" ማለትም፡ "ሰውን፡ በምድር ላይ ስለፈጠረው፡ እግዚአብሔር ተጸጸተ።" ተብሎ እንዲጻፍ ያድርግ እንጂ፡ ይህ ኹሉ እንደሚኾን፡ ፈጣሪ አስቀድሞ እንደሚያውቅ ጥርጥር የለውም። (ዘፍጥ. ፮፥ ፮።)

ስለዚህ፡ ከመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ እስከኖኅ፥ ቀጥሎ፡ እስከመልከ ጼዴቅ፥ ከዚያ፡ እስከአብርሃም፥ ተከትሎ፡ እስከሙሴና ከዚያ፡ እስከዳዊት ድረስ፡ በአጠቃላይ፡ የሰው ልጆች ውሳኔ፥ በተናጠልም፡ የእያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡሩ ምርጫ፡ እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚያበቃውን፡ መልካሙን ሳይኾን፡ ሰይጣን ወደመኾን የሚያደርሰውን፡ ክፉውን በመኾኑ፡ እግዚአብሔር ሲጸጸትበት የቆየበት፡ የፍጥረቱ፡ የኵነኔና የፍዳ ዘመን መኖሩ ሊታበል ከቶ አይቻልም።

አዎን! ይህ አሳዛኝ ኹኔታ፡ ዛሬም፡ በእምቢተኛው ሰብአዊ ትውልድ ዘንድ እንደቀጠለ የሚታይ ቢኾንም፡ ምርጫዋ፡ እግዚአብሔርን ለመምሰል የበቃችበትን መልካሙን ማድረግ የኾነና ይህንኑ በቍርጥ እውነተኛነት የፈጸመች፡ የመጀመሪያዋም፥ የመደምደሚያዋም፡ አንዲት ኢትዮጵያዊት፡ እርሷም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም የተገኘችበት፡ የመጨረሻው የሕይወት ዘመን ደረሰ።

ያ የሕይወት ዘመን በደረሰም ጊዜ፡ እነሆ፡ በእርሷና ከእርሷ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ሰው ኾኖ በተወለደው፡ በእግዚአብሔር አብ፡ የባሕርይ ልጅ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ያ፡ ፈጣሪን ሲያስጸጽት የኖረ አሳዛኝ ኹኔታ ተወግዶ፡ ፍጥረተ ዓለሙ፡ በቅዱሱ የምሕረት ኪዳን ሊመላ ቻለ።

እስከዚሁ፡ የምሕረት ዘመን ድረስ፡ መልከ ጼዴቅን በመሰሉት፡ በወንዶቹ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ዘንድ ተጠብቆ የኖረው፡ የእግዚአብሔሩ ልጅነት፥ ክህነትና መንግሥት፡ ከዚህ ጊዜ አንሥቶ ደግሞ፡ በሴቶቹም ኢትዮጵያውያት ጭምር የሚጠበቅ ኾኖ፡ በመለኮታዊው የትስብእት ቤዛነት፡ በዘለዓለማዊ ጽናት ሊቀጥል በመቻሉ፡ እግዚአብሔር፡ ሰውን በመፍጠሩ "ተጸጸተ!" የተባለበት፡ ያ፡ ክፉ ኹኔታ፡ በመልካሙ ተተክቶ፡ እግዚአብሔር፡ ሰውን በመፍጠሩ፡ "ተደሰተ!" በተባለበት የትንሣኤ ሕይወት እነሆ እንድንኖር ኾነ!!!

፲፩. በዚሁ ምዕራፍ፡ ገጽ ፴፬ (34) ላይ፡ *"ሕገ ኦሪት ከማን ለማን በነማንስ በኩል ተሰጠ"* በሚለው ርእስ ሥር ለተገለጸው አሳብ፡ በእኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ዘንድ ያለውን እውነታ በማብራራት፡ ማስተካከያ መስጠቱን አስፈላጊ ኾኖ አግኝቼዋለሁ። ይህም፡ እንደሚከተለው ነው:-

ከሕገ [ከኪዳነ] ኦሪት በፊት፡ ኪዳነ ልቦና መኖሩ፡ የታመነ ሲኾን፡ እርሱም፡ ማለትም፡ ይኸው ኪዳነ ልቦና፡ ተጠብቆና ሕይወት ኾኖ ኖረው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ዘንድ መኾኑ፡ ኹሉ የሚያውቀው እውነታ ነው። ከኪዳነ ልቦና በኋላ፡ ወደ፫ ሽህ ዓመታት ቆይቶ፡ ኪዳነ ኦሪት፡ ለእኒሁ ኢትዮጵያውያን ሳይኾን፡ ለእሥራኤላውያን የተሰጠ፥ እርሱም፡ ከማንና ለምን እንደተሰጠ፡ ከዚህ በላይ ቀደም ብሎ ተገልጿል።

ይኸውም፡ እሥራኤል፡ በእግዚአብሔር ላይ በፈጸሙት፡ የአምልኮ ክህደትና ዓመፅ፥ አመንዝራነት ምክንያት መኾኑ ነው። እኒያ እሥራኤላውያን፡ ያንኑ የአምልኮ ባዕድ ኃጢአታቸውን፡ በበለጠ አጠናክረው በመቀጠላቸው፡ በጽላተ ሕጉ አማካይነት፡ ኪዳነ ኦሪት ወደኢትዮጵያውያኑ የመጣው፡ በባለአደራነት መኾኑ፡ እዚህ ላይ ሊታወስ ይገባል።

"ኦሪት፡ በሙሴ በኩል ተሰጥ፤ ተጻፈም።" ቢባልም፡ ሙሴ፡ የኦሪት መጻሕፍቱን፥ በተለይም፡ በዘፍጥረት መጀመሪያና ዘፀዓትን በከፊል የጻፈው፡ ከኢትዮጵያውያን ባገኘው እውቀቱና አምልኮቱ፥ በኢትዮጵያዊነቱ ማንነትም መኾኑ፡ መዘንጋት የለበትም።

፲፪. በዚሁ ምዕራፍ፡ በገጽ ፴፮ (36) ላይ፡ *"እስከ ኦሪት ፍጻሜ የሰው ምንነትና ዘለዓለማዊነት ተለይቶ አልተረጋገጠም ነበር"* በሚለው ርእስ ሥር ለሠፈረው አሳብ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት እምነት የሚለውን፡ እንደሚከተለው በመግለጽ፡ ማስተካከሉን፡ አግባብ ኾኖ አግኝቼዋለሁ።

ሰው፡ ፍጹምነትን ያገኘው፡ ገና በመጀመሪያ ፍጥረቱ ነው፤ ይኸውም፡ እግዚአብሔር፡ "ሰውን፡ በመልካችን፥ በምሳሌያችን እንፍጠር!" ብሎ፡ ወንድና ሴት የሚገኙበትን፡ አዳምን፡ በቅድሚያ፡ በመልካሙ ንጽሓ ባሕርይ ብቻ በፈጠረው ጊዜ ሲኾን፥ ቀጥሎ ደግሞ፡ ይኸው የፈጠረው ሰው፡ ዕፀ-በለስን በመብላቱ፡ **"ናሁ አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ፤ ያእምር ሠናየ፥ ወእኩየ!"** ማለትም፡ **"መልካምንና ክፋን ለይቶ ያውቅ ዘንድ፡ እነሆ አዳም፡ ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!"** ባለው ጊዜ መኾኑ ተረጋግጧል። (ዘፍጥ. ፫፥ ፳፪።)

ለዚህ መለኮታዊ ቃል እውነተኛነት፡ ከላይ፡ በመልካሙና በወንዶቹ ወገን ከተጠቀሱት ጋር፡ አቤልና ሴት፥ ሄኖክና ኖኅ፥ መልከ ጼዴቅና ሙሴ፥ ኤልያስና ዮሐንስ መጥምቁ፥ እኒህና እነርሱን የመሰሉት፡ በምስክርነት የሚዘከሩ ሲኾኑ፥ በዚሁ፡ በፍጹሙ መልካምነት፡ ለአምላክ እናትነት የበቃችው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከሴቶች መካከል፡ በታላቅ አብነት የምትጠራ ኾናለች።

እንዲያውም፡ ኦሪት፡ ሰው፡ ፍጹምነትን ያገኘበት ሳይኾን፡ ፍጹምነቱን፡ በታላቅ ውርደት፡ ጨርሶ ያጣበት መኾኑ፡ ኦሪታውያኑ አይሁድ፡ በእግዚአብሔርና በአገልጋዩ በሙሴ፥ በሌሎቹ ነቢያትና በመጨረሻ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ከዚያ በኋላ፡ እስከዛሬም፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው ኢትዮጵያና በልጆቿ ላይ በገሃድ በፈጸሙትና እየፈጸሙት ባለው የጠላትነት ሥራ ታይቷል፤ እየታየም ነው። ከዚህ የተነሣ፡ "ሰይጣን" በተባለው፡ በርኩስ መንፈስ አበጋዝነት የተካኼደው፡ የእሥራኤል የአምልኮ ክህደትና ዓመፅ፥ አመንዝራነትም ያመጣው ሕገ ኦሪት፡ የክፋት ምልክት ሲኾን፥ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መሪነትና በቅድስት ድንግል ማርያም እናትነት፡ በተከናወነው በምሥጢረ ሥጋዌ የተገኘው ኪዳነ ምሕረት ደግሞ፡ የመልካም ምልክት ሊኾን ችሏል።

ስለዚህ፡ ፍጡራኑ፡ መላእክትና ሰዎች፡ ገና ከመጀመሪያው፡ በተፈጥሮአቸው፡ እንደአምላክ የመኾንን ብቅዓት፡ ከራሱ ከፈጣሪ፡ በቸርነት የተለገሡ በመኾናቸው፡ ፍጹምነትን የተቀዳጁ ሲኾን፥ ያንንም ፍጹምነት፡ ከእነርሱ መካከል፡ ከክፉው ይልቅ፡ መልካሙን በመምረጥ፡ ይዘው መቀጠል የተቻላቸው ጥቂቶች ሲኖሩ፥ ነገር ግን፡ አብዛኞቹ፥ በተለይ በሰዎች በኩል ያሉት፡ ከመልካሙ ይልቅ፡ ክፋትን መርጠው፡ የእርሱ አበጋዝ ከኾነው፡ ከሰይጣን ጋር በመወገናቸው፡ ያን ፍጹምነት አጥተው፡ የመጨረሻውን ጠቅላላ ጥፋት፡ በየራሳቸው ላይ ያደረሱ መኖራቸው ይታወቃል።

ለዚህም፡ ቀድሞ፡ ከአዳምና ሔዋን ጊዜ ጀምሮ፡ በዘመነ ኪዳነ ልቦና ከነበሩት መካከል፡ በመልካሙ ወገን፡ ይህን ፍጹምነታቸውን የጠበቁት፡ ለምሳሌ ያህል፡ አቤልና ሄኖክ፥ ኖኅና መልከ ጼዴቅ፥ አብርሃምና ሎጥ፥ ዮቶርና ሙሴ፥ በዘመነ ኪዳነ ኦሪት ደግሞ፥ ሳሙኤልና ዳዊት፥ ኤርምያስና ኤልያስ፥ እነአቤሜሌክና ቤተሰቦቻቸው፡ በማስረጃነት ይጠቀሳሉ።

በክፉው ወገን ደግሞ፡ ያን ፍጹምነታቸውን አጥተው፡ በጥፋት ውኃና በተለያዩ መቅሠፍቶች፥ በእሳትና በሰይፍ ያለቁትን የሰውን ዘሮች፡ ከቃኤል ጀምሮ፡ የፈርዖንን ግብፃውያን፥ የሰዶምንና የገሞራን ሰዎች፥ እንዲሁም፡ እሥራኤልንና አይሁድን፡ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። ስለዚህ፡ ኪዳነ ኦሪቱ፡ የክፋት ምርጫ ያመጣው፡ የሞት መራራ የፍሬ ሲኾን፥ ኪዳነ ምሕረቱ ደግሞ፡ የመልካሙ ምርጫ ያመጣው፡ የሕይወት ጣፋጭ ፍሬ መኾኑን በማስተዋል መመልከት ይገባል። (ዘፍጥ. ፫፥ ፳፬።)

በዚህ መልክና ይዘት፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በግል ውሳኔዋ፡ ምርጫዋ፡ መልካሙ በመኾኑ፡ በቤዛነቱ፡ ኪዳነ ምሕረትን ያስገኘውን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመውለድ እንደበቃች ኹሉ፡ እያንዳንዷ ሴት እና እያንዳንዱ ወንድ፡ በየግል ውሳኔያቸው፡ ምርጫቸው፡ መልካሙ በሚኾንበት ጊዜ፡ ሴቷ፡ ድንግል ማርያምን፥ ወንዱ ደግሞ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን መስሎ እንዲገኝ የሚቻል ኾነ።

የሰው ልጆች፡ ይህን የመሰለውን፡ ፍጹም ሙሉ የኾነ፡ የችሎታና የሥልጣን ብቅዓት፡ ገና ከፍጥረት ልደት ጀምረው እስከዛሬ ተቀዳጅተው የሚገኙ ሲኾን፡ አብዛኞዎቹ ግን፡ ዛሬም፡ የምርጫ ዝንባሌያቸው፡ ወደክፉው ኾኖ ይታያል። ከዚህ የተነሣም፡ እነሆ፡ ዓለም፡ በጥፋት ጐዳና ላይ መጓዙን ቀጥሎበት ይገኛል። ፍጻሜውም፡ በጥፋት ውኃ ጊዜ እንደኾነው፡ ከእግዚአብሔር ሕይወት ተለይቶ መደምሰስ እንደሚኾን ይታመናል። በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል፡ **"ወበከመ ኮነ፡ በመዋዕለ ኖኅ፡ ከማሁ ይከውን ምጽአቱ ለወልደ እጓለ እመሕያው።"** ማለትም፡ **"በኖኅ ዘመን የነበሩት ሰዎች፡ የጥፋት ውኃ መጥቶ፡ ኹሉን እስከወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፡ የሰው ልጅ አመጣጥ፡ እንደዚያ ይኾናል።"** ተብሎ እንደተነገረው። (ማቴ. ፳፬፥ ፴፱።)

፲፫. በዚሁ ምዕራፍ፡ በገጽ ፵ (40)፥ በ፫ኛውና በ፬ኛው አንቀጾች ውስጥ፡ የካምን፡ በአባቱ በኖኅ የመረገሙን ዝክረ ነገር ባነሣህበት ሓተታህ ውስጥ፡ ይህን ርእስ በሚመለከት፡ በመጽሓፍ ቅዱስ ዓምድ ላይ እንዲሠፍር የተደረገው ቃል፡ ቀድሞውንም ቢኾን፡ በሰዎች አሳሳችና ሓሳዊ እጅ እንጂ፡ "በእውነት የእግዚአብሔር ቃል ነው!" ብሎ ለመቀበል የሚያዳግት ስለመኾኑ፡ ከመጻሕፍቴ፡ በአንደኛው ውስጥ የሠነዘርሁትን የማስተካከያ ትችት፡ ሳታነብበው እንዳልቀረህ እገምታለሁ። ነገር ግን፡ እዚህ ላይ አላወሳኸውም፤ ለምን?

ለምን እንዳላነሳኸው፡ ምክንያቱን ለማወቅ፡ አጥብቆ የመከታተሉንና የመጠየቁን ግዳጅ ከመቀጠል ይልቅ፡ "ያን፡ የማስተካከያ ትችቴን፡ እዚህ ላይ መጥቀሱ ይሻላል!" በማለት፡ እነሆ፡ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ፤ እርሱም፡ "አዳምና ሔዋን" በተባሉ፡ ኹለት ወጣቶችና በእኔ መካከል ከተደረገው አጭር መጠይቃዊ ቃለ-ምልልስ፡ የተወሰደው ነው።

አርእስቱ፡ "የኖኅ ስካር ያስከተለውን ጠንቅ፡ ኢትዮጵያውያን ያስወገዱበት መፍትሔ፡፡" የሚል ሲኾን፡ አጭሩ መጠይቃዊ ቃለ ምልልስ፡ እንዲህ እያለ ይቀጥላል፡-

"**ጥያቄ፡-**

*ይህን፡ እጅግ የጠቀመንን ውይይት፡ ከአንተ ጋር በመጀመራችን ምክንያት፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን የማንበብ ባህልንም ስላዳበርን፡ ኖኅንና ልጆቹን በሚመለከት፡ አእምሮአችን ሊሸከመው፥ ሕሊናችንም ሊቀበለው ያቃተው፡ አንድ ቍም ነገር፡ በቅዱሱ መጽሐፍ ውስጥ ሠፍሮ አይተናልና፡ ያን፡ ቍም ነገር፡ እዚህ ላይ እናነሣብህ ዘንድ ፍቀድልን! እንግዴህ፡ እንዳስተማርኸን፡ በሃይማኖት ይሉኝታና ፍርሃት የለምና፡ ይህን በመጠየቃችን፡ እንደድፍረት እንደማይቆጠርብን፥ አንተም፡ ይቅር እንደምትለን እናምናለን።*

*"ቍም ነገር" ያልነውም፡ በአሪቱ፡ የመጀመሪያ መጽሐፍ በኾነው፡ በዘፍጥረት፡ በምዕራፍ ፱፥ ከ፳ እስከ፳፯ ባሉት ቍጥሮች ውስጥ ተጽፎ ስለሚነበበው ቃል ነው፤ ይህ ጥቅስ፡ ኖኅ፡ ገበሬ ኾኖ፡ ወይንን ከተከለ በኋላ፡ ከተመረተው የወይኑ ፍሬ የተጠመቀውን ጠጅ ጠጥቶ፡ እንደሰከረና በድንኳኑ ውስጥ እንደተራቈተ፥ ያን ራቁትነቱንም፡ ከልጆቹ አንዱ የኾነው፡ ካም እንዳየ፥ ባየውም ጊዜ፡ የአባቱን ራቁትነት፡ በልብስ በመሸፈን ፈንታ፡ ስቆ፡ ተመልሶ ወጥቶ፡ ለኹለቱ ወንድሞቹ፡ ለሴምና ለያፌት እንደነገራቸው፥ እነርሱም፡ የአባታቸውን ራቁትነት ላለማየት፡ ሸማ፡ በጫንቃቸው ላይ አድርገውና የኋሊት ኼደው፡ የአባታቸውን ዕርቃን እንደሸፈኑ ይናገራል።*

*ይኸው ቃል፡ ከዚህ አያይዞ፡ አባታቸው፡ የኖኅ፡ ስካሩ ከለቀቀው በኋላ፡ የኾነውን ኹሉ ስላወቀ፡ ሴምንና ያፌትን፡ እንደመረቃቸው፥ ስሙ፡ በድርጊቱ ውስጥ ፈጽሞ ያልተወሳውን፡ የካምን ልጅ፡ ከነዓንን ግን፡ በክፉ እርግማን እንደረገመው፥ ያም እርግማን፡ ከነዓን ርጉም ኾኖ፡ ወንድሞቹን፡ በተገዢነት እንዲያገለግል ለሚያደርግ ባርነት እንደዳረገው ያስረዳል።*

*ታዲያ! የዚህ ጥቅስ ቃል፡ በውስጡ፡ እርስ በርሱ የሚቃረን ድርጊት ጎልቶ ስለሚታይበት፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ፍጹም ሃይማኖት ላይ የተመሠረተና የጸና ሕሊና ያለውን ሰው፡ ግራ ስለሚያጋባው፡ ስለዚሁ፡ "የእግዚአብሔር ቃል ነው!" ተብሎ፡ ተቀባይነትን ስላገኘው አጻጻፍ፡ ምን ዓይነት የመፍትሔ አሳብ ይኖራል?*

"**መልስ፡-**

መቸም፡ እግዚአብሔር፡ እናንተን የጠራችሁ፡ ለእርሱ መሣሪያዎቹ ኾናችሁ፡ በመድኃኒትነት እንድታገለግሉት፥ እርሱም፡ የተለመደ ቸርነቱን ይፈጽምባችሁ ዘንድ ነው፤ እናንተም፡ ጥሪውን ተቀብላችሁ፡ መልእክቱን ለማድረስ የተስማማችሁት፡ ያለምክንያት አይደለም። "የእርሱ ሕያዋን ቅርሶቹ አድርጎ የሠራቸውን፥ የመሠረታቸውንና የሚጠብቃቸውን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ከታወቀው የጠላት የሙስና ጠንቅ ሊያድናቸው ስለፈቀደ ነው!" ብዬ አምኛለሁ፤ በዚህም፡ ድንቅ የመለኮት ጥበባዊ ሥራ፡ እኔን ደስ እንዳለኝ፡ እናንተንም፡ እንዲሁ፡ ደስ ሊላችሁ ይገባል።

ይህንም ያልኩት፡ በዚህ ጥያቄያችሁ አቀራረብ ውስጥ፡ ለዚህ እውነታ፡ ማረጋገጫ የኾነውን ምልክት፡ በማስተዋል ስለተመለከትሁ ነው። አዎን! በእኛ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ እውን ኾኖ፡ ጥንትም፥ በመካከለኛውም ዘመን፥ ዛሬና ወደፊትም፡ ሲሠራ የሚታየው፡ ሕያው የኾነው፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ፡ ጊዜያዊ፥ ወይም፡ ጠፊ የኾነው፡ የፍጡራን ጥበብና ኃይል፥ ሀብትም  አለመኾኑን፡ የኹለንተና ህልውናችን፡ በሚበቃ አረጋግጦ ያስረዳል።

ያም የእግዚአብሔር ፈቃድ፡ ምን እንደኾነ፡ ቃሉ፡ በዚህ፡ ረዥምና የጠለቀ ውይይታችን ጊዜ፡ በየአጋጣሚው፡ ተመላልሶ ስለተጠቀሰ፥ በእናንተም፡ በየልባችሁ ጽላት ላይ ተጽፎ የሚገኝ መኾኑን እንድታውቁት ስለተደረገ፡ ይህን እውነታ፡ በተለይ እናንተ፡ በአኹኑ ሰዓት፡ ደኅና አድርጋችሁ የተገነዘባችሁት ለመኾኑ አልጠራጠርም።

ይህም እውነታ፡ **"ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ።...እያንዳንዱ ሰው፡ ባልንጀራውን፥ እያንዳንዱም፡ ወንድሙን፡ 'እግዚአብሔርን እወቅ!' ብሎ አያስተምርም፤ ከታናሹ ጀምሮ እስከታላቁ ድረስ፡ ኹሉ ያውቁኛልና!"** ደግሞም፡ **"ልጆችሽም ኹሉ፡ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይኾናሉ፤"** የሚለውን የነቢያትን ቃል በመጥቀስ፡ እውነተኛው መምህር ኢየሱስ ክርስቶስ፡ **"'ኹሉም፡ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይኾናሉ!' ተብሎ፡ በነቢያት ተጽፏል፤ እንግዴህ፡ ከአብ የሰማ፥ የተማረም ኹሉ፡ ወደእኔ ይመጣል"** በሚለው ቃል መሠረት፡ በኢትዮጵያውያን ሰውነት ላይ ሕያው ኾኖ ሲታይና ሲፈጸም የኖረውና ዛሬም፡ እየተፈጸመ ያለው እውነታ ነው። (ኢሳ. ፶፬፥ ፲፫። ኤር. ፴፩–፴፩-፴፬። ዮሐ. ፮–፵፭።)

በፈጣሪው መልክ የተፈጠረው ሰው፡ በተፈጥሮ በተለገሠው፡ የመምረጥ ነጻነቱና የመወሰን ሥልጣኑ፡ ፍላጎቱን ከሚፈጽምበት፡ የሕሊና ባሕርዩ ጋር፡ በተጨማሪ፡ ይህ፡ መለኮታዊው የተስፋ ቃል፡ በጸጋ ታክሎ ስለተሰጠው፡ ለእውነት አዋቂነትና ለሃይማኖት ባለቤትነት እንዲበቃ አስችሎታል፤ ከዚህ ብቅዓት የደረሰውም፡ ኢትዮጵያዊው ነው፤ እርሱም፡ የዛሬዎቹ፡ እናንተ ናችሁ።

ስለዚህ፡ ሕሊናችሁ ከሚነግራችሁ ጋር፡ እግዚአብሔር፡ በየልቦናችሁ ውስጥ ካሳደረው፥ በየልባችሁ ጽላትም ላይ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጣቶቹ ከጻፈው ሕጉ፡ የተለየ፥ ወይም፡ ተቃራኒ ኾኖ የምትሰሙትን፡ ማናቸውንም ዓይነት ቃል፥ የምታነብቡትን፡ ማናቸውንም ዓይነት ጽሑፍ፡ አምናችሁ ልትቀበሉት አይገባም። ለዚህም፡ አኹን የጠቀሳችሁትን፡ በኖኅ ስካር ምክንያት፡ በእርሱና በልጆቹ መካከል፡ "ደረሰ!" ተብሎ የተጻፈውን ኹኔታ፡ እንደማስረጃ አድርጎ በማቅረብ፡ መመርመር ይቻላል።

በመሠረቱ፡ ኖኅ፡ ምንም እንኳ፡ አካኼዱን፡ ከእግዚአብሔር ጋር አድርጎ የኖረ ጻድቅ ሰው ቢኾን፥ ይህም ጽድቁ፡ ይኸው፡ ከዝክረ ነገሩ እንደተረዳነው፡ በምግባሩ የተረጋገጠም ቢኾን፡ እርሱም፡ እንደሌላው፡ እንደማናቸውም ተራ ሰው፡ ዕሩቅ ብእሲ መኾኑን እንመለከታለን። ይህም ማለት፡ ኖኅ፡ በ፩ቱ ባሕርያተ ሥጋና በ፫ቱ ባሕርያተ ነፍስ የተፈጠረ መኾኑን በማሳየት፡ የሰብአዊ ደካማነት ጎኑን ለማሳወቅ ያህል፡ የስካሩን ነገር ማንሣቱ፡ "ምናልባት፡ አግባብነት ይኖረው ይኾናል!" ብሎ መደምደሙ እንደሚያስኬድ መገመት ይቻላል።

ነገር ግን፡ የአባቱን ራቁትነት ያየው፡ እንደመጽሓፉ ቃል፡ ካም ሲኾን፡ ኋላ፡ ከስካሩ ሲነቃ ደግሞ፡ ኖኅ፡ ትንሹ የልጅ ልጁ ከነዓን እንደኾነ አውቆ፡ የረገመው፡ እርሱን፡ ከነዓንን እንደኾነ፡ በግልጽ ተጽፏል። እንደነገሩማ፡ ስካር፡ ራስን ጨርሶ እስከመርሳት የሚያደርስ፡ የአእምሮ ቀውስ በመኾኑ፡ የሰከረው ሰው፡ በራሱና በአካባቢው ላይ የሚኾነውንና የሚያደርገውን ኹሉ አለማወቁ ግልጽ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ ኖኅ፡ በስካሩ ምክንያት፡ የራሱን ራቁትነት እስካለማወቅ የደረሰ ሲኾን፡ ኋላ፡ ስካሩ ሲያልፍለት፡ ከልጆቹ መካከል፡ ያ፡ አንዱ ልጁ፥ ወይም፡ የልጅ ልጁ፡ "ዕርቃኔን አየ!" ብሎ፡ እንዴት ሊያውቅ፥ ራቁትነቱን ያየው፡ ካም ይኹን ከነዓን፡ እንዴት ሊለይስ እንደቻለ መጻፉ፡ አጻጻፉ መኾኑን፡ የማነኛውም ሰው ሕሊና፡ በቀላሉ የሚገነዘበው ነው።

ኖኅ፡ ዕርቃኑን ያየው፡ ልጁ ካም ይኹን፥ ወይም፡ የካም ልጅ፡ ከነዓን ይኹን፡ ለይቶ ለማወቅ ያልቻለው፡ "በስካሩ ምክንያት ነው!" ከተባለም፡ ታዲያ፡ እርግማኑ፡ እንዴት፡ "በትክክል የተደረገ ነው!" ተብሎ፡ ሊመዘገብ ይቻላል? በትክክል ካልተደረገስ እንዴት፡ "የእግዚአብሔር ነው!" ተብሎ፡ ሊጸናና ተፈጻሚነት ሊኖረው ይችላል? እንደመጽሓፉ ቃል፡ ጥፋቱን የፈጸመው፡ ካም ሲኾን፡ ጸሓፊው፡ እንዴት፡ ከነዓን ብሎ እንደጻፈው አያጠያይቅምን? በእርግጥ፡ ያጠያይቃል።

ደግሞም፡ ባንድ ወገን፡ ካም ኾነ፡ ከነዓን፡ ከኹለት አንደኛው፡ ድንገት ሳያስበው፡ አባቱ እነበረበት የድንኳኑ ክፍል ውስጥ፡ ዘው ብሎ ሲገባ፡ "እንደዚያ ኾኖ አየዋለሁ!" ብሎ ያላሰበውን፡ አባቱን፡ ራቁቱን ተዘርግቶ ሲያገኘው፡ ተደናግጦ፥ ወይም፡ ኖኅ፡ በስካሩ ምክንያት፡ ምናልባት፡ እንደሕፃን ልጅ ያደርገው የነበረ ነገር ኖሮ፡ ያ ነገር ስላሳቀው፡ ወደኋላው ምልስ ብሎና በችኮላ ኼዶ፡ ያየውን ጉድ፡ ለወንድሞቹ ነግሮ ይኾናል። እንግዴህ፡ ይህን በመናገሩ ብቻ ነው፡ ይህ አድራጎቱ፡ እንደታላቅ ኃጢኣት ተቆጥሮበት፡ ያን የመሰለ ከባድ የኾነ፥ ከትውልድ ወደትውልድ ሲተላለፍ የኖረ እርግማንን እንዳስከተለበት፡ በግልጽ የተጻፈው።

በሌላውም ወገን፡ ኹለቱ ልጆቹ፡ ሴምና ያፌት፡ ያን የአባታቸውን ኹኔታ፡ አስቀድመው፡ ከወንድማቸው፥ ወይም፡ ከወንድማቸው ልጅ በመረዳታቸው፡ በነገሩ ተዘጋጅተው፡ ተገቢዉን የጥንቃቄ ተግባር በመፈጸማቸው፡ ያን የመሰለ ምርቃትን ማግኘታቸው ተመዝግቧል።

ታዲያ! ይህ አጻጻፍ፡ በእርግጥ፡ "በትክክለኛ ፍርድ ላይ የተመሠረተ ነው!" ሊባል እንዴት ይቻላል? ከዚህ ይልቅ፡ ይህ ቃል እንዲስተካከል፡ በሰለባዎቹ የሰው ዘሮች፡ የፍትሕ ርትዕ ምንጭ ወደኾነው፡ ወደእውነተኛው መለኮታዊ ዳኛ፡ የይግባኝ አቤቱታ ሲቀርብበት አልኖረምን? ዛሬ ድረስስ እንዲቀርብበት አያስገድድምን? በውኑ፡ ይህ ነገር፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ቀርቶ፡ ደካማ ፍጡር በኾነው፡ ሰብአዊ ዳኛ ዘንድ እንኳ፡ "ይህን የመሰለውን ፍርድ ያስገኛል!" ብሎ የሚያስብ ኅሊና ከቶ ይኖራልን? የሚኖር አይመስለኝም።

ይልቁንም፡ ኖኅ ራሱ፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕያዋን ቅርሶች የኾኑትን ውርሶች የሚያስረክበው፡ ለሴም፥ ወይም ለያፌት ሳይኾን፡ ግንዱ፡ ካም ኾኖ፡ ከሴምና ከያፌት ዘሮች ጭምር፡ የልጅ ልጁ ልጅ ኾኖ ለተወለደውና "አብርሃምን የባረከው፥ አብርሃምም አሥራትን አውጥቶ የሰጠው፡ ይህ ሰው፡ እንዴት ታላቅ እንደኾነ፡ እስኪ ተመልከቱ!" ብሎ፡ ሓዋርያው ለመሰከረለት፥ የእግዚአብሔር ወልድ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ተቀዳሚ አርአያው ለኾነው፡ ለመጀመሪያው መልከ ጼዴቅ መኾኑ የታወቀ ስለኾነ፡ ከዚህ ሰው፡ ቅድመ አያቶች መካከል፡ አንዱ፡ ይህን የመሰለውን እርግማን፡ "በዚህ መልክ ተቀብሏል!" ብሎ ለማመን፡ አዎን! እጅግ ይከብዳል። (ዕብ. ፯፥ ፬።)

ቃሉ ከተጻፈበት ጊዜ አንሥቶ፡ በብሉዩ ዘመን ብቻ ሳይኾን፡ የዓለሙ መድኅን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለመላው የሰው ዘር ቤዛ ኾኖ፡ ፍጡሩን ኹሉ አስተካክሎ ማዳኑ ከታወቀም በኋላ፡ እስከዚች አፍታ ድረስ፡ ከዚሁ፡ ከመዘዘኛው፡ የመጽሓፍ ቃል የተነሣ፡ ሰዎች፡ በሰዎች ላይ የሚፈጽሙት በደልና ግፍ፡ እነሆ፡ አኹንም እንደቀጠለ ይታያል። ይኸውም፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ፡ በምድር ላይ በሚኖሩ ሕዝቦች መካከል፡ በሥውርና በገሃድ የሚካኼደው፡ ጠንቀኛ ድርጊት ነው፤ ይህ ድርጊት፡ እንኳንስ፡ በመልኩ ከመፍጠሩ ጀምሮ፡ እስከሞት ባደረሰው ፍቅሩ፡ ሰውን የወደደውን፡ እግዚአብሔርን ይቅርና፡ ቃሉን ተከትለው፡ አካኼዳቸውን፡ ከእርሱ፡ ከፈጣሪያቸው ጋር ያደረጉትን አማኞቹን፡ እጅግ እያሳዘናቸው ይገኛል።

ጠንቀኛ የተባለውም ድርጊት፡ "የሴምና የያፌት ልጆች ነን!" ብለው፡ የሚተማመኑት፡ ሴማውያን (ቀያዮቹና ቢጫዎቹ፡ ለምሳሌ፡ አይሁድ፥ ዓረቦችና ምሥራቃውያን የእስያ ሰዎች) እና ያፌታውያን (ነጮቹ)፡ "የካምና የከነዓን ዘሮች ናቸው!" ብለው እንደየሃይማኖታቸው፡ በዚህ ደረጃ የመደቧቸውን፥ በቆዳቸው ቀለም፡ ጥቁሮች የኾኑትን ወገኖች፡ በሙሉ፡ ለእርግማኑ ሰለባነት ዳርገዋቸው፥ ጥቁሮቹም፡ ይህንኑ የተሳሳተ አስተሳሰብ፡ በ"ሃይማኖት" ስም፡ በጸጋ ተቀብለውት እነሆ፡ በኹሉም ወገኖች ዘንድ፡ ተቀባይነት አግኝቶና እንደሥርዓት ተደርጎ፡ የሚሠራበት ልማድ ነው።

ለዚህ ብርቱ ጥያቄያችሁ፡ የምሰጣችሁን መልስ የማጠቃልለው፡ እንዲህ በሚለው ቃል ነው፡- በምድር ላይ፡ የየራሳቸውን መንግሥት አቋቁመው የሚኖሩት፡ የዓለም ሕዝቦች ኹሉ፡ በሕግ አወጣጥ፥ አመራርና አፈጻጸም ሥርዓታቸው ረገድ፡ የሚታመንበትን መሠረታዊ አቋም፡ "ታውቁታላችሁ!" ብዬ እገምታለሁ፤

ይኸውም፡- ፩ኛ፡ መመሪያዎቻቸውና ደንቦቻቸው፥ ድንጋጌዎቻቸውና ሌሎቹ ንዑሳን ሕጎቻቸው ኹሉ፡ የሚጸድቁትና የሚጸኑት፡ የኹላቸውም፡ ግንድ፥ ወይም፡ ነቅዕ ከኾነው፡ ሕገ መንግሥታቸው፡ ሠርፀው፥ ወይም፡ መንጭተው መኾኑን፥

፪ኛ፡ እነዚሁ፡ የሕግ ተቀጽላዎች፡ ከዚሁ ሕገ መንግሥት ጋር የማይጣጣሙና የማይስማሙ ኾነው በሚገኙበት ጊዜ ግን፡ እነርሱ፡ ውድቅ ተደርገው ሲሻሩ፡ እርሱ፡ ሕገ መንግሥቱ ብቻ፡ በሌሎቹ ላይ ጸንቶ የመቀጠል ኃይል የሚኖረው መኾኑን ነው።

ስለዚህ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ምንጊዜም ቢኾን፡ ከመጀመሪያው አንሥተን፡ አምነን የተቀበልነውና ስንፈጽመው የኖርነው አሠራር፡ የትኛውን ዓይነት እንደኾነ፡ ከዚህ ውይይታችን ተገንዝባችሁታል፤ ይኸውም፡- <u>ከፍጡር፡ ማለትም፡ ከሰው፡ ኾነ፥ ወይም፡ ከዲያብሎስ፡ የተነገረውንና የተጻፈውንተከትሎ መፈጸም ሳይኾን፡ ፈጣሪያችንና አምላካችን እግዚአብሔር፡ ጥንቱኑ፡ በልባችን የጻፈውን፥ ኋላም፡ ራሱ፡ በሰውነት ተገልጾ፡ በቃሉ በመናገር፥ በተግባርም በመፈጸም፡ ያጸናውን ሕገ መንግሥቱን ብቻ ተከትለን፡ በሥራ ላይ የምናውለው መኾናችን ነው።</u>

ይህ ግንዛቤያችሁ፡ በዚህ ብቻ ሳይወሰን፡ በሌላውም፡ ይህን የመሰለ፡ ግራ የሚያጋባ ኹኔታ በሚያጋጥማችሁ ጊዜ ኹሉ፡ ይህንኑ፡ ከፈጣሪያችሁ፡ በቃል ኪዳን የተሰጣችሁን፥ እናንተም፡ በኢትዮጵያዊነታችሁ፡ በሃይማኖት የተቀበላችሁትን ቋሚ መመሪያ፡ ተከትላችሁ ልትፈጽሙት የሚገባችሁ፡ መኾኑን፡ አበክራችሁ ልታውቁትና ልትሠሩበት ይገባችኋል።" ("ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት! ሦስተኛ መጽሓፍ፤" በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤ ፲፱፻፺፰ ዓ. ም. ገጾች ፪፻፴፩-፪፻፴፰።)

፲፬. በዚሁ ምዕራፍ፡ በገጽ ፵፩ (41)፥ በ፩ኛው አንቀጽ፡ *"የሰው ተፈጥሮዊ እድገት"* በሚለው ንዑስ ርእስ ሥር፡ *"ከዚህ የምንረዳው ነገር* ***ሰው*** *ተሰፋውን በአምላክ ላይ አሳድሮ ለመኖር የሚችልበት የተፈጥሮ ደረጃ ላይ የደረሰው፡ በአብርሀ[ሃ]ም የእ[ዕ]ድሜ ዘመን ላይ መሆ[ኾ]ኑን ነው። ...አብርሀ[ሃ]ም ...በ<u>ሰው</u>ና በአምላክ መካከል ለተዘረጋው የእምነት መስመር ድልድይ መሆ[ኾ]ን ችሏል። ከዚህን ግዜ አንስ[ሥ]ቶም አምላክ ይህን የእምነት ድልድይ በመጠቀም ከ<u>**ሰዎች**</u> ጋር በመንፈስ መቀራረብ ጀመረ። "* የሚለውን የአሳብ ድምዳሜ እዚህ ላይ ያጤኗል።

እንዲሁም፡ በገጽ ፵፪ (42)፥ በ፫ኛው አንቀጽ ላይ፡ *"አምላክ፡ እስከአሪት ዘመን ድረስ የሰይጣን መንፈስ በሰው ሥጋዊ ስሜት ላይ በእጅጉ ሰ[ሠ]ልጥኖ በዓለም ላይ የሰው ክፋት መብዛቱን እያየ እንኳ መንፈሱን በሰዎች ልቦና ውስጥ አሳድሮ ከክፉ ተግባር እንዲታቀቡ ለማሳሰብ አልፈቀደም። ወይንም ደግሞ እውነተኛውን ቃል በመንፈስ ልቦና ላይ ከመዝራት ይልቅ፣ ህ[ሕ]ጉንም ህ[ኅ]ሊና ላይ ከማተም ይልቅ፣ ፍርዱንም በልቦና ዳኝነት ከማሰማት ይልቅ፡ አስቀድሞ የወሰነው፡ ሁ[ኹ]ሉንም ነገር በድንጋይ ላይ ጽፎ፡ በምግዚት በኩል፡ ለሰው ልጆች ሁ[ኹ]ሉ ማሳወቅ ነበር።"* የሚለውን ኃይለ ቃል ልብ ይሏል።

አንተ ኢትዮጵያዊው፡ ይህን የመሰለውን፡ ከባድ አስተሳሰብ፡ በጥናትና በምርምር ከበሰለው አእምሮህ አፍልቀህ፡ በምትሠነዝርበት ጊዜ፡ ጣዖት አምላኪውን አብራምን፡ ለአምልኮተ እግዚአብሔርና ለኪዳነ ግዝረት ያበቃውን፡ **"የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን"** የተባለውን **"መልከ ጼዴቅ"** እና እርሱን የመሰሉትን፡ የቅዱሱ ኪዳን ባለአደራ ወራሾች የኾኑት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እንዴት ሳታስባቸውና ሳታስታውሳቸው ቀረህ? ይህን እውነታ፡ እኔ፡ በመጻሕፍቴ ውስጥ፡ በስፋትና በጥልቀት ያተትኩበት በመኾኔ፡ በማንበብ ካወቅኸው፡ ከአንተ፡ ይህ መጽሓፋዊ አገላለጽ፡ በዚህ መልክ ሲሠነዘር፡ እነርሱን፡ ከህልውና ውጭ አድርጎ፡ እንዳልነበሩ የሚያስቆጥራቸው አይኾንምን? እጅግ ይገርማል!

ስለዚህ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት እምነታችን በኩል፡ ያለውን እግዚአብሔራዊ እውነታ መሠረት በማድረግ፡ ከላይ በሠፈረው፡ በመጽሓፍህ ጥቅስ ውስጥ፡ "<u>ሰው</u>" እና "<u>ሰዎች</u>" በሚሉት፡ በተሠመረባቸው ቃላት ቦታ፡ ሊተካ የሚገባው፡ **"በጣዖት አምላኪነቱ፡ 'አረማዊ'፥ ወይም፡ 'አሕዛብ' የተባለው/በተባለው/ከተባለው፡ የሰው ዘር ወገን"** የሚለው፡ የዐረፍተ ነገር ሐረግ መኾኑን ላመለክትህ እወድዳለሁ።

፲፰. በዚሁ ምዕራፍ፤ በገጽ፡ ፵፩ (41)፥ በ፫ኛው አንቀጽ፡ *"ይህ እምነት ሊመሰ[ሠ]ረት የበቃው ሣራ መካን ሳ[ሣ]ለች አብርሀ[ሃ]ም ግን ዘሩ እንደሚበዛለት ከአምላክ የተሰጠውን ተስፋ በማመኑ ብቻ ነበር። ነገር ግን በእርሱ በኩል የተገኘው እምነት የጸና መሆ[ኾ]ኑ ሊረጋገጥ የቻለው፡ተስፋው ሰ[ሠ]ምሮለት ከአጋር ያገኘውን የበኵር ልጁን መስ[ሥ]ዋእ[ዕ]ት ያደርግ ዘንድ በታዘዘ ግዜ ነው።"* ተብሏል።

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት እምነታችን፡ ተቀብሎ ያጸናው እውነት፡ እንዲህ ተብሎ የሠፈረውን፡ ይኼን የመሰለውን አስተሳሰብ ሳይኾን፡ "**አብርሃም፡ ከሣራ፡ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ያገኘውን ልጁን ይስሐቅን፡ መሥዋዕት ያደርግ ዘንድ፡ በታዘዘ ጊዜ ነው።**" የሚለውን መኾኑን በመግለጽ፡ አብርሃምና ሣራ፡ የቤት አገልጋያቸውን አጋርን በሚመለከት ስለፈጸሙት ድርጊታቸው፡ እምነታችን፡ ያለውን፡ የእውነት አቋም፡ እዚህ ላይ ማውሳቱን አግባብ ኾኖ አግኝቼዋለሁ። ይህም፡ እንደሚከተለው ነው፡-

የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች፡ በህልውናቸው ዘመን ኹሉ፡ ቅድሚያንና ብልጫን የሚሰጡት፡ በተፈጠሩበት፡ የእግዚአብሔር መልካቸው፡ ይኖሩበት ዘንድ፡ በቃል ኪዳን የተሰጣቸውን መለኮታዊ ሥርዓትና በየልቦናቸው ላይ የተጻፈውን፡ የእግዚአብሔርን ቃል በመኾኑ፡ የሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት መጀመሪያና መሠረት የኾነውን፡ የጋብቻን፥ ይኸውም፡ የአዳምንና የሔዋንን ቃል ኪዳን፡ ምንጊዜም አክብረው በመፈጸም ይገኛሉ።

ይኹን እንጂ፡ ከኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ፡ ስለእግዚአብሔርና ስለአምልኮቱ ተምሮና አውቆ፡ ለእውነተኛው የኢትዮጵያዊነት እምነት፥ ለግርዛት ቃል ኪዳንም የበቃው አብርሃም፡ በዚሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱ ጸንቶ፡ ከፈጣሪው የተሰጠውን የተስፋ ቃል፡ በትዕግሥት መጠበቅ ሲገባው፡ አዳምን እንዳሳተችው እንደሔዋን፡ እርሱም፡ በሚስቱ፡ በሣራ አሳብና ፍላጎት ተመርቶና ተሸንፎ፡ የእግዚአብሔር የኾነውን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱን እምነታዊ ሥርዓት አፈረሰ፤ ከአጋርም፡ እስማኤልን ወለደ።

ከአዳምና ሔዋን አንሥቶ፡ እስከዛሬ፡ ምንጊዜም ቢኾን፡ የእግዚአብሔርን ቃል መተላለፍ፥ ሥርዓቱንም አለማክበር፡ በራስ ላይ የሚያስከትለው፡ ጽኑ ጉዳትንና ጥፋትን በመኾኑ፡ እነሆ፡ አብርሃምና ሣራም፡ ያን፡ የእግዚአብሔር የኾነውን፡ የጋብቻ ቃል ኪዳን አፍርሰው፡ በአጋር አማካይነት የፈጸሙት ኃጢአት፡ ፍዳው፡ በእነርሱና በመካከላቸው የተነሣሣውን ፀብ ክርክር ብቻ ሳይኾን፡ ጠንቁ፡ ወደልጆቻቸውና ወደልጅ ልጆቻቸው፥ ከዚያም፡ ወደዘርማንዘራቸው እየተላለፈ ሲወርድ ሲዋረድ፡ ዛሬ በገሃድ እስከሚታየው፡ የእርስ በርስ ፍጅትና እልቂት ይኸው ደርሶ ይገኛል።

፲፮. በምዕራፍ አራት፡ በገጽ ፵፮ (46)፥ በ፪ኛው አንቀጽ ውስጥ፡ *"የሚጠፋውና ብስባሽ የኾነው ሥጋ ዘር የማይጠፋና የማይበሰብስ መንፈሳዊ ዘር ሆ[ኾ]ኖ ሳይታደስ ከሚጠፋና ብስባሽ ከኾነው ዘር የተገኘ ፍሬ የማይጠፋና የማይበሰብስ መንፈሳዊ ፍሬ ሆ[ኾ]ኖ ይታደሳል ማለት ዘበት ነው።"* የሚለው ልዩ ቃል፡ እንዲህ ይተቻል፡-

በነገረ ቀደም፡ እግዚአብሔር፡ ከባሕርዩ አስገኝቶ የፈጠራቸው፡ መንፈስና ነፍስ ብቻ ሳይኾኑ፡ ሥጋና የሥነ ፍጥረት አባላት የኾኑት ነገሮች ኹሉ ጭምር፡ እንደራሱ፡ እንደፈጣሪ ባሕርይ፡ ጨርሰው የማይጠፉ መኾናቸውን፡ መንፈስንና ነፍስን ትተን፡ ሥጋን ብቻ እንኳ፡ ራሱን፡ ከግዑዛን ባሕርያቱ ጋር ምስክር እናደርገዋለን።

ለምሳሌ፡ የሥጋ ባሕርያት የኾኑትን፡ አፈርን (ማዕድናትን)፥ ውኃን፥ ነፋስንና እሳትን ብንወስድ፡ የመጀመሪያ ኵነት የኾነው አፈር፡ በቅድሚያ፡ ወደውኃነት፥ ቀጥሎ፡ ወደነፋስነት፥ በመጨረሻ፡ ወደእሳትነት ይለወጣል፤ ይህም ማለት፡ የመጨረሻው እሳት፡ ረቂቅ ኃይል ይኾንና፡ ወደራሱ ጥንተ-ማንነት ተመልሶ መጥቶ፡ አፈርነቱን ሲያቃጥለው፡ አፈር (ማዕድኑ) ቀልጦ፡ ይፈስሳል፡ ማለትም፡ ውኃ ይኾናል፤ እሳቱ፡ አኹንም፡ ያን ፈሳሽ ሲለበልበው፡ ይተንና ወደጭስነት፥ ወይም፡ ወደእንፋሎትነት ይለወጣል፤ ማለትም፡ አየር፥ ወይም፡ ነፋስ ይኾንና፡ ወደላይ ያርጋል፤ እሳቱ፡ እንደገና አይሎ አየሩን ሲያነድደው፡ ያ ነፋስ፡ ራሱ፡ ወደእሳትነት ይቀየርና፡ የመጨረሻው ኃይል ኾኖ፡ ወደመጀመሪያ ማንነቱ፡ ማለትም፡ ወደአፈርነቱ፡ በተዋሕዶ ይመለሳል እንጂ፡ ጨርሶ አይጠፋም።

ስለዚህ፡ እነዚህ አራት ባሕርያት ያሉት ሥጋ፡ ጠባያቱንና አካሉን፡ በእነዚሁ አራት ባሕርያት፡ ማለትም፡ ከግዙፍነት፡ ወደፈሳሽነት፥ ከዚያ፡ ወደረቂቅነት፥ በፍጻሜውም፡ ወደኃይልነት በመለዋወጥ፡ ህልውናውን ይቀጥላል እንጂ፡ ወደአለመኖር እንደማይዳረግ የታወቀ ነው።

እንዲሁ ኹሉ፡ ከወንድ አብራክ የሚወጣው የሥጋ ነፍሳዊ ዘር፡ ከሴት ማሕፀን፡ የሥጋ ነፍሳዊ እርሻ ላይ ወድቆ፡ በለሰለሰ ማሳ ላይ ተዘርቶና ማስኖ፡ እንደገና በአዲስ ሕይወት እንደሚበቅል የእህል ዘር፡ በስብሶና ጠፍቶ የማይቀር፡ሕያው የኾነ፡ ሰብአዊ ፍጡር ይፀነሳል!

፲፯. በዚሁ ምዕራፍ፥ በገጽ ፵፮ (46)፥ አንቀጽ ፬ እና ገጽ ፵፯ (47)፥ አንቀጽ ፩ ላይ፡ *"አዳም በፊተኛነቱ ህ[ሕ]ያውነትን በነፍስ ብቻ የተሞላ ነበረ። ይህ ሁ[ኹ]ኔታ ደግሞ ለግዜአዊው ምድራዊ ህ[ሕ]ይወት ብቻ የሚያበቃ እንጅ ለዘለዓለማዊው ሰማያዊ ህ[ሕ]ይወት የሚያደርስ አልነበረም። ዘሩ በዚህ ደረጃ ላይ ተወስኖ ነበር ማለት ደግሞ ከዘሩ የተገኘ ፍሬ ሁ[ኹ]ሉ ህ[ሕ]ያውነቱ በምድራዊ ህ[ሕ]ይወት ላይ ብቻ ተወስኖ የነበረ ነው ማለት ነው።"* በሚለው አንድምታ ላይ መተቸት ግድ ይኾናል። ይህንም ትችት፡ እንዲህ በሚል አጭር ቃል እገልጸዋለሁ፡-

በመሠረቱ፡ ሰው፡ ገና ከመጀመሪያው፡ በፈጣሪው መልክ በመፈጠሩ፥ ከዚያም፡ የዕፀ-በለስን ፍሬ ከመብላቱ የተነሣ፡ በዚሁ ፈጣሪው አንደበት፡ እንደእርሱ፡ እንደፈጣሪው የመኾኑ ብቅዓት፡ ተረጋግጦ በመነገሩ፡ በሥጋም፥ በነፍስም፥ በመንፈስም፡ ከፍጹምነት የአምላክነት ደረጃ የደረሰና የመጨረሻውን፡ የክብር አክሊል የተቀዳጀ መኾኑ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ በእምነት የተቀበሉትና ያጸኑት እውነታ ነው።

ይህ በመኾኑ ነው እኮ፡ ስማቸው፡ ከላይ የተጠቀሱት፡ ሞት ሊቀርባቸው ያልቻሉት እነሄኖክና እነኤልያስ፥ ደግሞም፡ እየራሳቸውን፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌነት ያበቁትን መልከ ጼዴቆች፥ ከሴቶች መካከል፡ በነፍሳዊ ኅሊናዋና በሥጋዊ ንጽሕናዋ፡ በተፈጠረችበት የእግዚአብሔር መልኳ፡ ፍጹም ጸንታ በመገኘቷ፡ እግዚአብሔር ወልድን የወለደች፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፥ እንዲሁም፡ እንደእነርሱ ያሉት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በምድርና በሥጋ የኖሩት።

ኢየሱስ ክርስቶስም፡ የመጣው፡ ለይቶ፡ የእሥራኤል ቤት የኾኑትን፡ የጠፉትን በጎች ለማዳን መኾኑን፡ በመኮታዊ አንደበቱ ከገለጸ፡ ሌሎች ያልጠፉ መኖራቸውን፥ የቤዛነት ደሙንም የሚያፈስሰው፡ ስለብዙዎች ኃጢአት ማስተስረያ መኾኑን ከመሰከረ፡ ያ ስርየት ያላስፈላጋቸው፡ ጥቂቶች፡ የበቁ መኖራቸውን ማረጋገጡ መኾኑ ሊታበል አይቻልም። እነዚህም፡ ባለቅኔው፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመልቶ፡ "አንሰ እቤ፡ **'አማልክት አንትሙ፤ ወደቂቀ ልዑል ኵልክሙ!'"** ማለትም፡ **"እኔ ግን፡ 'እናንተ አማልክት ናችሁ፤ የልዑል እግዚአብሔርም ልጆች ናችሁ!' አልሁ።"** ብሎ የዘመረላቸው ናቸው። (መዝ. ፹፩፥ ፯።)

መሢሕ፡ አዳም፥ አዳምም፡ መሢሕ ከኾነ፡ አዳምን የፈጠረና "የዕፀ-በለስን ፍሬ አትብላ!" ያለው ማን ሊኾን ነው? "አትብላ!" የተባለውስ ፍጡር፡ ማን ሊኾን ነው? ፈጣሪና ፍጡር ተብለው፡ በኹለትነት ካልተመደቡ በቀር፡ ያው አንዱ መሢሕ፡ ራሱ፡ በአንድ ወገን፡ ሕግ አውጪና ትእዛዝ ሰጪ፥ በሌላ ወገን ደግሞ፡ ትእዛዝ ተቀባይና ሕግ አፍራሽ ከኾነ፥ በቅዱሳት መጻሕፍት፡ በግልጽ ተጽፎ የሚነበበውን፡ የኹለቱን ማንነት፡ እንዴት አድርጎ መግለጽና አግዝፎ ማቅረብ ይቻላል? በአንድ ጊዜ፡ ራሱ ፈጣሪና ራሱ አጥፊ፥ ራሱ ቀጪና ራሱ ተቀጪ መኾንስ እንደምን ይቻላል?

በዚህ ረገድ፡ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ እምነታችን የሚያስገነዝበን፡ የመጀመሪያው ሰው የኾነው አዳም፡ የፈጠረው እግዚአብሔር ወልድ፡ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ፡ 'አትብላ!' ያለውን መለኮታዊ መመሪያ ተቀብሎና አምኖ፥ መርጦና ፈልጎ መፈጸም ሲችል፡ ያን ማድረጉን ትቶ፡ የክፋት ፊታውራሪ ከኾነውና "ሰይጣን" ከተባለው ርኩስ መንፈስ ጋር ወግኖ፡ በፈጣሪው ላይ ባመፀና በራሱ ላይ ጥፋትን፥ ኃጢአትና ሞትን ማምጣቱን ነው።

ከዚያም፡ ይኸው ፈጣሪው፡ በርኅራኄውና በመሓሪነቱ፥ በቸርነቱና በምሕረቱ፡ የዚህኑ፡ የራሱ ሥራ የኾነውንና ጥፋት የፈጸመውን፡ የፍጡሩን ሰውነት፡ በተዋሕዶ ወርሶና በዚያ ማንነት፡ ወደምድር ወርዶ፡ በቤዛነት ያዳነው፤ ወደቀደመ ክብሩም፡ የመለሰው መኾኑን ነው።

እግዚአብሔር ወልድ፡ "የሰው ልጅ" ተብሎና መሢሕ ኢየሱስ ኾኖ፡ ወደዚህ ዓለም የመጣው፡ ጥፉ ፍጥረቱን፡ እንዲህ፡ በቤዛነት ለማዳን ብቻ ሳይኾን፡ ሰብአዊው ፍጡር፡ ገና ከመጀመሪያው አንሥቶ፡ በገዛ ፍላጎቱና ምርጫው፡ ያመጣውን ታላቅ ውድቀት፡ እንዳይደርስ አድርጎ፡ በዚያ፡ ጥንቱኑ በተፈጠረበት፡ የፈጣሪ መልኩ፥ ደግሞም፡ ክፉና ደጉን፡ ለይቶ አውቆ፡ በተቀዳጀው፡ በዚያ ብቅዓቱ መቀጠል ይቻለው የነበረ መኾኑን፥ ዛሬም የሚቻለው መኾኑን ጭምር፡ በዘመኑ ለነበረውና ከዚያ ለተከታተለው የሰው ትውልድ ኹሉ፡ ለማሳየትና በአርአያነት ለማስታማር መኾኑ፡ በድርጊቱ ታይቷል፤ ተረጋግጧልም።

፲፰. በዚሁ ምዕራፍ፡ *"መሢሕ አዳም ስለመኾኑ የሚያረጋግጡ በቂ መረጃዎች"* በሚለው ንዑስ ርእስ ሥር፡ በገጽ ፵፯ (47) ላይ፡ *"መሢሕ ስለአዳምነቱ በራሱ አንደበት ከሰጠው የምስክርነት ቃል ብንነሣ ...አምላክ የፈጠረው፡ የመጀመሪያው ሰው እርሱ መሆ[ኾ]ኑን፣ አስቀድሞ ሞቶ የነበረው በፍጻሜውም ህ[ሕ]ያው የሆ[ኾ]ነው እርሱ እንደሆ[ኾ]ነ ገልጾ ለሰው ፍጥረት ሁ[ኹ]ሉ ፊተኛውና ኋለኛው እኔ ነኝ በማለት ስለእራሱ ማንነት ራሱ መስክሮአል።"* የሚለውና ከዚሁ አገላለጽ ጋር ዐብረው የተጠቀሱት ማስረጃዎች የሚናገሩት፡ የመጀመሪያውን አዳምና "ኹለተኛው አዳም" የሚል ስያሜ ተሰጥቶት፡ የተዋሓደውን ፍጹም ሰውነት ስለፈጠረው፡ ስለመለኮትና ይኸው የእግዚአብሔር ልጅና ቃል፡ በተዋሓደው ሰውነቱ ስለገለጸው የማንነቱ እውነታ እንጂ፡ እርሱ ስለፈጠረው፡ ስለመጀመሪያው አዳም አለመኾኑ፡ ተለይቶ መታወቅ አለበት።

"ቃል ሥጋ ኾነ!" በሚለው፡ በዮሓንስ የምሥራች ጽሑፍ መሠረት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው መኾኑን፡ ምንጊዜም ባለመዘንጋት፡ በተዋሕዶ የከበረው፡ ያው አንዱ መሢሕ ኢየሱስ፡ ባሰበውና በተናገረው፥ ባደረገውም ኹሉ፡ የመለኮታዊ አካሉንና ባሕርዩን ሥራ፡ በተዋሓደው አዳማዊ አካሉና ባሕርዩ፥ የአዳማዊ አካሉንና ባሕርዩን ሥራ ደግሞ፡ በመለኮታዊ አካሉና ባሕርዩ የፈጸመ መኾኑን አምኖ በምግባር መግለጥ እንጂ፡ የተዋሕዶ ምሥጢርን፡ እንዲህ ማምታታትና ማመሠቃቀል አይገባም፤ አያስፈልግምም። ራሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ቀድሞም ነቢያቱ፥ ኋላም ሓዋርያቱ በተናገሩት ቃል ያስተላለፉት መልእክት ትክክለኛ ትርጉሙ፡ በዚህ እውነታ ላይ የተመሠረተው መኾኑን ማስተባበል ከቶ አይቻልም።

ከዚህ የተነሣም፡ በገጽ ፵፱ (49)፥ በአንቀጽ ፩ እና በገጽ ፶፥ አንቀጽ ፫ ላይ፡ *"ሐዋርያው ጳውሎስ፡ ...ለምሳሌ ወደ ኤፌሶን በላከው ሁ[ኹ]ለተኛ መልእክቱ ላይ ...በአዳምነቱ ወርዶ የሞተውና በመሢሕነቱ ወደሰማይ ያረገው ሰው አንድ መሆ[ኾ]ኑን ለማስረዳት ሞክሯል።"* ደግሞም፡ *"የአዳም ብልሹ ሥጋ ይወገድ ዘንድ አምላክ በጥበብ ወደ ምድር አወረደው መልሶም አምላክ ያንኑ አዳም እንደወደደ መሢሕ አድርጎ ፈጸመው"* ተብሎ የተጻፈው ቃል፡ ራሱ፡ መለኮት የኾነው እግዚአብሔር ወልድ፡ እርሱም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከፍጹም አምላክነቱ ጋር፡ በተዋሕዶ አንድ ባደረገው፡ በአዳማዊው ፍጹም ሰውነቱ የፈጸመው መኾኑን መገንዘብ ይገባል።

እንዲሁም፡ በገጽ ፵፱ (49)፥ በአንቀጽ ፫ ላይ፡ *"ልደትን አስመልክቶ መሢሕ እራሱም ቢሆ[ኾ]ን በዳግም ልደቱ በክብር ዙፋን ላይ እንደሚቀመጥ መስክሯል። ዳግም ሲል ታዲያ ምን ማለቱ ነው?"* ለሚለው መጠይቃዊ አስተያየት፡ መልሱ፡ በመጽሓፉ ውስጥ የሠፈረው ቃል ሳይኾን፡ "በተዋሕዶ የከበረውና ከኹለት አካላት፡ አንድ አካል፥ ከኹለት ባሕርያት፡ አንድ ባሕርይ የኾነው የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ልደትማ፡ በሥጋ፡ ማለትም፡ በአዳማዊው ፍጹም ሰውነት፡ ከቅድስት እናቱ፡ ከድንግል ማርያም፡ ያለአባት፡ ማለትም፡ ያለሰብአዊው የወንድ ዘር የተወደለበት ልደት ነው!" የሚል መኾኑን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት እምነታችን ያረጋግጥልናል፤ ከመለኮታዊው የባሕርይ አባቱ፡ ከእግዚአብሔር አብ፡ ከፍጥረተ ዓለማቱ በፊት፡ ያለእናት የተወለደበት ልደቱ፡ የመጀመሪያውና አንደኛው ኾኖ ማለት ነው።

አለዚያ፡ በመጽሓፍህ ውስጥ የተሠነዘረው አባባል፡ *"አምላክ የፈጠረው፡ የመጀመሪያው ሰው፡ እርሱ ራሱ፡ መሢሕ ነው!"* ማለትም፡ እኛ፡ "'አዳም' የተባለውን፡ የመጀመሪያውን ሰው የፈጠረውና 'እግዚአብሔር ወልድ' የምንለው ነው!" የሚል አንድምታ ያለው ከኾነ፡ ፈጣሪ የኾነውን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ "ፍጡር ነው!" ያለውን አርዮስን በመምሰል፡ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ እምነታችንን መሠረታዊ አቋም ሊያቃውስ የሚቃጣ ሥንዛሬ ስለኾነ፥ ይህንኑ የተሳሳተ ዘይቤ፡ በማያወላውል ቍርጠኝነት ፈጽመን የምናስተሓቅረው መኾኑን፡ ማስታወቅ ግድ ይኾንብኛል።

ይህን ርእሰ ነገር በሚመለከት፡ ቀደም ባሉት ገጾችና ዓምዶች ላይ የሚበቃ ሐተታ ስለተሰጠበት፡ እዚህ ላይ፡ እንደገና ማብራራቱ አስፈላጊ አይኾንም።

፲፱. በዚሁ ምዕራፍ፥ በገጽ ፶፩ (51)፡ *"መሢሕ በአዳምነቱ ሞተ እንጂ በመሢሕነቱ አልሞተም"* በሚለው ንዑስ ርእስ ሥር፡ በአንቀጽ ፩ እና ፪ ላይ፥ እንዲሁም፡ በገጽ ፶፫ (53)፥ አንቀጽ ፩ ላይ፡ *"አስቀድሞ ፍጥረታዊና ሥጋዊ የአጥንት ዘር ሆ[ኾ]ኖ ሳ[ሣ]ለ በአዳማዊነቱ ሞተ እንጂ መንፈሳዊና መለኮታዊ ዘር ከሆ[ኾ]ነ በኋላ በመሢሕነቱ አልሞተም። ...ሳይሞት ሞትን ድል ነስቶ ተነሳ[ሣ] እንጅ ለሞት እጅ ሰቶ ፍጹም ከሞተ በኋላ አልተነሳ[ሣ]ም። በእርግጥ አይሁዶች ሊገድሉት ብለው ደብድበውታል ሰቅለውትማል። ነገር ግን ...የሰቀሉት የመሢሕነቱን መንፈስ በተጨባጭ አግኝተውት ሳይሆ[ኾ]ን የመሢሕነቱ አካል በሀ[ሓ]ሳብ ተመስሎባቸው ነው። ...ስለዚህ መሢሕ በአዳምነቱ ሞተ እንጅ አዳም በመሢሕነቱ አልሞተም።"* የሚለው አገላለጽ፡ ከላይ ከተሰጠው የእምነታችን አተረጓጎም ስለተለየ፡ ማስተካከሉ አስፈላጊ ይኾናል።

ይኸውም፡ **"ሞተ በሥጋ፤ ወሐይወ በመንፈስ!"** በሚለው፡ በመጽሐፍ ቃል መሠረት፡ መለኮታዊው አምላክ የኾነውና በዚህ ባሕርዩ የማይሞተው እግዚአብሔር ወልድ፡ በተዋሐደው አዳማዊ ሰውነቱ ሞቶ፡ ሟች የኾነውን አዳማዊዉን ሰውነት፡ በመንፈስ ሕያው አደረገው!" የሚለውን የእምነታችንን ይትበሃል እንዲከተል በማድረግ ነው። (፩ጴጥ. ፫፥ ፲፰።)

፳. በዚሁ ምዕራፍ፡ *"ከአምላክ እንደአምላክ ኾኖ መፈጠር ማለት ምን ማለት ነው?"* በሚለው ንዑስ ርእስ ሥር፡ በገጽ ፶፬ (54)፥ አንቀጽ ፫ ላይ፡ የመሢሕ ኢየሱስን፡ *"የተወጋውን ቁስል በዓይኑ ማየት ተስኖት፡ በእጁ ዳሶ ማመኑ"* የተባለው፡ "ቶማስ"፡ *"በእጁ ዳሶ ማመኑ"* የሚለው ኃይለ ቃል፡ እዚያው: እምሥራቹ መጽሐፍ ውስጥ፡ ከሙታን ተለይቶ የተነሣው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ መግደላዊት ማርያምን፡ **"ኢትልክፍኒ፡ እስመ ዓዲ ኢዐረግሁ ኀበ አቡየ!"** ማለትም፡ **"ገና ወደአባቴ አላረግሁምና፡ አትንኪኝ!"** ካላት መለኮታዊ ቃል ጋር አይስማማም። "ያ፡ ተሰቅሎና ሞቶ፥ ተገንዞና ተቀብሮ የነበረው ኢየሱስ ክርስቶስ እኮ፡ ይኸውልህ፡ በሦስተኛው ቀን ተነሣ!" ተብሎ፡ በወንድሞቹ ሐዋርያት የተነገረውን ምሥራች፡ አምኖ ለመቀበል የተሳነው ቶማስ፡ በዚሁ ረገድ ተናግሮ ካደረገውም ጋር የሚቃረን ኾኖ ይገኛል።

ምክንያቱም፡ **"የተቸነከሩ እጆቹንና እግሮቹን፡ ካላየሁ፥ ጣቶቼን፡ በእነዚያ የችንካር ምልክቶች ውስጥ ካልጨመርሁ፥ እጄንም፡ በተወጋ ጎኑ ውስጥ ካላገባሁ በቀር፡ አላምንም!"** ያለውን ቃሉን ይፈጽም ዘንድ፡ ራሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሳምንቱ ተገልጾለት በጋበዘው ጊዜ፡ ቶማስ፡ የሰጠው መልስና ያሳየው ጸጸት፡ ይህን እውነታ ያረጋግጣል። ይኸም፡ **"ወአውሥአ ቶማስ ወይቤሎ፡ 'እግዚእየ! ወአምላኪየ!' ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ፡ 'እስመ ርኢከኒሁ አመንከኒ። ብፁዓንሰ፡ እለ እንዘ ኢይሬእዩኒ የአምኑኒ። "** ማለትም፡ **"ቶማስም፡ 'ጌታዬ! አምላኬም!' ሲል መለሰለት። ጌታችን ኢየሱስም፡ 'አንተ፡ ስላየኸኝ፡ አመንክብኝ፤ ብፁዓንስ፡ ሳያዩኝ የሚያምኑብኝ ናቸው!' አለው።"** በሚሉት ቃላት ይታወቃል። (ዮሐ. ፳፥ ፲፯-፳፱።)

እነዚህ ቃላት፡ ቶማስ፡ ባለማመኑ፡ በራሱ አነጋገርና ሥራ ዐፍሮና ፈርቶ፥ ደንግጦና አጎንብሶ፡ ያን መልስ ሰጠ እንጂ፡ እንደተናገረው "ላድርግ!" ብሎ አልደፈረም፤ የምሥራቹ ጸሓፊም፡ ቶማስ የተናገረውን መፈጸሙን አልዘገበም፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም፡ "ስላየኸኝ" አለ እንጂ፡ "ይኸው እንደፈለግኸው፡ ዳስሰኸኝ ስላረጋገጥህ፡ አመንክብኝ!" አላለም። ስለዚህ፡ በትንሣኤ ዘጉባኤ ጊዜ፡ እርሱን መስለው ለሚነሡት አማኞቹ፡ በኵር የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በተዋሓደው አዳማዊ ሰውነቱ፡ የለበሰውን፡ ያንን የትንሣኤ አካሉን፡ ገና በሥጋና በደም ህልውና ተወስኖ የሚኖር ሰብአዊ ፍጡር ሊነካው እንደማይችል፡ የእምነታችን እውነታ ነው።

፳፩. በዚሁ ምዕራፍ፡ *"ከሥላሴዎቹ አንዱ ተፈጣሪ እንጅ ፈጣሪ አይደለም፤ አንዱ ሰ[ሠ]ራጺ እንጅ አስ[ሥ]ራጺ አይደለም"* በሚለው ንዑስ ርእስ ሥር፡ በገጽ ፶፭ (55)፥ አንቀጽ ፫፥ በገጽ ፶፮ (56)፥ አንቀጾች ፩-፫ ላይ፡ ስለመሢሕ፡ ራሱ፡ ንዑስ ርእሱ በግልጽ ከሚከሥተው መሠረታዊ ልዩነት ጋር፡ በትርጓሜ አንድምታ የተሰጠውን ሓተታ በማጠቃለል፡ *"በአጭሩ መሢሕ እራሱ እግዚአብሄ[ሔ]ር ነው ማለት አይደለም። ...በመጽሓፍ ቅዱስ ውስጥ ሥላሤ[ሴ] የሚል ስያሜ ከሌለ ደግሞ ሥላሤ[ሴ] የአበዎች ተረት ነው ማለት ነው። ..."* የሚለው የሓሳብ ሥንዛሬ፡ የእምነታችንን መሠረትና አቅዋም፡ ፈጽሞ የሚፃረር በመኾኑ፡ ተጣርቶና ተስተካክሎ፡ እንደሚከተለው፡ ሊታረም የሚገባው ነው።

ስለእግዚአብሔር፡ የአንድነትና የሦስትነት ህልውና ምሥጢር የሚገልጸውና የሚያስረዳው፥ ትርጉሙም ይኸው የኾነው፡ "ሥላሴ" የሚለው ቃል፡ በመጽሓፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሌለ፡ ስለዚሁ ምሥጢር፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ዘንድ ያለውን እውነታ አይለውጠውም፤ ይኼም፡ የእነርሱ መጽሓፍ፡ ሰዎች፡ ያዘጋጁትና የጻፉት፥ አልፎ አልፎ፡ ግድፈቶችንና ስሕተቶችን፥ ጉድለቶችንና ጥፋቶችን የያዘው፡ የማሰነው ጥራዝ ሳይኾን፡ ራሱ ፈጣሪ ያዘጋጀው፡ የየራሳቸው ሰውነታቸው በመኾኑ ነው።

ሰዎች በጻፉት መጽሓፍ ውስጥም ቢኾን፡ ይህንኑ የሥላሴን ምሥጢር የሚያመላክቱ ፍንጮች ተጽፈው ይነበባሉ፤ ለምሳሌ፡ "ናሁ አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ!" ማለትም፡ "እነሆ አዳም፡ ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" ደግሞም፤ **"ወአስተርአዮ እግዚአብሔር ለአብርሃም፤ ...ወሶበ አልዐለ አዕይንቲሁ፡ ነጸረ፤ ወናሁ ሠለስተ ዕደው፡ ይቀውሙ መልዕልቴሁ። ...ወይቤሎ፡ 'እግዚአ! እመ ረከብኩ ሞገሰ በቅድመ አዕይንቲከ፡ ኢትኅልፍ እምገብርከ። ናምጽእ ለክሙ ማየ፤ ወንጽሕብ እገሪክሙ!'"** ማለትም፡ **"እግዚአብሔር፡ ለአብርሃም ተገለጠለት፤ ...ዓይኑንም አንሥቶ ተመለከተ፤ እነሆ፡ ሦስት ሰዎች፡ በፊቱ ቆመው ነበር። ...እንዲህም አለው፡- 'አቤቱ፡ በፊትህ፡ ባለሟልነትን አግኝቼ እንደኾነ፡ አገልጋይህን አትለፈኝ! ውኃ አምጥተንላችሁ፡ እግራችሁን እንጠባችሁ!'"**

እንዲሁም፡ "ርኢክዎ ለእግዚአብሔር ጸባኦት፡ እንዘ ይነብር ዲበ መንበሩ ልዑል፤ ወነዋኅ፤ ወምሉእ ቤተ ስብሓቲሁ፤ ወሱራፌል ይቀውሙ ዓውዶ፤ ...ወይብሉ፡ 'ቅዱስ! ቅዱስ! ቅዱስ! እግዚአብሔር ጸባኦት! ፍጹም ምሉእ ሰማያተ ወምድረ! ቅድሳተ ስብሓቲከ!" ማለትም፡ "አሸናፊ እግዚአብሔር፡ በምስጋና ክብሩ በተመላ አዳራሹ ውስጥ በተዘረጋው ታላቅና ከፍ ያለ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ፡ ሱራፌልም፡ ዙርያውን ከብበውት አየሁት። ...እነርሱም፡ 'ፍጹም አሸናፊ የምትኾን እግዚአብሔር! ‹ቅዱስ! ቅዱስ! ቅዱስ!› ተብለህ የምትመሰገነው ምስጋናህ፡ በምድርና በሰማይ የመላ ነው!' እያሉ ያመሰግኑሃል።" የሚሉት ይገኙባቸዋል። (ዘፍጥ. ፫፥ ፳፪፤ ፲፰፥ ፩-፲፮። ኢሳ. ፮፥ ፩-፫።)

ይህ የእግዚአብሔር ማንነት፥ የአንድነቱና የሦስትነቱም ምሥጢር፡ በይበልጥ ጠርቶ፡ በትክክል ሊታወቅ፥ በድምፅ ሊሰሰማና ገዝፎም ሊታይ የተቻለው፡ ከመለኮታዊ አብነቱ፡ በመለኮታዊ ልጅነት የተወለደው "እግዚአብሔር ወልድ" ወይም፡ "የእግዚአብሔር ልጅ"፡ "ቃል" ተብሎ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሰውነት ተጸንሶ ከተወለደ በኋላ ነው።

አዎን! በተጸነሰ ጊዜ፡ በሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ምስክርነት፥ በበረት በተወለደ ጊዜ፡ በመላእክት ሠራዊትና በእረኞች ምስክርነት፥ በዮርዳኖስ ወንዝ በተጠመቀ ጊዜ፡ በአጥማቂው ዮሓንስ ምስክርነት፥ በግርማ መለኮቱ፡ በደብረ ታቦር በተገለጸ ጊዜ ደግሞ፡ በሓዋርያቱ፡ በነቅዱስ ጴጥሮስ ምስክርነት የታየውና የተሰማው፡ የአንዱ እግዚአብሔር፡ የአብነት፣ የወልድነትና የመንፈስ ቅዱስነት ገጽታና ድምፅ፡ የሥላሴን ምሥጢር ምንነትና ማንነት ገሃድ አድርጎታል።

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከስቅለቱና ከሞቱ፥ ከትንሣኤውም በፊትና በኋላ፡ ስለዚሁ ምሥጢር፡ ለደቀ መዛሙርቱ፡ በስፋትና በምልዓት፥ በጥልቀትና በምጥቀት በሚያስተምራቸው ጊዜ፡ ከተናገራቸው ከብዙዎቹ ቅዱሳት ቃላት ጋር፡ "ወቀርበ እግዚእ ኢየሱስ፤ ወተናገሮሙ እንዘ ይብል፡- 'ሑሩ! ወመሀሩ ኵሎ አሕዛበ! ወእንዘ ታጠምቅዎሙ፡ በሉ! ‹በስመ አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ!›" ማለትም፡ "ጌታችን ኢየሱስ፡ ወደእነርሱ ቀርቦ፡ እንዲህ ሲል ነገራቸው፡-'እንግዴህ፡ ኺዱና አሕዛብን ኹሉ አስተምሩዋቸው! ስታጠምቋቸውም፡ ‹በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም!› በሉ! አላቸው።" የሚለው፡ የመጨረሻው ነው። (ማቴ. ፳፰፥ ፲፰-፳።)

ሰው የኾነውን እግዚአብሔር፡ በዓይኖቹ ያየውና ንግግሩንም፡ በጆሮዎቹ የሰማው፡ ባለምሥራቹ ሓዋርያ፡ ቅዱስ ዮሓንስ፡ ስለዚሁ፡ ታላቅ ምሥጢር፡ አያሌ ቍም ነገሮችን የጻፈ ሲኾን፡ ለምሥራቹ መልእክት፡ መክፈቻ አድርጎ የዘገበው ቃል፡ ለዚህ እውነታ፡ አንዱ ዓይነተኛ ማረጋገጫ ነው።

ይኸውም፡ "ቀዳሚሁ፡ ቃል ውእቱ፤ ወውእቱ ቃል ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ፤ ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል። ...ቦቱ፡ ሕይወት ውእቱ።" ማለትም፡ "በመጀመሪያው፡ ቃል ነበረ፤ ቃልም፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም፡ እግዚአብሔር ነበረ። ...በእርሱ፡ ሕይወት ነበረች።" የሚለው ነው። (ዮሐ. ፩፥ ፩-፬።)

በዚሁ ምዕራፍና በዚሁ ንዑስ ርእስ ሥር፡ በገጽ ፶፮ (56)፥ አንቀጽ ፫ ላይ፡ *"የመሢሕን እግዚአብሄ[ሔ]ርነት ይገልጣሉ በማለት ክርስቲያኖች ከሚያቀርቧቸው ዋና ዋናዎች መረጃዎች መካከል ለምሣሌ"* ይህ፡ ከዚህ በላይ የተመለከተው፡ የዮሓንስ ቃል፡ አንዱ እንደኾነ ተደርጎ በቅድሚያ ሲወሳ፥ ይህንም *"መሰ[ሠ]ረት አድርገው የሚሉት ነገር ሁ[ኹ]ሉ የተጣመመ ትርጉምን ያዘለ ተረት ነው።"* ተብሎም ሲነቀፍ፡ ጥቅሱ፡ ለምን ተቀናንሶ ቀረበ? ማለትም፡ "ቃልም፡ እግዚአብሔር ነበረ።" የሚለው፡ ዋናው ኃይለ ቃል፡ ለምን ተዘለለ? ባለማወቅ? ወይስ፡ በስሕተት? ወይስ፡ ኾነ ተብሎ? ትክክለኛ ምክንያቱን የምታውቁ አንተ፥ ተባባሪ ካለህ ደግሞ፡ እርሱና አምላክህ ስትኾኑ፡ በአስተዋይ ተመልካች ግን፡አድራጎቱ፡ ታማኝነት የጎደለው፡ የክፉ ምልክት ኾኖ ይታያል።

፷፪. በዚሁ ምዕራፍና በዚሁ ንዑስ ርእስ ሥር፡ በገጽ ፶፯ (57)፥ አንቀጽ ፫ ላይ፡ "እኔና አብ አንድ ነን። አብ፡ በእኔ እንዳለ፡ እኔም በአብ አለሁ።" የሚለውን፡ ግልጽና ቀና አባባል፡ ያጣመመና ያከፋ፥ እንዲያውም ያጠማዘዘና ያጨለመ የትኛው ዓይነት አፈታትና አባባል እንደኾነ ለይቶ ለማወቅና ለማሳወቅ፡ እስኪ፡ በራሱ፡ በትችቱ ውስጥ የቀረቡትን ተነጻጻሪ አንድምታዎች፡ በማማረጫ ጥያቄ መልክ አድርጌ ላቅርባቸው!?

እነዚህም፡ ያ፡ በተዋሕዶ ምሥጢር፡ ሰው የኾነው እግዚአብሔር ወልድ፥ እርሱም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ይህን ቃል የተናገረበት፡ አንደኛው አማራጭ ምክንያት፡ *"መሢሕ ከአምላክ እንደ አምላክ ኾኖ የተፈጠረ ሰው በመሆ[ኾ]ኑ በእርሱነቱ ውስጥ እንደ አምላክ የኾነ ምሣሌና እንደ አምላክ የሆ[ኾ]ነ መልክ መኖሩን ለመግለጥ ነውን?"* የሚል ሲኾን፥ ሌላው አማራጭ ምክንያት ደግሞ፡ ወይስ፡ "ራሱ፡ ፈጣሪ እግዚአብሔር መኾኑን ለመግለጥ ነው?" የሚለው ነው።

ለዚህ ጥያቄ፡ መልስ ለመስጠት፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ መመላት፥ ወይም፡ የዕድሜ ልኅቀት፥ ወይም፡ ፊደል መቁጠር እንኳ አያስፈልግም፤ ማንም፡ ነፍስ ያወቀ፥ አእምሮው፡ በአንዳች ጠንቅ ያልተበከለ፥ ጤናማና ቅን የኾነ ተራ ሰብኣዊ ፍጡር፡ በቀላሉ የሚመልሰው ነው፤ መልሱም፡ ያለጥርጥር፡ ከላይ የሠፈረው፡ "ራሱ፡ ፈጣሪ እግዚአብሔር መኾኑን ለመግለጥ ነው!" የሚለው፡ ኹለተኛውና የመጨረሻው ነው። ከዚህ የተለየው ሌላኛው ተቃራኒ መልስ ግን፡ ምንጩ ከየት እንደኾነ ለይቶ ለማወቅ፡ ለእምነት ሰው አይቸግረውም።

ይህን ቃል ለማረጋገጥ፡ ከዚህ የሚከተለውን፡ የተያያዘ ጥቅስ፡ በማስተዋል መመልከቱ ይበቃል፤ ይኸውም፡ በዓይናቸው ከሚያዩት መምህራቸው አንደበት፡ በቀጥታ በጆሮአቸው እየሰሙ ካሉት ተማሪዎቹ አንዱ፡ "እግዚኦ! አርእየነሁ ለአብ፤ ወየአክለነ።" ማለትም፡ "አቤቱ! አብን አሳየንና ይበቃናል።" ብሎ፡ ጌታችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን በጠየቀው ጊዜ፡ የሰጠው መልስ ነው፤ እርሱም፡ "ዘርእየ ኪያየ፡ ርእዮ ለአብ።" ማለትም፡ "እኔን ያየ፡ አብን አይቷል።" የሚለው ሲኾን፡ ይህንኑም እውነታ፡ አጠንክሮ ለማረጋገጥ፡ ከዚህ የድምዳሜ ቃሉ አስቀድሞ፡ ጠያቂውን፡ በበለጠ ሊያሳምነው ፈልጎ፡ "መጠነዝ መዋዕል፡ ሀሎኩ ምስሌክሙ፤ ኢያእመርከኒኑ ፊልጶስ?" ማለትም፡ "አንተ ፊልጶስ! ይህን ያህል ዘመን፡ ዐብሬአችሁ ስኖር፡ አታውቀኝምን?" በማለት ያቀረበለት መጠይቃዊ መልስ ይበቃል። (ዮሐ. ፲፬፥ ፩-፲፩።)

እውን የኾነው ነገር፡ ለሰዎች ገብቷቸውና አውቀውት እንዲቀበሉትና እንዲያምኑበት፡ በፈጣሪ አንደበት ሳይቀር፡ እንዲህ፡ ብሩህ ኾኖ የተነገረውንና የተብራራውን የእግዚአብሔር እውነት፡ እንደገና ተብትቦና አወሳስቦ፡ ማደነጋገር፡ ከባድ ጥፋት ነው፤ ኃጢአትም ነው።

፳፫. በዚሁ ምዕራፍና በዚሁ ንዑስ ርእስ ሥር፡ በገጽ ፶፱ (59)፥ አንቀጽ ፫ እና በገጽ ፷ (60)፥ አንቀጽ ፩-፪ ላይ፡ *"የሚገርመው የመሢሕን ምንነትና ማንነት በምንም መልኩ መንዝረውት ከእግዚአብሄ[ሔ]ር ጋር ማስተካከል ማለት ሐሳዊ መሢሐዊነት መሆ[ኾ]ን ማለት እንደሆ[ኾ]ነ ሰዎች አለመረዳታቸው ነው። ምክንያቱም እግዚአብሄ[ሔ]ር መንፈስ እንደ መሆ[ኾ]ኑ መጠን ብስባሽ ሥጋና ደም ሊኖረው ይቅርና የእርሱን መንግስ[ሥ]ት እንኳ ሥጋና ደም ሊወርስ እንደማይችል እየታመነ በአዳምነቱ ፈራሽ ሥጋ ለብሶ የተፈጠረን ሰው በምንም መልኩ ፈጣሪ አምላክ ነው የሚል ሰው ካለ 'መሢሕ በሥጋ እንደመጣ የማያምን ሐሳዊ መሢሕ ነው' በሚለው ቃል መሰ[ሠ]ረት እርሱ ሐሳዊነትን የሚያራምድ ሰው ነው።"* በሚል ዘይቤ፡ እስካኹን፡ በዚህ መልክ ሲሠነዘር የቆየው ስሑትና ንፉቅ አስተሳሰብ ኹሉ፡ ዓላማውና ግቡ፡ ለምን እንደኾነ፡ ወረድ ብሎ የተጻፈው፡ *"ጥንታዊ[ው]ያን ሊቃውን[ት]ቶች ...በሥላሤ[ሴ] የተረጎሙትን የተሳሳተ የፍልስፍና አቅጣጫ እኛ በዚህ ዘመን የተቃና ትርጉም እንዲኖረው አድርገን <u>ክርስትያኑም ሆ[ኾ]ነ እስላሙ</u> በዚህ ጉዳይ ላይ በአንድ ሀ[ሓ]ሳብ እንዲግባባ ማድረግ አያዳግተንም።"* የሚለው ጠንቀኛ አስተያየት ገላልጦ ያሳያል።

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እስልምና ከመፈልሰፉ፥ ወይም፡ በመሢሕ ተቃዋሚው መንፈስ ግፊት ከመከሠቱ፡ እጅግ ቀደም ብለው፡ ከአያሌ ሺህ ዓመታት በፊት፡ ከፈጣሪያቸውና አምላካቸው ያገኙትንና አጽንተው ያቆዩትን፡ የቅዱሱን ኪዳን እምነታቸውን፡ እንደዓለማውያኑና እንደሥጋውያኑ ባዕዳን ሰዎች፡ በሰውኛው ብልጠት፥ በገንዘብ ስስትና በሥልጣን ጥማት አይለውጡም፤ አያሻሽሉም፤ ለማናቸውም ዓይነት ድርድር አያቀርቡም።

በዓለሙ ሃይማኖቶች፡ በአንዳቸውም ዘንድ፡ ድጋፍንና ተገኝነትን ሊያገኝ ባለመቻሉ፡ መጠጊያ አጥቶ በመሳደድ ላይ የነበረው እስልምና፡ መጠለያ አግኝቶና ተስተናግዶ፡ በደኅና ወደመጣበት መዲናው የተሸኘው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው በቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ መኾኑ ሊዘነጋ አይገባም።

ዛሬ ያለው የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ትውልድ፡ ሊፈጽም የሚገባው ግዳጅ ቢኖር፡ ከእውነተኛ ኢትዮጵያዊነቱ ስቶ የወጣውን ወገኑን ኹሉ፥ ወደእስላምነት የገባውን ጭምር፡ እውነቱን አሳውቆ፡ ወደቀደመውና ለእስልምና እምነት ጭምር መጠጊያ ሊኾን ወደቻለው ወደእውነተኛ ማንነቱ፡ ማለትም፡ ወደቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱ እንዲመለስ ማድረግ እንጂ፡ እንደገና የባሰ እንዲጠፋ ወደሚያመራው የስሕተት መንገድ እንዲኼድ ማሳየት አይደለም።

በዚህ ረገድ፡ ሼህ ዘከርያ፥ ኋላም፡ "አለቃ ዘካርያስ"፥ ይልቁንም፡ ወደክርስትና እምነታቸውና ኢትዮጵያዊነታቸው፡ በጥምቀት ተመልሰው፡ ዐማራ ሲኾኑ፡ "ንዋየ ክርስቶስ" የተባሉት፡ የእስልምና ሊቀ ምሁራን፡ ስለፈጸሙት ገድልና ሙያ የሚገልጸውን ሓተታ፡ ከመጻሕፍቴ፥ በተለይም፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በሚለው ውስጥ ተመልክተኸው ይኾናል፤ ስለዚህ፡ እግዚአብሔር፡ በቅዱስ መንፈሱ እርሳቸውን አነቃቅቶና አነሣሥቶ፡ ለኢትዮጵያና ለልጆቿ፥ በተለይም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ለሚለው፡ ለዛሬው ትውልድ፡ የፈጸመው የታዳጊነት ሥራው፡ እጅግ ታላቅ ትምህርታዊና ለአርአያነቱ ወደር የሌለው ነውና፡ ማነኛውም ኢትዮጵያዊ በአትኩሮትና በማስተዋል ሊመለከተውና ሊያውቀው የሚገባ ቍም ነገር መኾኑን፡ እዚህ ላይ አበክሬ ማሳሰብን እወድዳለሁ።

በአጠቃላይ፡ በዚህ ምዕራፍና በንዑሳን ርእሶቹ ሥር ተደጋግሞ የተነሣው ስሑት (የተሳሳተ) አሳብና የተሠነዘረው የኑፋቄ (የጥርጣሬ) አስተያየት ሲገመገም፡ የዕፀ-በለስ መጽሓፍ ደራሲ፡ ያልተረዳውና ያልገባው ነገር ያለ ይመስላል። ይኸውም፡ እኛ የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች፡ "'መሢሕ' የምንለው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ብቻው አምላክ፥ ወይም ብቻው ሰው ሳይኾን፡ ፍጹም አምላክም፥ ፍጹም ሰውም የኾነው፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው እግዚአብሔር ወልድ መኾኑን ካለማወቅ፥ ወይም፡ ይህ እውነታ ታውቆ ከኾነ፡ ይህንኑ እውነታ ኾነ ብሎ ለማፈራረስ ከሚደረግ ሙከራ የተነሣ ነው!" ብሎ ወደመደምደሙ የሚያስኬድ አዝማሚያ እንዲኖር የሚጋብዝ ኹኔታ ስለሚታይ ነው።

ምክንያቱም፡ ከላይ፡ በየቦታው ተደጋግሞ እንደታተተው፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በተዋሕዶ፡ ከኹለት፡ ማለትም፡ ከመለኮትና ከሰውነት አካላት፡ አንድ አካል፥ ከኹለት፡ ማለትም፡ ከመለኮትና ከሰውነት ባሕርያት፡ አንድ ባሕርይ የኾነ፡ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው!" ስለምንል፡ ይኸው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ራሱን፡ "እኔ" ብሎ በሚጠራበት የአንድነት ማንነቱ፡ የመሢሕነቱን ሥራ፡ በአሳብም፥ በንግግርም፥ በግብርም ይፈጽማል።

ይህም ማለት፡ በዚያው የእኔነት አንድነቱና ማንነቱ፡ በአንድ በኩል፡ ከኃጢአት በቀር፡ ፍጹም የሰውን ጠባይና ግብር ሲፈጽም ይታያል፤ በሌላ ጎኑ ደግሞ፡ በዚያው የእኔነት አንድነቱና ማንነቱ፡ የአምላክነቱን ባሕርይና ሥራ ሲፈጽም ይገኛል። ይህ በመኾኑ፡ "የለም፡ መሢሕነቱ፡ በአዳማዊው ሰውነቱ ብቻ እንጂ፡ በመለኮታዊው እግዚአብሔርነቱ አይደለም።" ወይም ደግሞ፡ "የለም! መሢሕነቱ፡ በመለኮታዊው እግዚአብሔርነቱ ብቻ እንጂ፡ በአዳማዊው ሰውነቱ አይደለም።" ሊባል አይገባም። መሢሕነቱ፡ በኹለቱም በኩል ያለውን ግዳጅ፡ በትክክልና በተሟላ ኹኔታ የፈጸመበት መኾኑ ሊታመንበት ይገባል።

በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ውስጥ ያለው የመለኮትነቱ አካልና ባሕርዩ፡ በተዋሕዶ ከድንግል ማርያም የተወለደበትን የሰውነት አካልና ባሕርይ፡ በእግዚአብሔር መልክ ለተፈጠረበትና "ከእኛ እንደአንዱ ኾነ!" ተብሎ፡ የመጨረሻውን ክብር ለተቀዳጀበት ፍጹም ልዕልና ስላበቃው፡ ያ ሥጋዊ አካልና ባሕርይ፡ የክፋት ኃይል፥ የኃጢአት ፍዳና የሞት ጽዋ የማያገኘው ኾኖ፡ አዲሱን የትንሣኤ አካልና ባሕርይ ለመልበስ ቻለ። ከዚህ የተነሣ፡ ለትንሣኤ፡ በኵር የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለዚያ ሰውነቱ፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ በሥጋም፥ በነፍስም፥ በመንፈስም ለመውረስ የሚያበቃውን፡ አዲሱን አካል በማልበስ፡ "ሥጋና ደም፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም!" የሚለውንና ሊሻር የማይቻለውን መለኮታዊ ቃል አጽንቶ፡ እውን አደረገው ማለት ነው።

ይህም እውነታ፡ በእኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን አማኞቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ ሳይቀር፡ ተፈጻሚነት ያለው መኾኑን፡ እንዲህ የሚለው፡ የሐዋርያው የምስክርነት ቃል ያረጋግጥልናል፡- "ናሁ ኅቡአ ነገረ እነግረክሙ! አኮ ኵልነ ዘንመውት። ወባሕቱ ኵልነ ንትዌለጥ፡ በምዕር፡ ከመ ቅጽበተ ዐይን፡ በደኃሪ ንፍኀተ ቀርን። ወይነፍኁ ቀርነ፤ ወይትነሥኡ ምውታን፡ እንዘ ኢይትነከዩ፤ ወንሕነኒ ንትዌለጥ። እስመ ሀለዎ ለዝንቱ ዘይማስን ይልበስ ዘኢይማስን፤ ወዝንቱ መዋቲ ይልበስ ዘኢይመውት።"

የዚህም፡ "እነሆ፡ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ! ኹላችን የምናቀላፋ አይደለንም። ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ፡ ወዲያው፡ በቅጽበተ ዓይን እንለወጣለን። መለከት ይነፋልና፤ ሙታንም፡ የማይበሰብሱ ኾነው ይነሣሉ፤ እኛም እንለወጣለን። ይህ የሚበሰብሰው፡ የማይበሰብሰውን ሊለብስ፥ ይህም የሚሞተው፡ የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና።" ማለት ነው።

ይህ የብቅዓት ጸጋ፡ ለብዙዎች የተገኘው፡ ሐዋርያው፡ "ወለእግዚአብሔር አኰቴት፡ ዘወሀበነ ንማዕ በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ!" ማለትም፡ "በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል፡ ይህን ድል መንሣትን ለሰጠን እግዚአብሔር፡ ምስጋና ይኹን!" ሲል እንደደመደመው፡ ሰው በኾነው እግዚአብሔር ወልድ መኾኑ እርግጥ ነው። (፩ቆሮ. ፲፭፥ ፶፩-፶፰፤ ፩ተሰ. ፬፥ ፲፫-፲፰። ራእ. ፳፥ ፩-፮።)

"ሥጋና ደም፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም!" በሚለው ቃል መሠረት፡ ከአዳምና ሔዋን አንሥቶ፡ እስከዛሬ፡ ሰዎች፡ ሥጋና ደማቸውን ብቻ ሳይኾን፡ ነፍሳቸውን ጭምር፡ ለሞት፥ ለመቃብርና ለሙስና (ለመበስበስ) የዳረጉት፡ በየራሳቸው የግል ምርጫ፡ ከክፉት ጋር በመወገናቸውና እየራሳቸውን ከፈጣሪያቸው ሕይወት ለሚለያቸው ለኃጢአት በማስገዛታቸው መኾኑ፡ በራሱ በፍጥረት ዘንድ፡ ተረጋግጦ ከታወቀ ዘመናት አልፈዋል።

በዚህ አንጻር ደግሞ፡ በሰው ጥንተ ተፈጥሮ እንደሚታወቀው፡ ከመለኮት ባሕርይ ተከፍላ በመገኘት፡ ሰውን፡ "በእግዚአብሔር መልክ ተፈጠረ!" ያስሰኘችው ነፍስ፡ ካላት ንጽሓ ባሕርይ የተነሣ፡ እስከመጨረሻው የሚጸናው ምርጫዋ፡ የእግዚአብሔር ወገን የኾነው መልካሙ በሚኾንበት ጊዜ፡ ሥጋዋን ጭምር፡ ሞት ሊነካው የማይችልና ወደመቃብር ሊወርድ የማይገባው፡ የማይበሰብስ እስከመኾን የምታደርስ መኾኗ፥ ማለትም፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ለሚያስችለው፡ ለዚያ፡ ለትንሣኤ አካል የምታበቃው መኾኗ፡ ቀደም ብሎ እንደተነገረው፡ በሄኖክና በኤልያስ፥ በመጨረሻም፡ አምላክን በወለደችው፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ሕያው ዕርገት ታይቷል።

ይህ ትንግርታዊ ኹኔታ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት በተገኘው የትንሣኤ ጸጋ፡ በይበልጥ እውን ኾኗል፤ ይኸውም፡ ምርጫው፡ እግዚአብሔራዊው መልካም የኾነው ሰብአዊው ፍጡር፡ በዚህ ምድራዊ ዓለም፡ ገና፡ በሕይወተ ሥጋ እየኖረ በሚገኝበት ጊዜ እንኳ፡ ነፍሱ ብቻ ሳትኾን፡ ሥጋው ጭምር፡ በመጀመሪያው መንፈሳዊ ትንሣኤ፡ ባለዕድል ኾኖ፡ ለብፅዕና እንዲበቃ ማድረግ የሚችል ስለመኾኑ፡ ባለምሥራቹ ዮሐንስ፡ በራእዩ በጻፈው መልእክቱ፡ አብራርቶ ገልጾታል። የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በምድር ላይ፡ በሕይወተ ሥጋቸው የሚገኙበት ኑሮ፡ የምሥራች! ይህ መኾኑን የማያውቅ ካለ፡ ይወቀው!

ስለዚህ፡ በዚሁ ምዕራፍና በዚሁ ንዑስ ርእስ ሥር፡ በገጽ ፸፩ (71)፥ አንቀጽ ፫ እና በገጽ ፸፪ (72)፥ አንቀጽ ፩ ላይ፡ *"በሰው ስ[ሥ]ጋዊ ገፅ[ጽ]ታ ላይ የክፉ አልያም የመልካም መንፈሳዊ ድባብ ሰፍኖ በመታየቱ ብቻ እንዲሁም በሰው ምድራዊ ህ[ሕ]ይወት ላይ የሁ[ኹ]ለቱ ተቃራኒ ባህሪ[ሕርይ] በመንፀባረቁ ብቻ 'ሰውን በመልካችን እንደ ምሣሌአችን እንፍጠር' የሚለው ቃል ሙሉ ለሙሉ በምድር ላይ ተግባራዊ ሆ[ኾ]ኖ ተጠናቋል ማለት አይደለም። በቅድሚያ ከአፈር የተገኘው ፈራሽ አካል በሞት ተወግዶ ወደ አፈርነቱ መመለስ ይኖርበታል።"* የሚለው አስተሳሰብ፡ ፈጽሞ ውድቅ ይኾናል።

በዚህ መሠረት፡ "ተረት" እና "ፍልስፍና" የሚሉት ስያሜዎች፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ የተመሠረተውን፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት እምነትን እንደማይጨምር በማመን፡ ይልቅስ፡ እንደተረትና ፍልስፍና ሊቆጠር የሚገባው፡ "በዚህ መጽሓፍህ ውስጥ የተሠነዘረው አስተያየት ነው!" ቢባል ያስኬዳል።

፳፬. በምዕራፍ አምሥ[ስ]ት፥ *"በኩ[ኵ]ሩ ማነው?"* በሚለው፡ ዋና ርእስ ሥር፡ በገጽ ፸፭ (75)፥ አንቀጽ ፪፡ *"ከጥንት ሲጀመር ገና አምላክ የእርሱ መንግስ[ሥ]ት ወራሾች ይሆ[ኾ]ኑ ዘንድ ተስፋውንና እምነቱን በፈጠረው ሰው ላይ አሳርፎ ነበር። ይሁ[ኹ]ንና አብርሀ[ሃ]ም እስካመነበት እ[ዕ]ለት ድረስ ይህ ተስፋው ይፈጸም ዘንድ አምላክንና ሰውን የሚያገናኝ ድልድይ አልተዘረጋም ነበር። ነገር ግን አብርሀ[ሃ]ም ተስፋውንና እምነቱን መልሶ በአምላክ ላይ ባሳረፈ ጊዜ አምላክንና ሰውን የሚያቀራርብ ድልድይ ለመጀመሪያ ግዜ ለመዘርጋት ተቻለ።"* የሚለው አገላለጽ፡ ያለትችት የሚታለፍ አይደለም፤ እርሱም፡ ከትዝብት ጋር፡ በአንድ ዐረፍተ ነገር ይጠቃለላል፡-

የቅዱስ ኪዳኗን ኢትዮጵያንና ልጆቿን በሚመለከት፡ እኔ እንኳ፡ በቅርቡ፡ በሰፊና በዝርዝር ትንተና የጻፍኳቸው፡ ቍጥራቸው አነስተኛ ያልኾነ መጻሕፍት መኖራቸውን፡ ማወቅ ብቻ ሳይኾን፡ አንዳንዶቹን፡ ራስህ አንብበሃቸው፡ መልእክታቸውን የተረዳህ መኾንህ፡ የሚታመንበት መኾኑ፡ በግልጽ እየታየ ቀርቶ፤ ያም ባይኾን እንኳ፡ በኢትዮጵያዊነትህ ብቻ እንኳ፡ ይህን የመሰለውን አስተያየት፥ ያውም፡ በመጽሓፍ ውስጥ ማሥፈርህ፡ ያስገምታል፤ ያስተዛዝባልም። ምክንያቱም፡ አብርሃምን፡ ለአምልኮተ እግዚአብሔርና ለመለኮታዊው ቃል ኪዳን ያበቃውን፡ እነመልከ ጼዴቅን የመሰሉ፡ ስመጥር ማንነታቸውና ገናና ሥራቸው፡ ዓለም በተቀበለው መጽሓፍ ቅዱስ ውስጥ ጭምር የተመዘገበላቸው ቅዱሳን የእግዚአብሔር ታማኞች ልጆችና አገልጋዮች ኢትዮጵያውያን እያሉ፡ እንደሌሉ መቆጠራቸው ነው። (ዘፍጥ. ፲፬፥ ፲፯-፳። ዕብ. ምዕ. ፭-፯።)

ከዚሁ ርእስ ጋር በተያያዘ፡ ስለአብርሃም፡ ቀደም ብሎ፡ በየቦታውና በየአግባቡ የተነገረ ስለኾነ፡ ከዚያ አልፎ፡ እዚህ ላይ መድገሙ አላስፈለገም።

፳፭. በዚሁ ምዕራፍ፥ *"ሣራና አጋር የጽድቅና የፍርድ ኪዳኖች ናቸው"* በሚለው፡ ንዑስ ርእስ ሥር፡ በገጽ ፸፯ (77)፥ አንቀጽ ፩ ላይ፡ *"በአምላክና በሰው መካከል የተገባውን ሶ[ሦ]ስተኛ ቃል ኪዳን አብርሀ[ሃ]ም በተቀበለበት ወቅት"* ብለህ ስትጽፍ፡ የቅዱሱ ኪዳን፡ ሦስተኛ የኾነውንና እግዚአብሔር፡ ለአብርሃም፡ ነቢይ፥ ሓዋርያና ካህን አድርጎ ከላከው፡ ከመልከ ጼዴቅ ጋር የተጋባውን፡ መደበኛውን ቃል ኪዳን ወዴት ወስደኸው ነው? ተራውን አዛንፈኸው ነው? ወይስ፡ ጨርሰህ ሠርዘኸው ነው? ይህማ ከኾነ፡ ካለፈው ስሕተትና ጥፋት፡ የአኹኑ ይባስ የሚያስሰኝ ነው።

፳፮. በዚሁ ምዕራፍ፥ በዚሁም ንዑስ ርእስ ሥር፡ በገጽ ፸፰ (78)፥ አንቀጽ ፩ ላይ፡ *"መሢሕ* [ኢየሱስ ክርስቶስ] *የጽድቁን መንገድ በብርሃን ትመላለሱበት ዘንድ የምሥራች ቃሉን ላሰማችሁ መጣሁ በማለት በእርሱ በኩል የጽድቁ ተስፋ መፈጸሙን ባበሰ[ሠ]ረበት ወቅት የፍርዱ ተስፋ ከእርሱ እ[ዕ]ርገት በኋላ እንደሚፈጸም ከመናገሩ በቀር በዘመኑ ፍርድን አስመልክቶ ስለ ወረደ መንፈስ ያለው ነገር አልነበረም።*

*"የፍርድ ተስፋ መፈጸሙ ይረጋገጥ ዘንድ ወቅቱን ጠብቆ መሀመድ በተነሳ[ሣ] ግዜ በቅዱስ ቁርዐን ላይ የፍርዱ መንገድ በብርሀ[ሃ]ን ተሞልቶ በእያንዳንዱ ሰው ልቦና ውስጥ በመንፈስ መውረዱን በስፋት ሲያብራራ በሙሚሕ በኩል የጽድቁ ተስፋ ስለመፈጸሙ ከመናገሩ በቀር ጽድቅን አስመልክቶ በእርሱ ዘመን ስለወረደ መንፈስ ያለው ነገር አልነበረም።"* ተብሎ የተጻፈው አሳብ፡ ሌላው አስገራሚ ግላዊ አስተሳሰብህ ነውና፡ አጭር መጠይቃዊ ማስተካከያ ሊሰሰጠው የሚገባ ይኾናል።

"አላወቅህም!" እንዳልል፡ ማወቅህን ተረድቻለሁ፤ "አላነበብህም!" እንዳልል፡ ለብዙ ዓመታት፡ ጥናትና ምርምር እንዳደረግህ ጽፈሃል፤ ታዲያ! ሰው የኾነው ፈጣሪ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከመስቀለ ሞቱና ትንሣኤው በፊት፡ ለሐዋርያቱ፡ "ወኢየኀድገክሙ እጓለ ማውታ ትኩኑ! እስመ አነ እመጽእ ኀቤክሙ። እምድኅረ ኅዳጥ መዋዕል፡ ወኢይሬእየኒ እንከ ዓለም፤ ወአንትሙሰ ትሬእዩኒ። ...ወጰራቅሊጦስ መንፈሰ ጽድቅ፡ ዘይፌኑ አብ በስምየ፡ ውእቱ፡ ይሜህረክሙ ኵሎ፤ ወያዜክረክሙ፡ ኵሎ ዘነገርኩክሙ አነ።"

ማለትም፡ "እንደሙታን ልጆች አልተዋችሁም! ወደእናንተ እመጣለሁና። ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ ዓለሙ እንግዴህ አያየኝም፤ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ። ...አብ በስሜ የሚልከው፡ የእውነት መንፈስ የኾነው አጽናኝ፡ እርሱ፡ ኹሉን ያስተምራችኋል፤ እኔም የነገርኋችሁን ኹሉ ያሳስባችኋል።"

ደግሞም፡ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላና ከማረጉ በፊት፡ "አዘዞሙ፡ ኢይፃኡ እምኢየሩሳሌም፤ አላ ይጽንሑ ተስፋሁ ለአብ። ወይቤሎሙ፡ 'ዮሐንስ አጥመቀ በማይ፤ ወአንትሙሰ፡ ታጠምቁ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ እስከ መዋዕል፡ ዘኢኮነ ርኁቀ። ...ሶበ ይወርድ ላዕሌክሙ መንፈስ ቅዱስ፡ ትነሥኡ ኃይለ፣ ወትከውኑኒ ሰማዕትየ ...እስከ አጽናፈ ምድር።'"

ማለትም፡ "አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል እንዲጠብቁ እንጂ፡ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው! አላቸውም፡ 'ዮሐንስ፡ በውኃ አጠመቀ፤ እናንተ ግን፡ ሩቅ ባልኾነ ጊዜ ውስጥ፡ በመንፈስ ቅዱስ ታጠምቃላችሁና! ...መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ፡ ኃይልን ትቀበላላችሁ! ...እስከምድር ዳርም፡ ምስክሮቼ ትኾናላችሁ!'" ባላቸው መሠረት፡ ያ የተስፋ ቃሉ ተፈጽሞ፡ በበዓለ ኀምሳ፡ ማለትም፡ በተነሣ በአምሳኛው ቀን፥ ይህን በተናገራቸውም፡ በአሥረኛው ቀን፡ የእግዚአብሔር የእውነት መንፈስ የኾነው "መንፈስ ቅዱስ፡ በኹሉም ሞላባቸው።" የሚለውን፥ ከመሀመድ ቁርዐን በፊት፡ የስድስት መቶ ዓመታት ቅድሚያ ያለውን፡ በእውንና በገሃድ የኾነውን፡ የእግዚአብሔርን እውነትና የተጻፈውን የእግዚአብሔርን ቃል፡ እንደሌለ ቆጥረህ፡ እንዲያ ብለህ መጻፍህ፡ በቀጥታና በግልጽ፡ ወደማን እንደወገንህ የሚያመለክት አይመስልህምን? (ዮሐ. ፲፬፥ ፲፰-፳፮፤ የሐዋ. ምዕ. ፪።)

እንግዴህ፡ በዚያን፡ በመጀመሪያው የትንሣኤ ሕይወት ወራት፡ በሐዋርያት ላይ የወረደው፡ መንፈስ ቅዱስ ከኾነ፡ ከስድስት መቶ ዓመታት በኋላ፡ በመሀመድ ላይ የወረደው መንፈስ የማን ይመስልሃል? ወይስ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ እንደገና ወርዷል ሊባል ነውን? እርሱ ካልኾነ፡ ታዲያ የማን ሊኾን ይችላል? በአንድ አምላክነትና በሦላሴነት ከሚመለከው፡ ከእግዚአብሔር፥ ከመሢሕ ኢየሱስና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንተ ያወዳደርከው፡ "ሰይጣን" የተባለው፡ የክፋት መንፈስ ነውን? ወይስ፡ ሌላ?

የማን ወገን መኾንህን ለማረጋገጥማ፡ በዚሁ ገጽ፡ ወረድ ብለህ፡ በ፪ኛው አንቀጽ፡ *"...አብርሀ[ሃ]ም ለአምላክ ፈቃድ ተገዢ ሆ[ኾ]ኖ እስማኤልን ለመሰ[ሠ]ዋት በወሰነ ግዜ ልጁም መስዋእ[ዕ]ት ለመሆ[ኾ]ን ፈቃደኛ በመሆ[ኾ]ኑ ምክንያት በአዳም አለመታዘዝ ተጥሎ የነበረው የቅጣት ፍርድ በምህ[ሕ]ረት ይነሳ[ሣ] ዘንድ በእርሱ በኩል ተስፋውን እንዳገኘንና ያንንም ተስፋ መሀመድ ይፈጽመው ዘንድ አዳም በመሢሕነቱ መከራን ተቀብሎ፡ መንገድ እንደከፈተለት ማረጋገጥ ችለናል።"* በሚል ቃል የሠነዘርህኸው አስተያየትህ በቅቶኛል።

፳፲. በዚሁ ምዕራፍ፥ <u>*"ነብዩ መሀመድና ስድስተኛው ቃል ኪዳን"*</u> በሚለው፡ ንዑስ ርእስ ሥር፡ በሰፊው የተሰጠውን ሓተታ ለማጠቃለል፡ በገጽ ፹፫ (83)፥ አንቀጽ ፪ እና ፫ ላይ፡ *"...መልከ ጼዴቅ በሳሌም ላይ የነበረውን አ[ዓ]ይነት ሹመት የእስማኤል ነገድ የሆ[ኾ]ነው መሀመድ በአምላክ ፈቃድ መካ ላይ ተሹሞ ...ከአምላክ የወረደ እውነተኛ መንፈስ በሰው ልቦና ውስጥ ማደሩን በቅዱስ ቁርዐን ላይ አብስራ[ሥሯ]ል። ...መሢሕ ለይስሀቃውያኖች [ለይስሓቃውያን] ብቻ ሳይሆ[ኾ]ን ለሰው ልጆች በሙሉ የጽድቁን ተስፋ እንደፈጸመ ሁ[ኹ]ሉ ነቢዩ መሀመድም በዘመኑ ስድስተኛውን ቃል ኪዳን የተቀበለውና የፍርዱን ተስፋ የፈጸመው ለእስማኤል ወገኖች ብቻ ሳይሆ[ኾ]ን ለአዳም ዘር በመላ ነው።"* የሚለውን የግለሰብ ድምዳሜ በመጥቀስ ማጠቃለሉ ይበቃል።

ከላይ እንደተመለከተው፡ እግዚአብሔር፡ ከመልከ ጼዴቅ ጋር የተጋባውንና ለኢትዮጵያዊነትም መገለጫ አብነት የኾነውን፡ ሦስተኛውን ቃል ኪዳን፡ በበኩልህ ሠርዘህ፥ ወይም፡ እንደሌለ ቆጥረህ፡ የአብርሃምን፡ መተካትህ ሳያንስ፡ እዚህ ላይ ደግሞ፡ ሌላውን ስሕተትና ጥፋት ደገምኸው።

ይኸውም፡ "የአብርሃም ልጆች ነን!" የሚሉት፡ እስራኤላውያን አይሁድና እስማኤላውያን እስላሞች ተጨምረው፡ መላዎቹ የሰው ልጆች፡ "አንቀበለውም!" ብለው ሲቃወሙት፡ የኢትዮጵያ ልጆች ብቻ፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" እና "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" የሚል፡ ዘውዳዊ ምልክትና ዙፋናዊ ማኅተም ባለው፡ በስድስተኛው ቃል ኪዳን የታወቀውን፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ክህነታዊ ንጉሥነትና በድንግል ማርያም መቅደሳዊ ንግሥትነት የሚመራውን፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነታቸውን ክብርና ሥልጣን፡ ለመሀመድ አሳልፈህ መስጠትህ ነው።

ይህ መለኮታዊ መንግሥት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ጥንት፡ ከመጀመሪያው፡ በአዳምና ሔዋን፥ በመካከሉ፡ በመልከ ጼዴቅ፥ ኋላም፡ በዳዊት አማካይነት፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ከፈጣሪያቸው፡ ተቀብለውና አምነው የሚኖሩበትና የሚተዳደሩበት፥ የሚታወቁበትና የሚያገለግሉበት ነው።

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ ይህ አኹን፡ በአንተ ድርሰት የታየውን የመሰለው፡ የተራቀቀ ስልታዊ አካኼድና ብልሃታዊ ዘዴ፡ በእውነተኞች የእምነት ሰዎች ዘንድ፥ በተለይም፡ በቅዱስ ኪዳኗ የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ አይሠራም፤ እንኳንስ ግብሩ፡ አሳቡም የላቸውም። ይህን የመሰለውን ይትበሃል፡ ለየግልና ለኅብረት ዓላማቸው አውጠንጥነው የሚያቅዱት፥ አዘጋጅተው የሚጠቀሙበትም፡ በሥጋዊው ዓለም ይኖሩ የነበሩትና ዛሬም ያሉት፡ ብልጦችና ፈሊጠኞች ሰዎች ናቸው።

እነርሱም፡ በመሪያቸው፡ "ሰይጣን" በተባለው፡ በርኩሱ መንፈስ አበጋዝነት፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምረው እስከዛሬ፥ ወደፊትም፡ ይህን ኹሉ ጥረትና ድካም፡ በሥውርም ኾነ በገሃድ፥ በግዘፍም ኾነ በረቂቅ መንገድ የሚፈጽሙት፡ ለአንድ ለታወቀው፡ እኩይ ዓላማቸው ነው። ይኸውም፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ብቸኛዋ የእግዚአብሔር መንግሥት ኾና፡ በምድር ላይ፡ ህልውናዋ፡ እነሆ፡ ዛሬ፡ ለ፻፹፭፻፫ኛ የነጻነት ዓመት የበቃውን፡ ኢትዮጵያን ለመደምሰስ ነው። ይህም የመቃተት ሙከራቸው፡ እስካኹን፡ ከግብ ሊደርስ እንዳልቻለ ኹሉ፥ አኹንና ወደፊትም፡ እንዲሁ፡ የማይቻል ፡ ከንቱኾኖ ይቀርላቸዋል።

ከላይ ተብራርቶ እንደተገለጸው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ በተነሣ፡ በአምሳኛው ቀን፥ ወደሰማይ ባረገም፡ በአሥረኛው ቀን፡ ሓዋርያት፡ ከብዙ አህጉር ከመጡ ሕዝብ ጋር በዓለ ሃምሳን ለማክበር በተሰበሰቡበት፡በኢየሩሳሌም፡ መንፈስ ቅዱስ፡ የነበሩበትን ቤት አናውጾ፥ በእነርሱም ላይ፡ በእሳት ላንቃ አምሳል ከመወረዱና በሥፍራው ለነበሩ አያሌ ወገኖች፡ በየራሳቸው ቋንቋ፡ ምሥራቹን ከማሰማቱ፥ እንዲሁም፡ መላውን ዓለም፡ በጸጋው ከመሙላቱ በቀር፡ ከስድስት መቶ ዓመታት በኋላ፡ "እንደገና መጥቶ፡ በሌላ ሰው ላይ ወርዷል!" ከተባለ፡ "ያ መንፈስ፡ መንፈስ ቅዱስ ሳይኾን፡ ሌላው ተፃራሪው መንፈስ መኾን ይኖርበታል!" ተብሎ እንደተነገረ ይታወሳል።

አኹን ደግሞ፡ እዚህ ላይ፡ በመልከ ጼዴቅ ሹመት፡ ዘለዓለማዊ ካህንና ንጉሥ ኾኖ፡ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከመጣው፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር፡ ከእርሱ በኋላ የመጣ "ሌላ አለ!" ከተባለ፡ ያ ሰብአዊ ፍጡር፡ የዚያው የተጻራሪው መንፈስ መሣሪያ እንጂ፡ የእግዚአብሔር አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ አገልጋይ ሊኾን እንደማይችል፡ አስረግጦና አስተማምኖ መናገር ይቻላል።

አብርሃም፡ ከእምነቱና ከምግባሩ ብቅዓት የተነሣ፡ ከፈጣሪው በተስፋ የተሰጠው፥ ኋላም፡ እንዲሠዋው፡ ይኸው ፈጣሪው በጠየቀው ጊዜ፡ መለኮታዊዉን ፈቃድ ሊፈጽም በምግባሩ ያረጋገጠበት የቃል ኪዳን ልጁ፡ እስማኤል ሳይኾን፡ ይስሓቅ ስለመኾኑ፡ የቅዱሱ ኪዳን እምነታችን የሚመሰክረው አቅዋም፡ ከዚህ ቀደም ብሎ የተገለጸ መኾኑን፡ በማውሳት፡ ይህን ርእሰ ነገር አልፈዋለሁ።

፷፰. በምዕራፍ ስድስት፥ *"እምነት ከምን ተነስ[ሥ]ቶ ምን ላይ ይጸናል?"* በሚለው፡ ዋና ርእስ እና *"ሰባቱ የሀበሻ ቃል ኪዳኖች"* በሚለው ንዑስ ርእስ ሥር የሠፈረው ሓተታ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን እምነት የተመዘገበው፡ የሰባቱ ኪዳናት ተራ፡ በዚሁ መጽሓፍህ የተፋለሰ ከመኾኑ በላይ፡ ቀደም ብሎ እንደተመለከተው፡ "ኪዳነ ዳዊት" የምንለው፡ ዋናው፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነቷ መታወቂያ ምልክት፡ ለመሀመድና ለቁርዐን የተሰጠበት ኾኖ ይነበባል። በድንግል ማርያምና በኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ቁርባን እውን የኾነውና "ኪዳነ ምሕረት" የምንለው፡ ሰባተኛው ኪዳን፡ በግልጽ አለመጠቀሱም፡ ጎልቶ ይታይበታል።

፷፱. በዚሁ ምዕራፍ፡ ዋና ርእስና ንዑስ ርእስ ሥር፡ በገጽ ፻፲፰-፻፲፱ (118-119) እና *"ህ[ሕ]ያው መቅደሳችንን ለመሞሸር በአንድ ልብ እንነሳ[ሣ]"* በሚለው ንዑስ ርእስ ሥር፡ በገጽ ፻፳፫ (123) ላይ፡ *"ኢትዮጵያ ከዓለማት ሁ[ኹ]ሉ ተለይታ ያለምንም ቅድመ ኹኔታ በንጉስ[ሥ] አርማህ[ሕ] ታማኝነት በነብዩ መሀመድ በኩል ተፈጻሚ የሆ[ኾ]ነውን የፍርድ ተስፋ ተቀብላ የስድስተኛውን ቃል ኪዳን ማህ[ኅ]ተም የሆ[ኾ]ነውን ቅዱስ ቁርዐን በእርሷ ዘንድ ከነበረው ኦሪትና ወንጌል ጋር አዋህ[ሕ]ዳ በነገሥታት ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ግዜ የተቀበለች ብቸኛዋ ሀገር ሆ[ኾ]ና እናገኛታለን። ...ንጉስ[ሥ] አርማህ[ሕ]ም በቀጥታ በአምላክ መንፈስ ተመርቶ ቁርዐንን ሊቀበል በመቻሉ ከእምነት አንጻር ከማንኛውም ሀገር በተለየ መልኩ የቃል ኪዳኑ ምእ[ዕ]ራፍ የተገለጠው በዚች ሀገራዊ ስሜት ላይ ነው ማለት እንችላለን። ...ስድስተኛውን ቃል ኪዳን መሀመድ በተቀበለበት ወቅት በሀ[ሐ]በሻው ንጉስ[ሥ] አርማህ[ሕ] መንግስ[ሥ]ት ላይ የጽድቁና የፍርዱ ዙፋን መቀመጫ ኾና ተሰየመች።"* በማለትና መልእክቱን ለማጠናከር ተደጋግሞ ለተነሣው ነገር፡ ባጭሩም ቢኾን፡ ተገቢውን ማስተካከያ መስጠት ያስፈልጋል።

ይህን ርእሰ ነገር በሚመለከት፡ ይህን የመሰለው መልእክት፡ በዚህ መጽሓፍህ ውስጥ ተደጋግሞ ሊቀርብ የተፈለገበት ምክንያት፡ "ምን ዓይነት አስገዳጅና ከኢትዮጵያዊነት፡ ምን ያህል፡ ብልጫነት ያለው ቢኾን ነው!" ስለሚያስሰኝ፥ ይልቁንም፡ እግዚአብሔር፡ ለዳዊት የሰጠው ስድስተኛው ቃል ኪዳን፡ መሢሕንና መለኮታዊቷን መንግሥት የያዘ ሲኾን፡ ይህ፡ ውድቅ ኾኖ፡ በእርሱ ምትክ፡ ይኸኛው የመሀመዱ እንዲጸና፡ በመጽሓፍ መመዝገቡ ቀርቶ፡ መታሰቡም እንኳ፡ ያስገርማል።

ኢትዮጵያ፡ የኪዳነ ልቡናውም፥ የኪዳነ አሪቱም፥ የኪዳነ መንፈስ ቅዱሱም ተቀባይና አማኝ፥ ባለአደራና ጠባቂ በመኾን፡ በእውነት የእግዚአብሔር መንግሥት ለመኾኗ ምስክሩ እኮ፡ ቀደም ባለው ዘመን፡ በኪዳነ ልቡና እምነት የሚመሩትን አረማውያንን፡ ከነአምልኳቸው፥ በመካከለኛውም ዘመን፡ በኪዳነ ኦሪት እምነት የሚመሩትን አይሁድን፡ ከነታቦተ ጽዮናቸው፥ በመጨረሻውም ዘመን፡ በልዩ ልዩ ስያሜ በኪዳነ ምሕረቱ የክርስትና እምነት የሚመሩትን ክርስቲያኖችን፥ ከእነዚህ ኹሉ "የተለየሁ ነኝ!" ብሎ፡ የኋላኋላ፡ በሠይፍ ኃይል ተመክቶ የሚካኼደውን የእስልምናንም እምነት እንኳ ሳይቀር ተቀብላ ማስተናገዱ ነው።

የሃይማኖቱ መሥራች መሀመድም ቢኾን፡ "ኢትዮጵያ" የምትባለው አገር፡ ቤተ ሕዝቧ፥ ቤተ ምልክናዋና ቤተ ክህነቷ፥ የእነዚህ ብሔራውያን አቋሞች ርእስ የኾነው አጼውም፡ ኹሉም፡ ደጋጎችና ሥዩማነ እግዚአብሔር ኾነው፥ የእግዚአብሔርን ሥርዓት ጠብቀውና በዚያ የእውነት መንፈስ እየተመሩ የሚተዳደሩባት መኾናቸውን፥ ማንኛውም ሰው፡ ሳይገፋና ሳይጨቆን፡ በነጻነት የሚኖርባት መኾኗን ስላወቀ፡ አልነበረምወይ፡ የቅርብ ቤተ ሰቡን፡ "እናንተም፡ በዚያ፡ መልካም አቀባበልና መስተንግዶን ታገኛላችሁና፡ ወደዚያ ኺዱ!" ብሎ የላካቸው? ለእነርሱስ፡ በእኒያ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ ያን የመሰለው አቀባበልና መስተንግዶ ተደርጎላቸው አልነበረምወይ፡ የፈለጉትን ያህል በእንግድነት ቆይተው የተሸኙትና ወደአገራቸው ወደመሀመድ የተመለሱት?

በዚህስ ኹኔታ፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የእውነቱና የመንግሥቱ መቅደስና ባለአደራ የኾኑትን ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ለመጠበቅ ሲል፡ በክርስቶስ ተቃራኒ መንፈስ ይመራ የነበረው መሀመድ፡ ስለኢትዮጵያና ስለልጆቿ፡ ያን የመሰለውን ጽኑ መመሪያና ማስጠንቀቂያ፡ ለተከታዮቹ ትቶ እንዲያልፍ ማድረጉ፡ ፍጡሩ በኾነውና "ሰይጣን" በተባለው፡ በርኩሱ የክፋት መንፈስ ላይ፡ የመቆጣጠር ሥልጣን ያለው መኾኑን የሚያረጋግጠው እውነታ መገለጡ አይደለምን? ያን የመሪያቸውን መመሪያና ማስጠንቀቂያ በድፍረት ተላልፎ፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ልጆች ላይ፡ ጥቃትን የፈጸመ፥ ጉዳትንም ያደረሰ እስላማዊ ወገን፥ ወይም አገር፡ የመጨረሻ ውድቀትና ጥፋት እየደረሰበት ታይቷል፤ እንደቀደሙት ቱርክና ግብፅ፥ እንደዛሬዎቹም፡ ፓኪስታን፥ ሱማሌ፥ ሊቢያ፥ ኢራቅና ሱዳን፥ እንደቀረውም፡ የዓረብና የእስላም ዓለም ማለት ነው።

በዚያን ጊዜ የነበረው አጼ አርማሕ፡ ይህን በጎ አድራጎት በመፈጸሙ፡ "ቁርዐንን ተቀበለ!" ብሎ፡ በድፍረት መናገር ይገባልን? አይገባም። አጼው፡ ያን እምነት፡ በእርግጥ ተቀብሎ ቢኾን ኖሮ፡ ከጥንት ጀምሮ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ሲሠራበት እንደኖረው፡ እንደኪዳነ ልቡናውና እንደኪዳነ ኦሪቱ፥ እንደኪዳነ መንፈስ ቅዱሱም የክርስትና እምነት፡ ለምን፡ ቤተ ክህነቱ፥ ቤተ ምልክናውና ቤተ ሕዝቡ፡ ማለትም፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ መላዋ ኢትዮጵያ፡ የእስልምናን እምነት አልተቀበሉም?

እስልምናም፡ ገና ከልደቱ ጀምሮ እስከዛሬ፡ በሌሎቹ አህጉር፡ በገሃድ ፈጽሞት እንደሚታየው ግብሩ ኹሉ፡ ለምን፡ ኢትዮጵያን፡ በሠይፉ ኃይል አምበርክኮና አሳምኖ፡ የእስልምና ግዛቱን አልመሠረተባትም? አዎን! ደግሞም፡ እስልምና፡ አንድን ሰው፥ ወይም፡ አንድን አገር፡ በግድም ኾነ በውድ፡ ወደሃይማኖቱ ካስገባ በኋላ እንደማይለቅ የታወቀ ሲኾን፡ ታዲያ፡ ያን የመሰለ ኹኔታ፥ በአህመድ ግራኝ ጊዜም ኾነ፥ እስካኹን፡ ለምን፡ በኢትዮጵያ አልታየም?

ከመጽሓፍህ፡ ከላይ የተጠቀሰውና ያልተጠቀሰው ተመሳሳይ አባባል ኹሉ፡ ፈጽሞ ሓሰት መኾኑን፡ ይህና እስከዛሬ፥ ዛሬም ያለው እውነታ ያረጋግጣል።

ስለዚህ፡ ይህንና እርሱን የመሰሉትን አርእስተ ነገሮች በሚመለከት፡ ባዕዳን የኢትዮጵያ ተፃረሪዎች፡ ኢትዮጵያዊ በኾነው፡ የእግዚአብሔር እውነት ላይ ካላቸው የጥፋት ዓላማ የተነሣ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸውና ወደፊትም እንደሚገለጸው፡ በዚህ ረገድ፡ በሓሰት የተሠነዘሩት አስተያየቶች ኹሉ ውድቅ ኾነው፡ በእግዚአብሔርዋ እውነት ሊስተካከሉ የሚገባቸው መኾናቸውን ላሳስብ እወድዳለሁ።

## ስለእስልምና መነሣት፡
## በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ያለው ምክንያታዊ እምነት።

እንግዴህ፡እግዚአብሔር፡ ከጥንት ጀምሮ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጣቶች፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልቦና ላይ ጽፎት፡ እነርሱም፡ በሕያው ሰውነታቸው ሕይወት አድርገውት እንደኖሩትና እንደሚያምኑበት፥ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያረጋግጡትም፡ ትንቢትና ነቢይነት፥ ሱባኤና ራእይ፥ ተስፋና ኪዳን፥ እንዲሁም፡ ርዕደተ መንፈስ ቅዱስ፡ በእግዚአብሔር እናት፡ ድንግል ማርያም እና በልጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተፈጽሞ አብቅቷል። ከዚህ በኋላ፡ ነቢይና ትንቢት፥ ሱባኤና ራእይ፥ ተስፋና ኪዳን የለም። ተፈጽሟል።

እንዲህ ከኾነ፡ <u>የመሀመድና የእስልምና መነሣት፥ ከዚያም አልፎ፡ የእምነቱ ጀማሪዎች፡ ወደኢትዮጵያ መጥተው በጥገኝነት መኖራቸውና ሃይማኖቱ፡ በጦርነት ኃይል ተስፋፍቶ፡ በይበልጥ የክርስቲያኑን ዓለም ማጥለቅለቁ፥ በአኹኑ ጊዜም፡ ከአስፈሪነት ደረጃ መድረሱ፡ "መሠረታዊ ምክንያቱ፡ ከቶ ለምንድር ነው?"</u> ለሚለው ጥያቄ፡ መልሱ፡ ባጭሩ፡ እንደሚከተለው ይኾናል፡-

ጥንት በመጀመሪያ፡ በአዳምና ሔዋን ፍጥረትና ሰውነት የተገለጸችው የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ምንም እንኳ፡ በኪዳነ ልቦናውና በኪዳነ ኦሪቱ ዘመናት፡ "ሰይጣን"፥ ወይም፡ "ዲያብሎስ" በተባለው፡ በፀረ እግዚአብሔሩ የክፋት መንፈስ ወጣኝነትና መሪነት፡ በኖኅ ጊዜ፡ ደርሶ የታየውን የጥፋት ውኃ በመሰሉ፡ ልዩ ልዩ የመቅሠፍት ማዕበሎች ብትናወጽም፡ በእግዚአብሔር ልጅነታቸው ሕይወት በሚኖሩት፡ በኢትዮጵያ የቅዱሱ ኪዳን ልጆች ዘንድ፡ መሠረታዊ ኹለንተናዋ ሳይነካ፥ የይፋ ህልውናዋም ተጠብቆ ቀጠለ።

ኋላም፡ በዘመኑ ፍጻሜ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው እግዚአብሔር ወልድ፡ በሕማማተ መስቀሉ ባፈሰሰው የመሥዋዕትነት ደሙ ዋጅቷትና አጽንቷት፡ ያ፡ በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያት ዘንድ ብቻ ተወስኖ የቆየው መሠረታዊ ኹለንተናዋና የይፋ ህልውናዋ፡ አኹን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ካህን ንጉሥነትና በድንግል ማርያም፡ መቅደስ ንግሥትነት፡ በመላው ዓለም ተዘርግቶና ተስፋፍቶ፡ ምስፍናው፡ በምልዓት ይካኼድ ጀመረ።

ይህችው የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እንዲህ እያደገችና እየገነነች በመጓዝ ላይ ሣለች፡ በዚሁ የእግዚአብሔር መንግሥትነቷ መቀጠል ሲገባት፡ በተለይ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት በኋላ ተከታትለው በመጡት፡ በቀዳሚዎቹ ጥቂት ምዕት ዓመታት ውስጥ፡ ሥጋዊው ሥልጣኔ በሰፈነባቸው አህጉር የሚኖሩት፡ እኒያ፡ "ተጠሪዎቿና አገልጋዮቿ ነን!" የሚሉት የቤተ ክህነቷ ወገኖች፡ በምሥጢራተ ሃይማኖት ጥራት ሽፋንና ሰበብ፡ እርስ በርሳቸው ከሚያደርጉት የፀጉር ሥንጠቃ ክርክርና ፀብ አልፈው፡ የሥልጣን ጥማታቸውንና የክብር ፍላጎታቸውን፥ የሀብት ጥቅማቸውንና የእውቀት ዕልቅናቸውን ሥጋዊና ዓለማዊ ፍትወት ለማርካት ሲሉ፡ ከቤተ ሕዝቧና ከቤተ ምልክናዋ ወገኖች ጋር መመሣጠርና ማሴር ጀመሩ።

የእርሱን፡ የባለቤቷን የኢየሱስ ክርስቶስንና የእናቱን የቅድስት ድንግል ማርያምን አብነትና የሓዋርያትን ፈለግ ገሸሽ በማድረግ፥ እንዲያውም በማቃወስ፡ "ሃይማኖት የግል፥ አገር የጋራ"፥ ወይም፡ "ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት (Church and State) ፈጽመው ተለያይተው፡ በየፊናቸው የየራሳቸውን ዓላማ ማካኼድ አለባቸው!" የሚለውን፡ የአገዛዝ ሰብአዊ ፍልስፍናና ሰይጣናዊ ስልት ለመተካት አሰቡ፤ አስበውም አልቀሩ፤ ይህንኑ አሳባቸውን ሊተገብሩ ቆርጠው ተነሡ! ተነሥተውም አልቀሩ፡ በሥራ ላይ ዐውለው ፈጸሙት።

አዎን! <u>ኢትዮጵያ ብቻ፡</u> ይህን፡ የሰዎችን፡ ሰይጣናዊ የምሥጢር ሴራ ባለመቀበል፡ በቅዱሱ ኪዳን ልጆቿ አማካይነት፡ ቤተ ሕዝቧን፥ ቤተ ክህነቷንና ቤተ ምልክናዋን፡ በምሥጢረ ተዋሕዶ አንድ አድርጋና አጽንታ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነቷን፡ ለብቻዋ ስትቀጥል፡ "ክርስቲያን ነን!" የሚሉት፡ የቀሩት የዓለም ሕዝቦች ግን፡ ከአይሁድና ከአረማውያን ጋር ሳይቀር በመሣጠር፡ ይህችኑ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስና ከድንግል ማርያም በአደራ የተረከቧትን፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ በእነርሱ በኩል በፈጠሩት፡ ሰይጣናዊ በኾነው ፍልስፍናቸው፡ ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት ብለው፡ ከኹለት በመክፈልና በመለየት፡ በአንድ ወገን፡ ካህናቱ፡ ቤተ ክህነቱን፡ "ቤተ ክርስቲያን" ብለው ለብቻቸው ያዙ፤ መንፈሳዊዉን ክፍልና ሃይማኖታዊዉን ሥልጣንም፡ አጠቃልለው ጨበጡ። በሌላው ወገን ደግሞ፡ ምሉኮቹ (የገዢው ወገኖች የኾኑት) ጨዋዎቹ፡ ቤተ ምልክናውን፡ "ቤተ መንግሥት" ብለው፡ ለብቻቸው ያዙ፤ ሥጋዊዉን ክፍልና ሰብአዊውንም ሥልጣን ጨበጡ።

ከዚህ በኋላ፡ የቤተ ሕዝቡ አባል የኾነው፡ እያንዳንዱ የክርስትና ምእመን፡ ወንዱም፥ ሴቱም፡ በእግዚአብሔር ጥንተ ተፈጥሮና በኢየሱስ ክርስቶስ ተዋሕዶ፡ አንድ የኾነ አንድ ራሱን፡ ከእምነቱ መመሪያ ውጭ፡ እንደገና፡ ሥጋና ነፍስ፥ ወይም፡ ሰብአዊና መንፈሳዊ፥ ወይም፡ ሃይማኖትና ዓለም ብሎ፡ ራሱን ከኹለት በመክፈል፡ ለሥጋዊ፥ ለሰብአዊና ለዓለማዊ ጉዳዩና ግልጋሎቱ፡ "መንግሥት" ወደተባለው ድርጅት፥ ለነፍሳዊ፥ ለመንፈሳዊና ለሃይማኖታዊ ጉዳዩና ግልጋሎቱ ደግሞ፡ "ቤተ ክርስቲያን" ወደምትባለው አቋም እንዲኼድ አስገደዱት።

እግዚአብሔር፡ ሰውን፡ ጥንቱኑ፡ በማንነቱ መልክ ሲፈጥረው፡ የሥላሴነቱ አርአያ የኾኑትን፡ ነፍስን፥ ሥጋንና መንፈስን፡ በተዋሕዶ አንድ አድርጎ የሠራው ሲኾን፥ ኋላ ግን፡ እኒህ አካላትና ባሕርያት፡ ማለትም፡ ቤተ ክህነቱና ቤተ ምልክናው፡ በክፋት ኃይል፡ በመለያየታቸው፡ ያ ሰብአዊ ፍጡሩ፡ ከመጨረሻ ውድቀት ላይ መድረሱን፡ ፈጣሪው አይቶ ስላዘነለት፡ የዚያን ፍጡሩን፡ ፍጹም ሰውነት ለብሶ፡ በዚያው ሰውነቱ፡ ካሣውን ከፍሎ፡ በመልካሙ የፍቅር መንፈስ፡ አንድ ያደረጋቸውን እኒያን፡ የነፍስ፥ የሥጋና የመንፈስ አካላትና ባሕርያት፡ እንደገና፡ በክፋት ኃይል መለያየት ታላቅ ኃጢአት ኾኖ ተገኘ።

ታዲያ! በፈጣሪ መልካም ሥራ ላይ የተፈጸመው፡ ይህ ታላቅ ኃጢአት፡ ምንን አስከተለ?

በዓለሙ የሠለጠኑትና የሰፈኑት የሰው ልጆች፡ የብቻው የፍጥረተ ዓለሙ ፈጣሪና ባለቤት የኾነው፡ የእግዚአብሔር የባሕርይ ሀብቱ የኾነችውን አንዲት መንግሥቱን፡ የቤተ ክህነቱ ሰዎች፡ እንዲህ አድርገው ከፋፍለው፡ ክህነትን፡ ለራሳቸው አስቀርተው፡ መንግሥትን ግን፡ ሰይጣናዊዉን ሥራ ያካኺዱበት ዘንድ፡ ለሰዎች፡ በይፋ አሳልፈው በመስጠታቸው፡ ለዚህ እኩይ ዓላማቸውና ግብራቸው፡ ተገቢ ዋጋቸውን ይከፍላቸው ዘንድ፡ ያን፡ ታላቁን ኃጢአት እንዲፈጽሙ፡ ላነሣሣቸውና ላደፋፈራቸው፥ ለደገፋቸውና ላስፈጸማቸው፡ ለዚያው የክፋት መንፈስ፡ እየራሳቸውንና ኹለንተናቸውን፡ ባጠቃላይ፡ አሳልፎ ሰጣቸው።

አዎን! ለመሀመድና ለመሀመዳውያን ሠይፍ ዳረጋቸው! መሀመድን፡ ከምድረ በዳ አስነሥቶ፡ እነሆ፡ ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ፡ እስከዛሬ፥ ዛሬም፡ በአረማውያኑ ጣዖት አምላኪዎችና በኦሪታውያኑ አይሁድ፥ በይበልጥም፡ በክርስቲያኑ ዓለም ላይ እያካኼደው ያለው፡ የሠይፍ ዘመቻ፡ መቀጫቸው ኾነ! እግዚአብሔር፡ ቀድሞ፡ በዘመነ ኦሪት፡ ለእስራኤል ልጆች፡ መቅጫ የሚኾኑ አሕዛብን፡ ሊያስቀር እንጂ፡ ምንጊዜም፡ ጨርሶ ላያጠፋ በተናገረው ዓይነት።

ስለዚህ፡ እስልምና የመጣው፡ በተለይ በንስሓ አልመለስ ያለውን፡ በስም ክርስቲያን፥ በአምልኮው ግን አረማዊ የኾነውን ዓለም ሊቀጣ መኾኑ፡ በይፋ መታወቅ አለበት! ትናንትናና ዛሬ፡ በዓይናችን ብረት እያየነው ያለነውና የምስክርነት ቃላችንን የምንሰጥለት እውነታው፡ ይኸው ነውና።

የሚያስገርመው፡ መሀመድ የመሠረተው እስልምናና ተከታዮቹ እስላሞች፡ ይህን የመሰለውን ደምሳሽ ጦርነት፡ በክርስቲያኑ የዓለም ሕዝብ ላይ እያካኼዱ፡ የክርስቲያን ማዕከሎች፥ መኖሪያዎችና መናኽሪያዎች የነበሩትን አህጉራት ኹሉ፡ እያሰለሙ ሲገዙ፥ እነኢየሩሳሌምንና አንጾኪያን፥ እስክንድርያንና ቍስጥንጥንያን የመሰሉትንም፡ ዋና ዋና የክርስቲያን መዲናዎችን ሲይዙ፡ ከላይ እንደተገለጸው፡ መጠጊያ አጥተው፡ ከቦታ ቦታ ሲባረሩ የነበሩትን፡ የመጀመሪያዎቹን እስላሞች ስደተኞች፡ በመልካም አስተናግዳ የሸኘችውና ኑሮአቸውን፡ በዚያው ለመቀጠል ለፈለጉትም ፈቅዳ፡ እስከዛሬ እንዲኖሩ ያደረገችው፡ ኢትዮጵያ ግን፡ በእግዚአብሔር መንግሥትነቷ፡ እስከዛሬ እንደቀጠለች መገኘቷ፡ ለዚሁ ማንነቷ፡ አንዱ ዓይነተኛ ምስክር ነው።

ከዚህም ጋር፡ የሃይማኖቱ መሥራች፡ መሀመድ፡ የቅርብ ቤተ ሰቡን ለጥገኝነት፡ "ወደኢትዮጵያ ኺዱ!" ብሎ፡ እነርሱን፡ ወደዚያ መስደዱና ለተከታዮቹም ሠይፈኞች፡ 'ኢትዮጵያውያንን፡ ካልነኳችሁ፡ አትንኳቸው!" የማለቱን እውነታ፡ እዚህ ላይ ዐብሮ መጠቀሱ አግባብ ይኾናል።

እግዚአብሔር፡ በተለይ፡ የዛሬው ክርስቲያኑ ዓለም፥ ኦሪታውያኑን አይሁድ ጨምሮ፡ በገዛ ፍላጎታቸውና ምርጫቸው ባመጡት ጥፋትና ኃጢአት ምክንያት፡ ለእስላማዊው የሠይፍ ቅጣት መዳረጋቸውን ዝም ብሎ የሚመለከተው፡ ስሕተታቸውን አጋልጦ በማቅረብ፡ ኹለቱም ወገኖች፡ ከፈጸሙት የአምልኮ ግብዝነታቸው ተጸጽተው፡ በንስሓ ይመለሱ ዘንድ፡ ሊያሳፍራቸውና ሊያስተምራቸው መኾኑ፡ በቀላሉ ተረጋግጦ ይታወቃል።

ይኸውም፡ በመሀመድና በተከታዮቹ እስላማውያን ላይ ያደረው፡ የክርስቶስ ተቃራኒው መንፈስ፡ የራሱን አሳሳች መንግሥት፡ የእግዚአብሔር አስመስሎ በማቅረብ፡ የእርሱ አማኞች የኾኑት አገልጋዮቹ፡ በዚህ ረገድ፡ በእንዴት ያለ ቅናትና ጽናት፡ ግዳጃቸውን እንደሚፈጽሙ፡ ክርስቲያኖችም፥ አይሁድም፡ ማየት እንዲችሉ ማድረጉ ነው።

ክርስቲያኑ ዓለም፡ አይሁድንና አረማውያንን ጨምሮ፡ አኹንም፡ ገና፡ የዚህ ድርጊት ትርጉም ያልገባቸው መኾኑ፡ በግልጽ ይታያል። ይህም ማለት፡ «እስላሞቹ፡ *"የዓለም ሕዝብ ሊኖረው የሚገባው መንግሥት፡ በመሀመድ በኩል የታወቀውና የመጣው፡ የአላህ መንግሥት ብቻ ነው፤ የህልውናና የአስተዳደር ሥርዓታችንም ኹሉ፡ በእርሱ ሕግ መሠረት መመራት አለበት!"* ካሉና እነርሱም፡ በዚሁ መሠረት ለመኖር ችለው፡ *"የቀረውም ዓለም፡ በዚህ ሥርዓት መኖር አለበት!"* ብለው፡ ይኸው፡ እንዲህ፡ በጦርነት እያስጨነቋችሁ ያሉ ከኾነ፡ ታዲያ! እናንተስ፡ 'ክርስቲያን ነን!' የምትሉ ወገኖች፡ እውነተኞች አማኞች ከኾናችሁ፡ ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባችሁ አስተውሉ!» ነው መልእክቱ።

«አዎን! የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች፡ ከጥንት ጀምረው፡ እስከዛሬና ዛሬም፡ በመጀመሪያው የትንሣኤ ሕይወት የሚኖሩባትን፥ በመካከሉም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "በውስጣችሁና በመካከላችሁ ናት!" ያላትን፥ በመጨረሻም፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ በፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ የሰፈነችውን፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ እናንተስ፡ እንደነርሱ፡ ለምን፡ በአዋጅ አሳውቃችሁና አጽንታችሁ፥ ሕጓን፡ ሕጋችሁ፥ ሥርዓቷንም ሥርዓታችሁ አድርጋችሁ አትኖሩባትም፤ አትመሩባትም፤ አትተዳደሩባትም?» ነው፡ በእስልምና የቅጣት ሠይፍ በኩል እየተላለፈ ያለው፡ የእግዚአብሔር መልእክት።

ይህን መለኮታዊ የምሥራች ጥሪ፡ ክርስቲያኑ ዓለም፥ አሪታውያኑ አይሁድና አረማውያኑ ጣዖት አምላኪዎች፡ መላው ፍጥረተ ዓለም፡ ሲቀበል፡ ወዲያውኑ፡ እስላማውያኑ ጦረኞች፡ ሠይፋቸውን ወደምድር ጥለው፡ የዕርቅ እጃቸውን ወደሰማይ ያነሣሉ፤ ሠይፋቸውን፡ ለቅጣት እንዲያነሡ ያነቃቃቸው ምክንያት ተወግዷልና። አለዚያ ግን፡ ይህ መለኮታዊ መልእክት፡ በኹሉም ወገኖች ዘንድ፡ ተቀባይነትን አግኝቶ እስካልተፈጸመ ድረስ፡ በምድር ላይ፥ በሰው ልጆችም መካከል፡ ደኅንነትና ሰላም፥ ፍቅርና ብልጽግና ከቶ አይኖርም። ፍጅቱና ዕልቂቱ፡ በበለጠ ይቀጥላል።

እስካኹን፡ ለአያሌ ዘመናት እንደታየው፡ የአእምሮው ብልሃትና ጥበብ፥ የገንዘቡ ብዛትና ፍሰሰት፥ የጦሩ ኃይልና ግዝፈት፡ የቱንም ያህል እየረቀቀ፥ እየናረና እየጨመረ እንዲኼድ ቢደረግ፡ ሥንዝር የሰላም ርምጃን ሊያመጣ እንዳልተቻለው ተረጋግጦ ታይቷል።

አዎን! በዚህ ረገድ፡ በኹሉም ፍጡር ዘንድ የሚፈለገው ጣፋጩ ፍሬ ሊመረትና ሊሰበሰብ፥ ሊያከማቹትና ተመግበውት ሊደሰቱበትም የሚቻለው፡ መልካሙ የእግዚአብሔር ሥርዓት፡ በእውነት ተቀባይነትን አግኝቶና በትክክል ተግባር ላይ ውሎ ሲፈጸም ብቻ ነው።

ይህን የምሥራች መልእክት የምታቀርብልን፡ የዚች፡ የእግዚአብሔር እውነት፡ ዕፁብ ድንቅ የምግባር ውጤት፡ ማንነታቸውና ሙያቸው፡ ከዚህ ቀደም ብሎ በተጠቀሱት፡ በእስልምና ስማቸው፡ ሼህ ዘከርያ፥ ኋላም፡ በጥምቀት፡ ወደዐማራነታቸው፡ ማለትም፡ ወደኢትዮጵያዊነታቸው ተመልሰው፡ በክርስትና ስማቸው፡ "ንዋየ ክርስቶስ"፥ በዓለም ስማቸውም፡ "አለቃ ዘካርያስ" የተባሉት፡ ቀድሞ፡ የእስልምና፥ በመጨረሻም፡ የክርስትና ምሁር በነበሩት፡ ኢትዮጵያዊ ሰውነትና ሕይወት ላይ ተከሥቶ ስለታየ፡ የእኚህ ስመጥሩ ኢትዮጵያዊ፡ ፍሬያማ ሥራቸውና ገናና ገድላቸው፡ እዚህ ላይ፡ በመልካም ምሳሌነት፡ እንደገና በአጽንዖት ሊወሳ ይገባል!

## አጭር ማጠቃለያና ማሳሰቢያ።

ስለኹለንተና ደኅነትህ የማስብልህና የምጨነቅልህ ትንግሌ!

ከእውነት ለመድረስ የምታደርገውን ብርቱ ጥረት፡ ከጽሑፎችህና ከመጽሓፍህ ለመረዳት ችያለሁ። በዚህ ይዘትህና ውጤትህ፥ በደራሲነት ሙያህና በቆራጥነትህም ሳደንቅህ ቆይቻለሁ። ይህንም፡ በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ላይ በጠቀስኋቸው፡ ባለፉት ደብዳቤዎቼ ገልጬልሃለሁና፡ ያወቅኸው ይመስለኛል።

አዎን! ስለኹለንተና ደኅንነትህ የማስብልህና የምጨነክልህ መኾኔን ግን፡ ፈጣሪዬና እኔ ብቻ ነን የምናውቀው። አኹንም፡ በመጽሓፍህ ውስጥ የሠፈሩትን አስተሳሰቦች በሚመለከት፡ የሠነዘርሁትን አስተያየት፡ ሳልቆጥብ፡ እንዲህ፡ በግልጽ ያበረከትሁልህ፡ በዚህ መሠረትና ባለብኝ የኃላፊነት ተልእኮ፥ ባከማቸሁትም እውቀት ላይ ተመርኩዤ መኾኑን፥ ደግሞም፡ አንተን ብቻ ሳይኾን፡ ሌላውን አስተዋይ ተመልካች ጭምር፡ ወደእውነተኛዪቱ የእግዚአብሔር እውነት ለማድረስ የሚያስችል ብሩህ መንገድ ኾኖ እንዲያገለግል በማሰብ መኾኑን እንድትገነዘብልኝ እሻለሁ።

በእኔ በኩል፡ የእግዚአብሔር እውነት፡ በኹላችንም ዘንድ እንዳለች አምናለሁ። በዚህ መልክ፡ እየራሳችን፡ እውነተኞች ከኾን፡ መልካም ነው፤ ምናልባት ግን፡ የተሳሳትንበት አንዳንድ ነገር ቢኖር፡ እየራሳችንን፡ በእውነተኛ ንስሓ መልሰን ማስተካከል እንችላለን። እንዲህ ሲኾን፡ በዚህ ጊዜና በዚህ ኹኔታ፡ በኹሉ ነገር ልንስማማ የማንችልበት ምክንያት የለም።

እንግዴህ፡ ከዚህ በፊት በጻፍሁልህ መልሶቼ ኹሉ የገባሁልህን የተስፋ ቃሎቼን፡ እነሆ፡ በዚህ ደብዳቤዬ፡ አጠቃልዬ በመፈጸም፡ የበኩሌን ድርሻ አከናውኛለሁ። ከአኹን በኋላ የሚቀረው፡ የአንተ ድርሻ ይመስለኛል።

በመጽሓፍህ ውስጥ፡ በአንተ የተጻፉት፥ እኔም፡ ትችቴንና የማስተካከያ አስተያየቴን የሰጠሁባቸው አስተሳሰቦች ኹሉ፡ "አንተ፡ ከራስህ ያፈለቅሃቸውና የራስህን እምነት የሚያንፀባርቁ ናቸው!" ብዬ በማሰብ፡ በእኔ በኩል፡ በቅዱሱ ኪዳን መሠረታዊ እምነታችን ረገድ፡ እንደተለያየን ለመገመት እንኳ፡ አልፈለግሁም፤ አልፈልግምም። ምክንያቱም፡ በዚህ ደብዳቤዬ መግቢያ ላይ፡ አንድ በአንድ እንደተጠቀስኋቸው ያንተው አባባሎችና አኹንም፡ በተጨማሪ፡ *"ከጸሐፊው ምናብ የፈለቁ ሳይኾኑ፡ '...መጽሐፍ ቅዱስንና ቅዱስ ቁርዐንን መሰ[ሠ]ረት አድርገናል!' ብለው የተለያዩ የክርስትና ኃ[ሃ]ይማኖትና እስላሞች የሚናገሩት ነገር ሁ[ኹ]ሉ ከመድበሉ መለኮታዊ ቃል ፍጹም የራቀና በክህደት መንፈስ የተሞላ የሥጋውያ[ን]ኖች ፍልስፍና መሆ[ኾ]ኑን ለመግለጽ' የቀረቡ ናቸው።"* በማለት፡ ስለነዚሁ አስተሳሰቦች፡ በዚሁ መጽሓፍህ መቅድም ውስጥ አረጋግጠህ እንዳብራራኸው፡ ያንተ፡ የግል አስተሳሰቦች እንደኾኑ አድርጌ መቁጠሩን ስላልመረጥሁ ነው።

ስለዚህ፡ የደብዳቤ ልውውጣችንን አመክሮ በጀመርንበት፡ በመነሻው ጊዜ በተስማማንበት አካኼዳችን መሠረት፡ ከአዳምና ሔዋን ፍጥረት ጀምሮ፡ እስከዛሬ ጸንቶ የቆየውንና የዓለም ሃይማኖቶች ኹሉ፥ እስልምና ጭምር፡ እውቅናን ሰጥተውት፡ በአክብሮትና በተዘክሮ፥ በአድናቆትና በፍቅር የሚመለከቱትን፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ እምነታችንንና ሥርዓታችንን፡ እኛም፡ በየራሳችን ጠብቀን፥ ሌሎችም እንዲጠብቁት በማድረግ፡ በዚህ፡ አንድ የተቀደሰ ዓላማ፡ ኹለታችንም፡ ዐባሪ ተባባሪ ኾነን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስንና ቅድስት እናቱን ኢትዮጵያን ድንግል ማርያምን፥ በእነርሱ ከምትመራው፡ መለኮታዊት መንግሥታቸው ጋር እናገለግላቸው ዘንድ፡ ከዚህ አስቀድሞ ተልኮልህ፡ በፊትህ የሚገኘውን የምስክርነት ቃልን የመስጠቱን ሥርዓት ፈጽመህ፡ ራስህን፡ ለዚህ፡ ታላቅና ዘለዓለማዊ ዕድል ታበቃ ዘንድ፡ ጥሪዬን፡ እንደገና አቀርብልሃለሁ።

ኹሉን የፈጠረውና የኹሉ ባለቤት የኾነው፡ አንዱና ሕያዉ፥ ደጉና ቸሩ አምላክ፡ እስከዛሬና ዛሬ፥ ለወደፊቱና ለዘለዓለሙ፡ ለኢትዮጵያና ለቅዱሱ ኪዳን ልጆቿ፥ ለዓለሙና ለፍጥረቱ፡ ያደረገውንና እያደረገ ያለውን፥ የሚያደርገውንም መልካሙን ኹሉ እየተመለከትን፥ ስለዚህ ኹሉ ጸጋውም እያመሰገንነው፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ ኾነን፡ በመጀመሪያው የትንሣኤ ሕይወት የምንገኝበትን መልካም ኑሮ፡ በያለንበት፡ በፍሥሓና በሓሤት እንቀጥላለን።

በሰላመ እግዚአብሔርና በድንግል ማርያም በረከት ደኅና ኹን!

ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ።